አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽንስ ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በ2012 ዓ.ም በፋና"ጉዞ ኢትዮጵያ"ና በኢቢኤስ "ኢትዮጵያን እንወቅ" ሳምንታዊ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ሸዋቀና ታህለው

ነሐሴ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በ2012ዓ.ም በፋና“ጉዞ ኢትዮጵያ”ና በኢቢኤስ“ኢትዮጵያን እንወቅ”ሳምንታዊ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና

በ


ሸዋቀና ታህለው

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አማካሪ

ዓለሙ ካሣዬ (ዶ/ር)

ነሐሴ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽንስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በ2012 ዓ.ም በፋና"ጉዞ ኢትዮጵያ"ና በኢቢኤስ "ኢትዮጵያን እንወቅ" ሳምንታዊ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና

ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ሸዋቀና ታህለው

2016 ዓ.ም

## የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| አማካሪ | ቀን | ፊርማ |
| -------------------------------- | -------------------------- | ------------------- |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| ----------------------------------- | -------------------------- | ----------------- |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| ----------------------------------- | ------------------------ | ------------------- |

# ማረጋገጫ

"በ2012 ዓ.ም በፋና "ጉዞ ኢትዮጵያ"ና በኢቢኤስ "ኢትዮጵያን እንወቅ" ሳምንታዊ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና " በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት በሸዋቀና ታህለው የቀረበው ይህ ጥናት ወጥ ሥራና እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ዲሲፕሊን መሠረት የቀረበ መሆኑን አሳዉቃለሁ፡፡

## የፈታኞች ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ___________________ ፊርማ_______________ ቀን_______________

የውጭ ፈታኝ ስም____________________ፊርማ_______________ ቀን_______________

የውስጥ ፈታኝ ስም____________________ፊርማ_______________ ቀን_______________

# ምሥጋና

በመጀመሪያ ይህ ጥናት እዚህ ደረጃ ላይ ይደርስ ዘንድ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው በማማከር ከጎኔ ለነበሩት መምህሬና አማካሪዬ ለዶክተር ዓለሙ ካሣዬ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ ለቀና ትብብራቸው የተለዬ አክብሮትና አድናቆት አለኝ፡፡ እንዲሁም ለጥናቱ የሚያስፈልጉኝን ቁሳቁሶች (የግል ኮምፒውተሩን ሳይቀር) ከማዋስ ጀምሮ የሚነበቡ መጻሕፍትንም በማፈላለግ ከፍተኛ እገዛ ሲያደርግልኝ ለነበረው የስራ ባልደረባዬ መምህር ፍሬስብሐት ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ጊዜአቸውንና ገንዘባቸውን ለሰጡኝ ለውዷ ባለቤቴ ለሮዛ መኮንን፣ ለልጆቼ ለየማርያም ሽዋቀና፣ለሜሎናይ ሽዋቀናና ለኤማሆስ ሽዋቀና ከፍያለ ምስጋና አቀርባለሁ ፡፡

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

አጠቃሎ ----------------------------------------------------------------------------------------iii
ምዕራፍ አንድ--------------------------------------------------------------------------------------1
1.መግቢያ-------------------------------------------------------------------------------------------1
1.1.የጥናቱ ዳራ -------------------------------------------------------------------------------------1
1.2.የጥናቱ ዓላማ ----------------------------------------------------------------------------------3
1.2.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ--------------------------------------------------------------------------3
1.2.2 የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች---------------------------------------------------------------------3
1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄ--------------------------------------------------------------------3
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት-----------------------------------------------------------------------------3
1.5. የጥናቱ ወሰን ---------------------------------------------------------------------------------3
1.6. ያጋጠሙ ችግሮችናየተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች----------------------------------4
ምዕራፍ ሁለት--------------------------------------------------------------------------------------5
2.ክለሳ ድርሳናት-----------------------------------------------------------------------------------5
2.1 የፎክሎር ምንነት------------------------------------------------------------------------------5
2.2 የፎክሎር ዘውጎች -----------------------------------------------------------------------------6
2.2.1 ሥነ-ቃል---------------------------------------------------------------------------------------7
2.2.2 ሐገረሰባዊ ትውን ጥበባት------------------------------------------------------------------9
2.2.3 ሀገረሰባዊ ልማድ ---------------------------------------------------------------------------10
2.2.4. ቁሳዊ ባሕል ---------------------------------------------------------------------------------11
2.3. ተግባራዊ ፎክሎር-------------------------------------------------------------------------------11
2.3.1.የተግባራዊ ፎክሎር ዘዴ ወይም አሰራር-----------------------------------------14
2.3.2. የተግባራዊ ፎክሎር ትግበራዊ አፈጻጸም ---------------------------------------14
2.4. የፎክሎርና የመገናኛ ብዙኀን ጥናት ትስስር--------------------------------------------15
2.5. የፎክሎርና የቴሌቭዥን ጥናት ግንኙነ --------------------------------------------------16
2.6. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ---------------------------------------------------------------------18
ምዕራፍ ሦስት -----------------------------------------------------------------------------------22
3. የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ----------------------------------------------------------22

3.1 የጥናቱ ንድፍ ----------------------------------------------------------------------22
3.2 የመረጃ ምንጭ--------------------------------------------------------------------22
3.3 የናሙና አመራረጥ ስልት ---------------------------------------------------------23
3.3.1 የቴሌቪዥን ጣቢያዎች አመራረጥ ---------------------------------------------23
3.3.2 ለጥናቱ የተለዩ ፕሮግራሞች አመራረጥ---------------------------------------23
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች--------------------------------------------------24
3.4.1 የቪዲዮ ፍተሻ--------------------------------------------------------------------24
3.4.2 ሰነድ ፍተሻ-------------------------------------------------------------------------25
3.4.3 ምልከታ-----------------------------------------------------------------------------25
ምዕራፍ አራት -------------------------------------------------------------------------26
4. የመረጃ ትንተና ---------------------------------------------------------------------26
4.1 በ 2012 ዓ.ም በፋናቴሌቪዥን በጉዞ ኢትዮጵያ
ፕሮግራም ውስጥ የተላለፉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና-----------------------26
4.2 በ 2012 ዓ.ም በኢቢኤስ ቴሌቪዥን በኢትዮጵያን እንወቅ
ፕሮግራም ውስጥ የተላለፉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና----------------------------58
ምዕራፍ አምስት------------------------------------------------------------------------71
5.ማጠቃለያ እና ይሁንታ--------------------------------------------------------------71
5.1 ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------------------71
5.2 ይሁንታ----------------------------------------------------------------------------76
ዋቢ መፅሐፍት----------------------------------------------------------------------------77
አባሪዎች-------------------------------------------------------------------------------------79

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት “በ2012 ዓ.ም በፋና“ጉዞ ኢትዮጵያ”ና በኢቢኤስ “ኢትዮጵያን እንወቅ” ሳምንታዊ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና” በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት ሁለቱ የቴሌቭዥን ተቋማት ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ የትኞቹ የፎክሎር ዘውጎች ተካተዋል?፤ ፎክሎራዊ ዘውጎቹ ለቴሌቭዥን ጣቢያዎቹ ምን ፋይዳ አላቸው?፤ ለጥናቱ በተለዩት ጣቢያዎች የፎክሎር መካተት ለመስኩ የምርምር ዘርፍ የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው?። ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ተችሏል።*

*ጥናቱ የተከተለው አይነታዊ የአጠናን ዘዴን ሲሆን፤በሰነድ ፍተሻና በቪዲዮ ምልከታ የተሰበሰበው መረጃ በገለጻና በትረካ ስልት ትንተና ተደርጎበታል።በመጨረሻም አራቱ የፎክሎር ዘውጎች ሥነ-ቃል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብና ቁሳዊ ባህል በተተኳዋሪ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች መካተታቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። ፎክሎሮቹ የሚያስገኟቸውን ፋይዳዎች በተመለከተም ማሕበረሰብን ከማስተማር፣ከቱሪዝም፣ከቴሌቭዥን ፕሮግራም፣ከጥናትና ምርምር፣ከመቀስቀስና ከማንቃት አኳያ አይተኬ ሚና ያላቸው መሆኑ ተመላክቷል። እንዲሁም የትረካ ስልትን የማሳመር፣የፕሮግራም ተደማጭነትን የማሳደግ ሚና ያላቸው መሆኑ፤ ለማስታወቂያ ስራዎች ተደራሽነትና አይረሴነት የሚጫወቱት ሚና መኖሩ፣ የታሪክ ጭብጥን ለማጉላትና ገጸ-ባህርያትን ለማቅረብም የማይናቅ ድርሻ ያላቸው መሆኑ፣ አድማጭና ተመልካቾች ለጣቢያዎቹ አድማጮችና ተመልካች ደንበኞች ሆነው እንዲቀጥሉ የማድረግ ሚና እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል።*

*በመጨረሻም አጥኚው ፎክሎር ለማኅበረሰብ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ዘላቂነት ይኖራቸው ዘንድ በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑትን ጨምሮ በተለያዩ ሚዲያዎች የተሰማሩ የፕሮግራም አቅራቢ ጋዜጠኞች ፎክሎሮችን በመዘገብና ሰንዶ በማቅረብ ተግባር በመትጋት ቁሳዊም ሆነ መንፈሳዊ ማህበረሰባዊ እሴቶችን ለትውልድ ለማሻገር ቢሞክሩ በሚል የመፍትሄ ሐሳቡን ለመጠቆም ሞክሯል።*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ፎክሎርና መገናኛ ብዙኀን በማኅበረሰብ ዕድገት ጥናት ዘርፍ የቅርብ ግንኙነት አላቸው፡፡ ፎክሎርን ስናነሳ የፎክሎር ባለቤት የሆነውን ማሕበረሰብ እናነሳለን፡፡ በአንጻሩ መገናኛ ብዙሃንንም ያለማሕበረሰብ ማሰብ ዓሣን ከውሃ ውጭ የማለምን ያህል የሚቆጠር ጉዳይ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ተከታዩ ማብራሪያና ገለጻ የሚያስረዳውም የሁለቱን ትስስር በተመለከተ በመሆኑ የሁለቱን ተራክቦ ምን መሰልነት ማሳያ ሰነድ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ፎክሎርና መገናኛ ብዙኀን የጠበቀ  ግንኙነት ያላቸው ስለመሆኑ በመስኩ ጥናትና ምርምር ያካሄዱ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በሁለቱ መካከል ስላለው ግንኙነት የተለያዩ የምርምር ስራዎች ሲከናወኑ የቆዩ ስለመሆኑ የJoyce(2014)መረጃ ያስገነዝባል፡፡እንደ እኚህ ምሁር ገለጻ ፎክሎርና መገናኛ ብዙሃን አንዱ ሌላውን በማጠንከርና በማጎልበት ትስስራቸውን አሳድገው የመጡ ናቸው ይላሉ፡፡ በዘርፉ በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ  የጥናትና ምርምር ስራዎችም የሚያስረዱት ይህንኑ እውነታ ነው፡፡ከእነዚህም መካከል Degh(1994) እና Boesinger(1990)ያቀረቧቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ መረጃዎች በቀጥታም ይባል በተዘዋዋሪ የፎክሎርንና የመገናኛ ብዙሃንን ትስስር የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ጥናቶቹ ጥቂት የማይባሉ ስራዎችን ናሙና የወከሉና ፎክሎሪስቶች እንዴት በፎክሎርና በመገናኛ ብዙሃን መካከል ስላለው ግንኙነት ከተለያዩ አመለካከቶች አንጻር እየተመራመሩና በተለያዩ ዘዴዎችና ምርምሮች እየሰሩ መሆናቸውን ያመላከቱ ስራዎች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የዘርፉ የጥናትና ምርምር እንቅስቃሴ ሲፈተሽ  ፎክሎር ከቴሌቭዥን መገናኛ ብዙኀን ጋር ስላለው የቆዬ ተራክቦና  የሁለትዮሽ ትስስር አመላካች የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችን እናገኛለን፡፡ ከነዚህም መካከል ተከታዮቹን ለአብነት ያህል ለማቅረብ ተችሏል፡፡

የፎክሎርና የመገናኛ ብዙኀን ጥናቶችን ግንኙነት አስመልክቶ በምርምር ስራዎች ይፋ ማድረግ የተስፋፋው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ እንደነበረ ይጠቀሳል ፡፡ ለዚህም እንደ Harold እና Innisna macluhan ያሉ ቀደምት ጥናቶችን በዋቢነት ጠቅሳ ዘይባ 2012 ዓ.ም ያቀረበችው መረጃ ያስገነዝባል፡፡ በዚሁ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ የተጀመረው የቴሌቭዥንና የፎክሎር ጥናት እየተስፋፋ በመሄድ በየጊዜው በተጠኑ ጥናቶች

ቴሌቪዥን በፎክሎር ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድርና ፎክሎርን ለመጠበቅ እና ለማስተዋወቅ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ማረጋገጥ እስከ ተቻለበት ደረጃ ላይ መደረሱን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ለአብነትም የDegh L.(1994) መረጃ እንዳመላከተው ፎክሎራዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ማጥናት ባህል የሚቀረፅበትን እና በሚዲያ የሚተላለፍበትን መንገድ ለማስተዋወቅ ግንዛቤን ይሰጣል፡፡ እንዲሁም ማህበረሰቦች ታሪኮችን፣ ምልክቶች እና ባህላዊ እሴቶችን እንዴት እንደሚጋሩ እና በትውልዶች ውስጥ እንደሚያስቀጥሉ እንድንገነዘብ ይረዳናል፡፡ በተጨማሪም ቴሌቪዥን በህይወታችን ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ እና የዓለምን የጋራ ግንዛቤ እንዴት እንደቀረጸው በተሻለ ደረጃ ለመገንዘብ ይረዳናል፡፡

በአጠቃላይ የ (Degh.L.1994) ሀተታ በውል እንደሚያስረዳው በቴሌቪዥን እና በፎክሎር ጥናት ላይ ትንታኔ የሰጡ ምሁራን በርካታ ቢሆንም ግንባር ቀደም ሆነው የሚጠቀሱት Handoo(2000)፣hoffmann(1965)፣Sullenserger(1974)፣Otero(1999)፣Handoo(2000)፣(Tatira 2001)፣Koven (2003)፣henderson and Baker(2003)፣Newton(2010)፣Staemmler(2005) እና Wood (2006) ናቸው፡፡ እነዚህ ምሁራን ፎክሎርና መገናኛ ብዙሃንን አስመልክቶ ባካሄዷቸው ጥናቶች በቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ ፎክሎር ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን መንገዶችና የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ደግሞ በፎክሎር ዘርፍ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ብሎም የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ፎክሎርን የተላመዱበትን እና እንዲሁም የተተረጎሙባቸው መንገዶችን መፈተሽ መቻላቸው ታውቋል፡፡

ይህ ጥናት በበኩሉ ትኩረቱን ለጥናቱ በተለዩ ሁለት የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ላይ በማሳረፍ በነዚህ ተቋማት አማካኝነት በ2012 ዓ.ም በተሰራጩ ፕሮግራሞች ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ትንታኔ ለማቅረብ ሞክሯል፡፡ ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች እንደምንረዳው የፎክሎርና መገናኛ ብዙሃን ትስስርን በተመለከተ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አያሌ ጥናቶች የመካሄዳቸውን ያህል በአንጻሩ በአማርኛ ቋንቋ የተጠኑት ግን በበቂ ደረጃ ላይ ናቸው ለማለት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ባለመሆናቸው ለዚህ ጥናት መካሄድ ምክንያት ሆነዋል፡፡

### 1.2. የጥናቱ ዓላማ

#### 1.2.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2012 ዓ.ም በኢቢኤስ “ኢትዮጵያን እንወቅ” እና እንዲሁም በፋና “ጉዞ ኢትዮጵያ ”ሳምንታዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ የቀረቡ የፎክሎር ዘርፎችን መለየትና የቀረቡበትን አግባብ መተንተን ነው፡፡

#### 1.2.2. የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች

* ለጥናቱ በተለዩት የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች የትኞቹ የፎክሎር ዘውጎች እንደ ተካተቱ መለየት፤
* ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በተሻለ ድግግሞሽ የዘገበው የትኛው ጣቢያ እንደሆነ ማሳየት፤
* በቴሌቭዥን ጣቢያዎቹ ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ የፎክሎር ዘውጎችን ማሳየት፤
* በቴሌቭዥን ጣቢያዎቹ ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ የፎክሎር ይዘቶች ማሳየት፤

### 1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

* ተተኳሪ ሚዲያዎች የትኞቹን ፎክሎራዊ ጉዳዮች በፕሮግራሞቻቸው አካተው አቅርበዋል?
* የትኛው የቴሌቭዥን ጣቢያ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በተሻለ ድግግሞሽ አካቷል?
* ልዩልዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ መካተታቸው የሚያስገኘው ፋይዳ ምንድን ነው?

### 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

የዚህ ጥናት አስፈላጊነት ከሚከተሉት ነጥቦች አንጻር የሚታይ ነው፡፡ እነዚህም ፦

❖ የፎክሎርና የቴሌቭዥን (በአጠቃላይ ደግሞ የመገናኛ ብዙሃንን)ትስስር እና አንዱ በሌላው ላይ የሚጫወተውን ሚና በዝርዝር የማሳየት ጠቀሜታ ይኖረዋል ፡፡

❖ ፎክሎርን ከቴሌቭዝን መገናኛ ብዙሃን ጋር በዚህ መልኩ አስተሳስሮ ማጥናት አንባቢያንን ከተለያዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ጋር የማስተዋወቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

❖ በተመሳሳይ መልኩ ሌላ ሰፊና ጥልቅ ምርምር ማካሄድ ለሚፈልጉ ወገኖች መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል የሚሉት ናቸው፡፡

### 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በተመረጡት ሚዲያዎች ውስጥ የተካተቱ (የቀረቡ) የፎክሎር አይነቶችንና ፋይዳቸውን በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይኼውም በ2012 ዓ.ም

በኢቢኤስ ቴሌቭዥን "ኢትዮጵያን እንወቅ" እና በፋና ቴሌቭዥን "ጉዞ ኢትዮጵያ" በተሰኙ ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ ተካትተው ለአድማጭ ተመልካች የተላለፉ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ብቻ የተመለከተ ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ በተተኳሪ ጣቢያዎቹ የተካተቱ የፎክሎር ዘውጎች ምን? ምን? እንደሆኑ ተለይተዋል፤ የተካተቱት የፎክሎር ዓይነቶች ፋይዳ ምን አንደሆነ ተመላክቷል ፡፡ከዚህ ባሻገር ጣቢያዎቹ የሚዘግቧቸውን (የሚያቀርቧቸው) ሌሎች ጉዳዮችና እንዲሁም ከሁለቱ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች በስተቀር ሌሎች የሚዲያ ተቋማትን በዚህ ጥናት ለማካተት አልተሞከረም፡፡

## 1.6. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

ይህን ጥናት በተፈለገውና በታለመለት ዓላማ መሰረት በማካሄድ ዳር ለማድረስ የተደረገውን ሙከራ የተፈታተኑ ተግዳሮቶች እንደነበሩ አይካድም፡፡ ከነዚህ ልዩልዩ ችግሮች መሀከል የሚከተሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የጥናቱ መረጃ የሚሰበሰበው በሰነድ ፍተሻ እንደመሆኑ መጠን ተፈላጊ ሰነዶችን ለማግነት በተደረገው ሙከራ በሁለቱም የቴሌቭዥን ድርጅቶች (ጣቢያዎች) ቅንነት የጎደለው መስተንግዶ አጋጥሟል፡፡ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው አካላት ከነሱ የሚጠበቀውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘትና ሌሎች ጉዳዩ በትክክል(በቀጥታ) የማይመለ ከታቸውን ግለሰቦች አገናኝቶ የመሸሽ ሁኔታም ሌላኛው ተግዳሮት ነበር፡፡ እንዲሁም አንዳንድ ባለ ድርሻ አካላት መረጃን በነጻነት ለመስጠት ሲቸገሩ ማየትና ቀጠሮ በተያዘባቸው ጊዜያት በተለያዩ ደራሽ ስራዎች ምክንያትና አንዳንዴም በቂ ባልሆነ ምክንያት ያለመገኘት ችግር በተደጋጋሚ ተስተውሏል፡፡

እነዚህ ሁሉ ችግሮች ባሉበት ሁኔታ ጥናቱ ቢካሄድ ሊፈጠር የሚችለዉን ክፍተት ከግምት ውስጥ በማስገባት መፍትሄ ለማፈላለግ ተሞክሯል፡፡ ከፍሲል የተዘረዘሩት ችግሮችን ቢቻል ሙሉበሙሉ ለመቅረፍ ካልተቻለም ለመቀነስ በዋናነት እንደመፍትሄ የተወሰደው እርምጃ በትእግስት ችግሮችን ለማለፍ መሞከርን፣ ያልተሳኩ ቀጠሮዎችን በጋራ ስምምነት ለሌላ ቀን ማመቻቸትን፣ የሚሰበሰበው መረጃ ከጥናቱ ዓላማ ውጭ ለሌላ ተግባር ሊውል እንደ ማይችል ማስረዳትን፣ ከተቋማቱ ኀላፊዎች ጋር ጥናቱ በታለመለት መሰረት ቢካሄድ ለተቋማቱ ስለሚኖረው ጠቀሜታ ማስረዳትን ያካተተ ነበር ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

ይህ ክፍል በጥናቱ ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ያላቸው ጽሑፎች እንዲሁም ቀደምት ጥናቶች ተከልሰው የቀረቡበት ነው፡፡

### 2.1.የፎክሎር ምንነት

“ፎክሎር” “ፎክ” እና “ሎር” ከሚሉ ሁለት የእንግሊዝኛ ቃላት ጥምረት የተዋቀረ ጽንሰ ሐሳብ መሆኑ እሙን ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ተጣማሪዎች እያንዳንዳቸው በቁማቸው የያዙትን ፍቺ ስንመለከት “ፎክ” የሚለው የሚወክለው የሰዎችን መሰባሰብ ወይም አብሮነት ሲሆን በአንጻሩ “ሎር” ደግሞ ሰዎችን ወደአንድ ያመጣውና ያሰባሰበው ርዕሰ ጉዳይ ወይም በአጭሩ ዕውቀት ማለት ነው፡፡ እንደ ታዋቂው የመስኩ ምሁር Dundes(1980፣6) ገለጻና ማብራሪያ የሁለቱ ተዋቃሪ ቃላት ጥምረት “የቡድን ዕውቀት” ማለት ነው፡፡ እኚህ ምሁር (1986፣6) ላይ በጉዳዩ ላይ ተመስርተው ያቀረቡት ብያኔ በውል የሚያስገነዝበው የጋራ ጉዳይ ያሰባሰባቸው ሁለትና ከሁለትም በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ “ፎክ” ተብሎ ሊጠራ መቻሉንና በብያኔው ውስጥም ለቡድኑ አባላት መሰባበሰብ መንስኤ /ምክንያት/ የሆናቸው የጋራ ባህርይ እንዳለም አስረድተዋል፡፡ይህንን የጋራ ባሕሪ አስመልክቶ Tolken (1996፣56) በበኩላቸው ሲያስረዱ ቡድን መገለጫቸው ባህልን መሰረት ያደረገ ተግባቦት ያላቸው ሰዎች ስብስብ ተደርጎ እንደሚታይ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም በፎክሎር መስክም ፎክሎር የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ ሲነሳ ሁልጊዜም የሰው ልጅና ሕይወቱን ይቃኛል፡፡

ሰለሞን (2007) ማርታና ማርቲን (2005፣8)ን በዋቢነት ጠቅሶ እንደገለጸው ፎክሎር ማለት በመደበኛ ህግ የማይገዛና ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ስለዓለማችን፣ስለራሳችን ስለማሕበረ ሰባችን፣ ስለእምነቶቻችን ፣ ስልባህሎቻችን ፣ ልምዶቻችን፣ ትውፊታችንና የምንማረው መደበኛ ያልሆነ ዕውቀት ሲሆን ይህም በቃላት ፣ በሙዚቃ፣ በባህርያትና በቁሳቁሶች የሚገለጽ ተደርጎ ይታያል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላኛው የመስኩ ጠበብት Ben-Amos (1979) በበኩሉ ፎክሎር ማሕበረሰቡ በቋንቋው አማካኝት ባሕላዊ እሴቶቹን የሚገልጽበት መስታዎት ከመሆኑ አንጻር የማህበረሰቡ ማንነት መግለጫና በውስጡም በርካታ እሴቶችን ያካተተ ስለመሆኑ በዝርዝር ያስረዳል፤አክሎም ፎክሎር አገልግሎት የሚሰጥበት ማህበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ንብረቱ እንደመሆኑ መጠን የሕዝቦች ልማድ፣ ወግ፣ እምነትና ጥበባትን ያካተተ የባህል ዘርፍ መሆኑንም አስገንዝቧል፡፡

በአጠቃላይ ከፍሲል ለማቅረብ እንደተሞከረው “ፎክሎር” የሚለው ቃል "ፎክ" /folk/ እና "ሎር"/lore/ ከሚሉ ሁለት የእንግሊዘኛ ቃላት ጥምረት የተገኘ ሲሆን "ፎክ"ን ህዝብ፣ ማህበረሰብ፣ ቡድን ወይም ክፍል ለማለት ስንገለገልበት"ሎር"ደግሞ ህዝቦች በጋራ የሚጠቀሚቸው የጋራ እውቀቶች፣ ጥበቦች፣ መረጃዎች፣ ውጤቶችና እነዚህ የህዝብ እውቀቶች የሚቀርቡበትን ቅርጽ ሁሉ የሚጠቀልል ጽንሰ ሐሳብ ነው፡፡ በሌላ በኩል “ሎር” ሊይዛቸው ከሚችሉ ዕውቀቶች መካከል ደግሞ ተረት፣ አፈታሪክ፣ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ሀገረሰባዊ እጅ-ሥራ፣ ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ የእነዚህን ቃላት ትርጓሜ ስናቀናጅም “ፎክሎር” ህዝቦች፣ ማህበረሰቦች ወይም ቡድኖች የፈጠሯቸው ዕውቀቶችን፣ ጥበቦችን፣ መረጃዎችን እና ውጤቶችን የሚገልጽ ቃል ሆኖ እንደሚታይ እንገነዘባለን፡፡

## 2.2. የፎክሎር ዘውጎች

በፎክሎር የጥናት መስክ ትኩረት ከሚቸራቸውና እንደ አንድ ንዑስ ርዕሰ ጉዳይ ከሚታዩ ነጥቦች መሀከል ፎክሎርን የመመደቡ ተግባር አንዱ ነው ፡፡ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ በመስኩ ምሁራን ዘንድ ወጥ የሆነ ምደባ አይታይም ፡፡ ይህንን ችግር ለማጥበብ ከተቻለም በመቅረፍ ስርዓት ለማስያዝና መልክ ለመስጠት ሲል ፎክሎርን በአራት ዋናዋና ክፍሎች የከፈላቸው መሆኑን የፈቃደ (1991፣2) መረጃ ያስገነዝባል፡፡ እነዚህ አራት ዋናዋና ክፍሎች የሚባሉትም ሥነ-ቃል (Oral Literature)፣ ሀገረሰባዊ ልማድ (Folk custom)፣ ቁሳዊ ባህል (Material Culture) እና ሀገረሰባዊ ትውንጥበባት (Performing Folk Arts) ናቸው፡፡ የዩኔስኮ መረጃ ደግሞ አራቱም ምደባዎች እንዳሉ ተውስደው ሐገረሰባዊ ልማድን ብቻ በሁለት በመክፈል የማይዳሰሰ ባህላዊ ቅርስ “Intanjible Cultural Heritage” ሚለውን በመጨመር በአምስት መድቧቸዋል፡፡ ይህንን ተጨማሪውን ምደባም የተፈጥሮ ዕውቀትና ትግበራ ይለዋል፡፡ ይህ ደግሞ ራሱንችሎ የሚወጣ ሳይሆን በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ሊካተት የሚችል ጽንሰ-ሐሳብን የያዘ ነው፡፡ ሰለሞን (2007)ም እንዲሁ ይህንን በአምስት ደረጃ አመዳደብን ተጠቅሞ (የዶርሰንን ምደባ) እንዳለ ወስዶ ሀገረሰባዊ ውክልናና ማህበረ ፖለቲካዊ ተቋም የሚሉትን በመጨመር በስድስት ይከፍላቸዋል፡፡ ሆኖም ሰለሞን የጨመራቸው ሁለቱ ዘውጎች ራሳቸውን ችለው ለብቻ ወጥተው የሚገኙ ሳይሆኑ በአራቱ ዋና ዋና የፎክሎር ዘውጎች ውስጥ በመካተት የሚገለጹ በመሆናቸው በዚህ ጥናት በፈቃደ (1991) በተገለጸው መሰረት ፎክሎርን በአራት አበይት ዘርፎች ከፍሎ የሚታይ ይሆናል፡፡ በዚህ ጥናት በተመረጡት ሁለቱም የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ውስጥ ተካትተው የሚገኙት የፎክሎር ዘውጎች አራቱም አይነቶች በመሆናቸው በአራቱም ላይ ትንተና ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት በፎክሎር ስር የሚጠቃለሉት አራቱም ዘውጎች (ርዕሰ ጉዳዮች) የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር በግሉ ወይም ከሌሎች ከመሰሎቹ ጋር በቡድን የሚከውናቸው ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ወዘተ ጉዳዮች /ድርጊቶች/ ናቸው ፡፡ አንድ ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ከቀደሙት መሰሎቹ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች በሚኖረው መቀራረብ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወርሶ እየተገለገለባቸው ያሉ አንጡራ ሀብቶቹ ናቸው ፡፡

## 2.2.1. *ሥነ-ቃል* /oral folklore/

ከስሙ እንደምንረዳው ስነ-ቃል የሚለው ሐረግ ከሁለት ስረው-ቃላት የተወሰደ ሲሆን "ሥነ" የሚለው ቅርጽ ብቻውን ውበት ወይም ጥበብ የሚሉትን ፍቺዎች የሚይዝ ይሆናል፡፡ ይኼውም በተለያዩ መስኮች እንደምንገለገልበት *ሥነ-ሥዕል*፣*ሥነ*-ጥበብ *ሥነ*-ጽሑፍ፣*ሥነ*-ምድር፣*ሥነ*-ፍጥረት፣*ሥነ*-ሰብዕ፣*ሥነ*-ውበት፣ወዘተ በሚሉት አውዶች ውስጥ እንደምናገኘው ነው፡፡ ከዚህ ጥናት አኳያ *ሥነ*-ቃል የሚለው ቃል በቁሙ የያዘውን ፍቺ ስንመለከት ጥሬ ትርጉሙ የቃል ጥናት እንደማለት ሲሆን በዚህ ውስጥ "*ሥነ*" የሚለውን ቃል በቁሙ ከወሰድን የተዋበ ቃል፣የቃል ውበት፣ውበት ያለው ቃል እና ጥበብ የተሞላበት ስምና ቃል እንደሆነ እንረዳለን፡፡

*ሥነ*-ቃል ማህበረሰቡ በረጅም የህይወት ውጣውረድ ዘመኑ እየፈጠረ ሲጠቀምበት የነበረ፤ እየተገለገለበትም ያለ፤ ለወደፊቱም ሲጠቀምበት የሚኖር አንጡራ ሀብቱ ነው፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱት ሎሮች ጠንካራ ፋክክርና አካላዊ መስተጋብር የማይጠይቁ ሲሆኑ በአብዛኛው የልጆችንም ሆነ የአዋቂዎችን የንግግር ክህሎት፣የማስተዋልና የማሰላሰል አቅም የሚያጎለ ብቱ እንደ መዝሙሮች፣ተረቶች፣እንቆቅልሾች፣እንካሰላንትያ፣ቀልዶች፣የተለያዩ ማንጓጠጦችን የሚጠቀልል እንደሆነ Elizabeth (2008) ይገልጻሉ፡፡

*"ሥነ-ቃል በመነገር ፣በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድ ማህበረሰብ ባህል ፣ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያ እና ልዩ ልዩ ክስተቶችን እና የህይወት መልኮችን መግለጫ ኪነ-ጥበብ ነው፡፡ ይህ ኪነ-ጥበብ ማህበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙት እና የሚያጠራቅሙት ቅርስ ከመሆኑም በላይ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት የሚከሰት ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሮ ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅም እና የገጠመኞቹም ማንጸባረቂያ ነው፡፡ ይህ ቃላዊ ኪነ-ጥበብ በተለይ ፊደል ቀርጸው በጽሑፍ በማይገለገሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ማንነትን እና አጠቃላይ የዓለም*

*አመለካከትን ቀርፆ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው።”/ዘሪሁን፤2007፣20/*

በአጠቃላይ ከፈሲል ከቀረቡት *መረጃዎችም እንደምንረዳው ሥነ-ቃል* ከሰው ልጅ *ታሪክ* ተነጥሎ የማይታይ እንዲሁም በስነ-ሰብና በማህበረሰብ ሳይንስ፣በፍልስፍና በስነ-አምልኮ፣ በሥነ-ጽሑፍ፣ ወዘተ መስኮችም ለረጅም ዘመናት ሲጠና ቢቆይም ለጽንሰ-ሐሳቡ ከተግባራዊ ብያኔ በስተቀር እስካሁን የተጠቃለለ ንድፈ-ሐሳባዊ ብያኔ አልተሰጠውም።

*ሥነ-ቃል* በሚለው የጥቅል ስም የሚካተቱት የ*ሥነ-ቃል* አይነቶች በርካታ ሲሆኑ ስነ-ቃልን ለመመርመር የተነሱ ሁሉ ከሞላ ጎደል ዘርዝረው ለማስቀመጥ ይሞክራሉ። ከነዚህ የዘርፉ ባለሙያዎች መካከል ሰለሞን ተሾመ በስነ-ቃል ስር መጠቃለል ያለባቸውን ጉዳዮች በሚገባ ዘርዝሮ እንደሚከተለው አቀርቧቸዋል።

*ሥነ-ቃል* በርካታ ቅርንጫፎች *ያሉት* ሲሆን እንደ ዘሪሁን (1997) *ሀተታ* የ*ሥነ-ቃል* ምድቦች “ተረት፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ *ፈሊጦች*፣ እንቆቅልሽ፣ እንካሰላንትያ፣ *አፈ-ታሪክ*፣ ምርቃን፣ እርግማን፣ ፉከራና፣ ቀረርቶ፣ የሙሾ፣ የቡሄና የእንቁጣጣሽ ግጥሞች፣ የአካባቢ *ሥያሜዎች*፣ ቀልዶች፣የቃል ግጥሞች(የሕጻናት ጨዋታ ግጥሞች)፣ የልመና ግጥሞች፣ (የብሶት *መግለጫ* ግጥሞች)፣ (የሙገሳ ግጥሞች)፣ ስለሰው፣ እንስሳና ተፈጥሮ አፈጣጠርና ባህርይ የሚገልጹ *ሀተታ* ተፈጥሮዎች ወዘተ“ ይካተታሉ።

*ሥነ-ቃል* የማህበረሰቡ አባል በሆነ/ች በአካል ተለይቶ/ታ በማይታወቅ/በማትታወቅ ግለሰብ ተፈጥሮ በልዩ ልዩ *አጋጣሚዎች* እየተሳበ ለማህበረሰቡ በማህበረሰቡ በቃል *መሳሪያነት* የሚቀርብ *ታላቅ* ጉልበት *ያለው* ቃላዊ *ሥነ-ጽሑፍ* ነው። ዘሪሁን የ*ሥነ-ጽፍ* መሰረታውያን በሚለው *መጽሐፋቸው* *ሥነ-ቃልን* በተመለከተ ሲያብራሩ “*ሥነ-ቃል* በመነገር፣በመተረት፣ ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ *አጋጣሚዎች* ላይ የሚከወን *ቃላዊ* ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ እንዲሁም *ታሪክ* ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን *መግለጫ* ኪነ-ጥበብ ነው። ”/ዘሪሁን፤2007፣20/ ብለዋል።

በሌላ በኩል በ*ሥነ-ቃል* ማህበረሰቡ በረጅም የህይወት ውጣውረድ ዘመኑ እየፈጠረ ሲጠቀምበት የነበረ፤እየተገለገለበትም *ያለ*፤ለወደፊቱም ሲጠቀምበት የሚኖር አንጡራ ሀብቱ ነው፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱት ሎሮች ጠንካራ ፉክክርና አካላዊ መስተጋብር የማይጠይቁ

ሲሆኑ በአብዛኛው የልጆችንም ሆነ የአዋቂዎችን የንግግር ክህሎት፣ የማስተዋልና የማሰላሰል አቅም የሚያጎለብቱ ሲሆኑ ከፍሲል እንደተመለከትነው መዝሙሮች፣ተረቶች፣ እንቆቅልሾች፣ እንካሰላንትያ፣ ቀልዶች፣ የተለያዩ ማንጓጠጦችን የሚጠቀልል እንደሆነ የElizabeth (2008) መረጃ ያስገነዝባል፡፡

እነዚህን ልዩልዩ ሎሮች ተተኳሪ በማድረግም የስነ-ልሳንና የፎክሎር ተመራማሪዎች በርካታ ጥናቶችን ሲያካሂዱ ይስተዋላል፡፡ ከእነሱም በተጨማሪ የሳይኮሎጂና የአንትሮፖሎጂ የጥናት መስኮችን ትኩረትንም ያገኙ ናቸው፡፡ እነዚህን ቃላዊ ሎሮች በምናጠናበት ጊዜም እንዴት ይከወናሉ?፣ ማን ይከውናቸዋል?፣ ምን ህገ-ደንብ አላቸው?፣ መቼ ይከወናሉ? ለምን ይከወናሉ?፣ ስለማህበረሰቡ ምን ይነግሩናል?፣ወዘተ የሚሉት ተተኳሪ ነጥቦች ሲሆኑ እንደሚገባ ከላይ በዝርዝር የቀረቡት መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

## 2.2.2. ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት /performing folk arts/

ይህ የፎክሎር ዘውግ አንዱን ከአንዱ ለመነጠል አስቸጋሪ የሆኑትን ሀገረሰባዊ ሙዚቃን /folk music/፣ሀገረሰባዊ ዳንስን/folk dance/ እና ሀገረሰባዊ ድራማን/folk drama/ አጠቃሎ የሚይዝ ነው፡፡አንዱ ለሌላው የላቀ ፋይዳ አለው፡፡አንዱ ደምቆ ለመታየት የሌላውን መኖር ይፈልጋል፡፡

ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ሀገር በቀል በሆኑ የምት፣የክር፣የትንፋሽ፣ወዘተ. መሳሪያዎች ታጅቦ ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት የሚፈጠር ስሜት ኮርኳሪ የሙዚቃ አይነት ሲሆን፤ ሀገረሰባዊ ዳንስ ደግሞ በሀገረሰባዊ ሙዚቃ አጃቢነት የሚቀርብ ዳንኪራ፣ጭፈራ፣ እስክስታ፣ ወዘተ፣ ነው፡፡ ሀገረሰባዊ ድራማ የምንለው የማህበረሰቡን ልዩልዩ መልኮች ለመሰሎቻቸው ለማሳየት ወይም ልዩ ልዩ ስሜቶቻቸውን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ጥበብ ነው፡፡እነዚህ በተለያዩ አነሳሽ ምክንያቶች የሚከወኑ ጥበባዊ ጉዳዮች ሲከወኑ አስፈላጊ መጊያጌያጥ /መዋብ/፣ መኳኳል፣ድባቡ የሚፈቅደውን ልብስ መልበስ፣ከሁነቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ቁሳቁሶችን መጠቀም ሊፈልግ ይችላል፡፡ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን በተመለከተ ፈቃደ እንደ ሚከተለው ያብራራል፡፡

*"የሀገርሰብ ልብስ ተለብሶ፣ በሀገረሰብ ሙዚቃ መሳሪያዎች ታጅቦ፣ አስፈላጊው መጊያጌጥ ከተከወነ በኋላ እንደ ሀገረሰቡ ልማድ አስፈላጊው ዝግጅት በሙሉ ከተደረገ በኋላ የሚከወነውን ነው ሙያው የሚያጠናው፡፡ ሙዚቃ፣ ዳንስ እና ድራማ ብቻቸውን የቆሙ*

አይደሉም። በተግባር ጊዜ አንዱ በአንዱ ውስጥ ይኖራል። አንዱ ያለሌላው የማይኖርበትም ጊዜ አለ።"/ፈ.ቃደ፤1991፣12/

## 2.2.3 ሀገረሰባዊ ልማድ /Social folk customs/

ሀገረሰባዊ ልማድ የሚባለው የአንድ ማህበረሰብ የጋራ ይዞታ የሆነ ነባርና ቋሚ ዘልማዳዊ የአኗኗር መንገድ ነው። ነባር ሲባልም የቆዩ (የጥንት) ፤ቋሚ ሲባል ዘላቂ ሊጠፉ የማይችሉ ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ የተወሰኑ ቡድኖች ወይም የማሕበረሰብ አባላት የወል የኑሮ ዘይቤ ነው።

የሀገረሳባዊ ልማዶችን በተመለከተ እንደ ሰለሞን(2007) ገለጻ ሃገረሰባዊ ልማድ ማህበ ረሰቡ በተደጋጋሚ የሚከውናቸው ድርጊትና ቅደም ተከተላዊ ሥርዓትን መሰረት በማድ ረግ የሚቀርቡ ጥበቦች ጥቅል መጠሪያ ነው።"በሀገረሰባዊ ልማዶች ሰዎች አጥብቀው የያዝዋቸው እምነቶችና ልማዶች መነሻ ምንጫቸው ምንድን ነው? የተወሰኑ ሥርዓቶ ችንና እምነቶችን ስለምን ይከተላሉ? እና የመሳሰሉት ጥያቄዎችን በተለይ ፈላስፎች፣ደራስያን፣ ስነ-ሰባውያን፣ ፎክሎረኞች ጊዜ ወስደው የተመራመሩባቸውና ዛሬም የሚመራ መሩባቸው ጥያቄዎች ናቸው" ፈ.ቃደ (1991፣13) ።

ከቀረበው ሐሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው ሀገረሰባዊ ልማዶች ሰዎች በዘመናቸው አጥብቀው የያዟቸው አመለካከቶች ናቸው ማለት ይቻላል።ሀገረሰባዊ ልማዶች የአንድ ሕዝብ የባህልና የእምነት መገለጫዎች ናቸው።ልማዳዊ ሕጎች፣ማህረሰባዊ ሥርዓት እንዳይናጋ ተባብሮ መኖር እንዲሰፍን፣ዘላቂ ሰላም እንዲኖር፣ወዘተ የሚጫወቱት ሚና ከፍያለ ነው፡፡የሀገ ረሰባዊ ልማድ እንደ ወግ ማዕረግ (የሕይወት ሽግግር)፣ሐገረሰባዊ እምነቶችና አምልኮ ዎች፣ሀገረሰባዊ መድሃኒቶች፣ሃገረሰባዊ ሃይማኖቶች ባህላዊ መዝናኛዎች፣ጨዋታዎችና ሀገረሰባዊ ስያሜዎችንም ይጨምራል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት አራቱ በሀገረሰባዊ ልማድ ስር የሚጠቃለሉት ርዕሰ ጉዳዮች የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር በግሉ ወይም ከሌሎች ከመሰሎቹ ጋር በቡድን የሚከውናቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ባህላዊ፣ወዘተ ጉዳዮች/ድርጊቶች/ ናቸው። አንድ ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ከቀደሙት መሰሎቹ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች በሚኖረው መቀራረብ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወርሶ እየተገለገለባቸው ያሉትን ዕምነቶች፣ሀገርበቀል መድኃኒቶች፣ተዝናኖትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች፣ልዩ ልዩ ከበራዎች፣ወዘተ.ሁሉ አጠቃሎ የሚይዝ ሰፊ የፎክሎር ዘውግ ነው።

### 2.2.4. ቁሳዊ ባህል /Material culture/

ቁሳዊ ባህል አንዱ የባህል መገለጫ የሆነ የፎክሎር ዘርፍ ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ የሚካተቱት በዓይን የሚታዩ፣ በእጅ የሚዳሰሱና በምላስ የሚቀመሱ ተጨባጭ የባህል አይነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ባህላዊ ቁሶች የማህበረሰቡን ፍልስፍና ታሪክ፣ እምነት ሃይማኖት፣ ባህል፣ ወዘተ መሰረት በማድረግ የማህበረሰብን የዘመን አሻራዎች የሚያሳዩ የጥበብ ውጤቶች ናቸው፡፡ ቁሳዊ ባህል ሀገረሰባዊ እጅ ሥራን /folk crafts/፣ሀገረሰባዊ ስዕልን /folk art/፣ሀገረሰባዊ ምህንድስናን /architecture/፣ሀገረሰባዊ ልብስ /folk costume/ እና ሀገረሰባዊ የምግብ አሠራርን /folkcookery/እንደሚያጠቃልል ዶርሰንን በመጥቀስ ፈቃደ/1991፣15/ ያብራራል፡፡

ጠቅለል ባለ ሁኔታ ሲታይ ከላይ የተዘረሰሩት በዶርሰን የተከፋፈሉት አራቱ የፎክሎር ዘውጎች ብቻቸውን የቆሙ የጥናት መስኮች ሳይሆኑ በመሃላቸው ሰፊ ግንኙነት ወይም ተደጋጋፊነት ያላቸው መሆኑ ልብ ይሏል፡፡

## 2.3. ተግባራዊ ፎክሎር

ለዚህ ጥናት አጥኚው ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን የሚጠቀም ይሆናል፡፡ የንድፈ ሀሳቡ ማእከላዊ ሀሳብ አንድ ማህበረሰብ የሚገነባባቸውን ልዩ ልዩ ተቋማት እንደ ግብዓት በመውሰድ ማህበረሰባቸውን በአዎንታዊነት ለመገንባት ያላቸውን ሙያ ወይም ተግባር ማጥናት ነው፡፡ የአንድ ማህበረሰብ ቃላዊም ሆነ ቁሳዊ ባህል መጠናትና መመርመር ያለበት ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ መሰረት በማድረግ ነው (Sims,2005:174)፡፡በመሆኑም በዋናነት የቀረቡትን ፎክሎራዊ ዘውጎች ለምን አገልግሎት ያውላቸዋል? በቀረቡት ፕሮግራሞች ለማህበረሰቡ የህይወት እንቅስቃሴ እና ማህበረሰቡ ለሚመራበት ስርዓት ዘገባዎቹ ምን አገልግሎት አላቸው? በተጨማሪም ዘገባዎቹ የሰዎችን አጠቃላይ የአኗኗር ሁኔታ ከመቃኘት አንፃር ምን ይመሳላል? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ስለሆነ ነው፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ፎክሎርን ለማጥናት ከሚያገለግሉት መስኮች አንዱ መሆኑን Dorson (1972) ያስረዳሉ፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ቃላዊ፣ልማዳዊና ቁሳዊ ፎክሎሮችን ለማህበሩ ምን እና እንዴት ይጠቅማሉ የሚለውን ለማጥናት ያስችላል፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን ከሰው ልጅ አካል ጋር አቆራኝቶ ያየዋል፡፡ በሰው ልጅ አካል ውስጥ አጥንቶች፣

ጡንቻዎች እና ሌሎች ክፍሎች በተናጥል ሳይሆን በጋራ የሰውን ልጅ እንደሚያኖሩት ሁሉ፤ የተለያዩ ማህበራዊ ክፍሎች በጋራ በመሆን ትክክለኛውን ማህበረሰብ ይፈጥራሉ። የተግባራዊ ትወራ Functional Approach ምልከታው በተናጠል ያለ ማህበራዊ መዋቅሮች ለትክክለኛ ማህበረሰብ መገንባት ያላቸውን ጥቅም ማጥናት ነው።

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ እንደ ቤተሰብ፣የእምነት ተቋማት፣የፍትህ ተቋማት፣ ማህበራዊ ተቋማት በመቀናጀት አዎንታዊ ጥቅም ያለውን ማህበረሰብ ይፈጥራሉ። ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ይህንን አዎንታዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር ተቋማቱ ያላቸውን ጥቅም ይመረምራሉ። ይህ አይነቱ ንድፈ ሀሳብ የጋራ ድክመቶች አሉት። ሰለሞን (2007፣76)። የተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ከማህበራዊ መዋቅር ጋር ያለውን ዝምድና በፎክሎር ባለሙያዎች ትንተና መሠረት ሲያስረዱ ማህበራዊ መዋቅሮች ባላቸው ጠቀሜታና ሚና ላይ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑን ይገልፃሉ።ፈቃደ(1992፣17)እንደገለፁት እ.ኤ.አ በ1930ዎቹ ዓመታት፣ የብሪታንያ የሥነ-ሰብእ ምሁራን የአፍሪካ ሥነ-ቃል ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ እንሰበስባለን ብለው ጀመሩ።የእነሱ የአስተሳሰብ ፈለግ"መዋቅራዊ ተግባራዊ"(Structural Functionalism) ይባላል። የዚህ ፈለግ ዋና ዓላማ በየጊዜው ያሉትን ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ሁኔታዎች ማጥናት ነው።

ፎክሎር ይህንን ንድፈ ሀሳብ ወደ ራሱ ሲያመጣው በተወሰነ ደረጃ ለራሱ እንዲስማማ አድርጎታል። በፎክሎር ጥናት ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በፎክሎሩ ይዘት በፎክሎሩ ባለቤት አጠቃቀም እና በሚሰጠው ትርጉም ላይ ተመሥርቶ ፎክሎሩን ለመተንተን የሚያስችል ግኝት የሚያመጣ ንድፈ ሀሳብ አድርጎ ነው። ሰለሞን(2007፣75) ይህ ንድፈ ሀሳብ ለፎክሎር ጥናት ባለሙያው የሚሰጠውን ግልጋሎት አስመልክቶ የጠቀሜታዊነት ንድፈ ሀሳብ አንድ ማህበረሰብ ወይም የፎክ ቡድን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለማህበረሰቡ ወይም ለፎክ ቡድኑ የሚሰጡት ጠቀሜታና በቡድኑ ውስጥ ያላቸው አውዲዊ ትርጓሜን በማሳየት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው። የዚህ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች ተረቶች፣ሚቶች ምሣሌያዊ አነጋገሮች እምነቶችና ሌሎችም ሎሮች ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ስነ-ልቦናዊ ወይም ሌላ ጥቅም መስጠትና የማህበረሰቡን ፍላጎት ማሟላት ይኖርባቸዋል የሚል አስተሳሰብ የሚያራምዱ ሲሆን ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ ምን አይነት ትርጓሜና ጠቀሜታ አለው? የሚለው አብይ ጥያቄያቸው ነው። በማለት ይገልፃሉ።

የአንድ ማህበረሰብ ፎክሎሮች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ስርዓቶች፣ህይወት የሚመራበትን መንገድ፣መልካም ስነ-ምግባራትን ያስተምራሉ።ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፈቃደ (1991፣20)

"ስነ-ቃሎች የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ የአለባበስ፣ የአቀማመጥ፣ የአነጋገር፣ የአካሄድ ሥርዓትን ያሳውቃሉ። በህይወት ውስጥ የትጋትን፣ የለጋስነትን፣ የህብረትን ጥቅም አጥብቀው ይሰብካሉ" በማለት ከፎክሎር ተግባራት አንዱ ማስተማር እንደሆነ ይገልፃሉ።

ሁለተኛው የፎክሎር ተግባር የማምለጫ ተግባር ነው። ፎክሎር ከተወሰኑብን እና በባህል ምክንያት ከታገድንባቸው ሥርዓቶች ማምለጫ ነው። ፎክሎር ከአሰልቺና ከተደጋጋሚ የህይወት ክስተቶች እንድናመልጥ ያደርገናል ። ፈቃደ (1991፣20) በመሆኑም የሰው ልጅ በፎክሎር በዙሪያው ከሚገኙ የማያስደስቱ እና ነፃነት ከሚነፍጉ ጉዳዮች በማምለጥ በውስጡ የራሱን የደስታና የነፃነት ዓለም ለመፍጠር ይጠቀምበታል።

ሶስተኛው የፍክሎር ተግባር የመትከል ወይም የመቆጣጠር ተግባር ነው። ፎክሎር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ቅቡል የሆኑ ባህሪያትን የመትከል ወይም የመቆጣጠር ተግባር አለው። ባህል በተደጋጋሚ ጊዜ አንድን ሰው ወደ ተረጋገጠ የባህርይ መስመር ይወስዳል(Sims, 2005፣176)። ይህም ማለት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ መልካም ከሆኑ መርሆች የሚያፈነግጥን ግለሰብ በግሳፄ መመለስ ነው። ፈቃደ (1991፣20)። ስለዚህም ማህበረሰቡ ስህተት ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መርሆች ለማጥፋትና መልካም ናቸው ብሎ ወደሚያምንባቸው መስመሮች ለመመለስና ሰናዮቹንም ለማፅናት በፎክሎር ይገለገላል።

የመጨረሻው የፎክሎር ተግባር የማረጋገጥ ወይም የማፅደቅ ተግባር ነው። ፎክሎር ስርዓትን በማክበር እነዚህ ድርጊቶች በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው በማድረግ ባህልን የማረጋገጥ ተግባር ይፈፅማሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፈቃደ (1991፣18) አድንዳሰፈሩት የቡድኑ አባላት በስነ-ቃል አማካኝነት ከልደት እስከ ሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ ክንዋኔዎቹ እንዳይከስሙና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ። ፎክሎር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወኑ ክዋኔዎችና ተቀባይነት ያላቸው መርሆች ትክክለኛ እና መቀጠል ያለባቸው እንደሆኑ ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ በማቅረብ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማድረግ አቅም አለው።

ፎክሎር ዘርፈ ብዙ በመሆኑ በርካታ ተግባራት አሉት። ቀደምት ተግባራውያን ሀገር በቀል እምነቶች ሁልጊዜ የሚያመለክቱት የማህበረሰቡን እምነት ነው፡ ተረቶች ደግሞ በአድማጭና በነጋሪው ምክንያት ማምለጥን ያመለክቱናል በማለት ጠቅላይ ድምዳሜ ያስቀምጡ ነበር። ሀገር በቀል እምነቶች ሁልጊዜ የሚያመለክቱት እምነትን ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡን የወደፊት ህይወት ለመተንበይ እና የሚመጣውን በማሰብ ጥንቃቄ ለማድረግም ጭምር እንደሆነ እነ Sims (2005: 177) ያስረዳሉ።

የፎክሎር አይነቶች ሲጠቀሱ ከሚጠቀሱት መካከል ተግባራዊ ፎክሎር አንዱ ነው፡፡እንደ https//antroholic.com>applied f…Aug 2023 ተግባራዊ መረጃ ፎክሎር የባህላዊ ማህበረሰብ መገልገያ ንኡስ ክፍል (Sub Set) ነው፡፡

ተግባራዊ ፎክሎር በዘመናዊ ማህበረሰብ ውስጥ የጥንታዊ ዕውቀትን ሚና እና ተግባር ተደራሽ የሚያደርግበትን ዘውግ ነው፡፡ ይህ ክፍል የፎክሎርን ተግባራዊ ክንውኖች በማቀናጀት ባህልን በማጠናከር ማስቀጠል ባህላዊ ማንነትን ጠብቆ ማሳደግና ማህበራዊ ዕድገትን ከፍ የማድረግ ሚና አለው ፡፡ለአብነትም ፦

1. ጥንታዊ ዕውቀት፣ታሪክ፣ሙዚቃ፣ልምዶችና ተሞክሮዎች ወዘተ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሸጋገሩበታል፡፡
2. የተወሰኑ የጋራ ጉዳዮችን የሚጋሩ ቡድኖች ለአብነትም ዜግነት፣ዘር ጎሳ፣ሙያ ወይም የጋራ ልምድ ያላቸው ሰዎችን ይመለከታል፡፡

### 2.3.1. የተግባራዊ ፎክሎር ዘዴ ወይም አሰራር

ከላይ የተጠቀሰው የድህረ ገጽ መረጃ እንደሚያመላክተው ተግባራዊ ፎክሎር የሚከተሉትን የአሰራር ዘዴዎች የሚከተል ነው፡፡እነዚህም ፦

ሀ.የመስክ ሥራ፦የመስክ ስራ በፎክሎር የጥናት መስክ ወሳኝና በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡

ለ.ጆግራፊ (ethnography) ፦ የሰው ልጅ ባህል ሳይንሳዊ ጥናት ነው፡፡ስለአንድ የተወሰነ ማህበረሰብ ዝርዝር የማንነት መረጃ በተቀዳሚነት የሚሰጥ ነው፡፡

ሐ.ቃለ-መጠይቅ፦ በቀረጻ ላይ በተመሰረተ መጠይቅ አማካኝነት ታሪካዊ መረጃዎችን የማሰባሰብ ሂደትን ለመተግበር ይረዳል፡፡

### 2.3.2. የተግባራዊ ፎክሎር ትግበራዊ አፈጻጸም

ከላይ በተገለጸው የድህረገጽ መረጃ ምንጭነት ሲታይ ተግባራዊ ፎክሎር የሚከተሉትን ትግበራዎች ለማከናወን ያገለግላል፡፡

1.ባህልን ለማቆየት ፦

ተግባራዊ ፎክሎር የባህልን ተወራራሽነት በማስቀጠል በተለይም በሐገር በቀል ማህበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያለው ስለመሆኑ ተከታዮቹ ማሳያዎች አመላካች ናቸው፡፡እነዚህም ፦

❖ ጥንታዊ ዕውቀቶችን ልምዶችን አስተሳሰብና እምነቶችን ይሰንዳል፡፡

❖ ልዩልዩ ባህላዊ እሴቶችን ለአዲሱ ትውልድ የማስተላፍ ሚናን ይጫወታል፡፡

❖ ባህላዊ ልማዶችን ጠብቀው ያቆዩ ዘንድ ማህበረሰቦችን ያበረታታል፡፡

2. ከትምህርት አንጻር

ይህ ዘውግ ፎክርን ከሥርአተ ትመህርት ጋር በማቀናጀት ትምህርትን ያሳድጋል፡፡ይህ ዘዴ ወይም አሰራር ብዝሃ ባህልን ያከብራል፣የባህል ሽግግርን ያጠናክራል፣ እንዲሁም ዓለማቀፋዊ ግንኙነትን ያሳድጋል ፡፡

3. በጤንነት ዘርፍ ፦ ተግባራዊ ፎክሎር ህሙማን ስለበሽታውና እንዲሁም ስለመዳን ያላቸውን አስተሳሰብና እምነት በመረዳትና በመርዳት ሂደት ተግባቦትን የማሻሻል ሚና አለው፡፡

## 2.4. የፎክሎርና የመገናኛ ብዙኃን ጥናት ትስስር

ፎክሎርና መገናኛ ብዙሃን የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ስለመሆኑ በመስኩ ጥናትና ምርምር ያካሄዱ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ ከ(1960)ዎቹ ጀምሮ በሁለቱ መካል ስላለው ግንኙነት የተለያዩ የምርምር ስራዎች ሲከናወኑ የቆዩ ስለመሆኑ Joyce (2014) ያሰፈሩት መረጃ ያስገነዝባል፡፡ እንደኚህ ምሁር መረጃ ፎክሎርና መገናኛ ብዙሃን አንዱ ሌላውን በማጠንከርና በማጎልበት ትስሰራቸውን አሳድገው የመጡ ስለመሆናቸው አስረግጦ መናገር ይቻላል፡፡ ለዚህም ጉዳይ አስረጅ ናቸው ያሏቸውን የተወሰኑ የምርምር ስራዎችን ለመጠቆም ሞክረዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል Degh (1994) በአሜሪካ መገናኛ ብዙሃን ውስጥ የፎክሎር ጥንተ ነገሮች በመገናኛ ብዙኃን ገጽታዎች በሚል ርዕስ፣ Boesinger (1990) ደግሞ "በመገናኛ ብዙኀን አማካኝነት የፎክሎር ተላልፎ በኢንዱስትሪያዊ አውዶች ውስጥ በሚል ርዕስ፣ሚቲዎሎጅና ጥንታዊ ስነ-ጽሑፍ በሲኒማና በቴሌቭዥን የሚል ጥናትና እንዲሁም ቃላዊ ስነ-ጽሁፍ በህንድ ሲኒማ ርእዮት" በሚል ርዕስ የቀረቡት ጥናትና ምርምሮች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ መረጃዎች በቀጥታም ይባል በተዘዋዋሪ የፎክሎርንና የመገናኛ ብዙኀንን ትስስር የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ጥናቶቹ እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ ስራዎችን ናሙና የሚወክሉ ፎክሎሪስቶች እንዴት በፎክሎርና በመገናኛ ብዙሃን መካከል ያለውን ግንኙነት ከተለያዩ አመለካከቶች አንጻር ለማስረዳትና በተለያዩ ዘዴዎችና ቁሳቁሶች እየሰሩ መሆናቸውን ያመላክቱ ስራዎች ናቸው፡፡

## 2.5. የፎክሎርና የቴሌቭዥን ጥናት ግንኙነት

ከላይ እንደተመለከተው ፎክሎር ከመገናኛ ብዙኀን ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡ይህውም ከፍሲል በስም የተጠቀሱትን ጥናቶች ጨምሮ ሌሎች መሰል ጥናቶችም እንደሚያስረዱት በፎክሎርና በቴሌቭዥን መካከል በተጨባጭ የሚታይ ግንኙነት አለ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በተለያዩ ጊዜያት የቀረቡ ጥናቶችም የሚያሳዩት ይህንኑ ሁኔታ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ቴሌቭዥንም አንዱ የመገናኛ ብዙኀን ዘውግ እንደመሆኑ መጠን ፎክሎር በቴሌቭዥን ውስጥም የሚጫወተው የራሱ የሆነ ሚና እንዳለው የተለያዩ የሙያው ባለቤቶች ባቀረቧቸው ጽሑፎቻቸው አስረድተዋል፡፡ ይህ ጉዳይ ከዚህ ጥናት ጋርም ቀጥተኛ ግንኙነት ስላለው ቀጥሎ የምንመለከተው የሙያው ጠበብት በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ያቀረቧቸውን ማብራሪያዎችን እና ገለጻዎችን ነው፡፡

እንደ Degh L. (1992) መረጃ በተለይ ቴሌቭዥን፣ በአጠቃላይ ደግሞ መገናኛ ብዙኀን ፎክሎርን በማሰራጨትና ለሰፊው ማሕበረሰብ በማስተዋወቅ ሂደት የጎላ ሚና አለው ፡፡ ይሄውም የፎክሎር ባለቤት የገጠሩ ማህበረሰብ አስኪመስል ድረስ በገጠሩ ዝቅተኛ የማሕበረሰብ ክፍል ባለቤትነት ብቻ ተፈርጆ ይኖር ከነበረበት ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ነጻ በማውጣት ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል የፎክሎር ባለቤት ሆኖ እንዲታይ የማስቻል ሚና ተጫውተዋል ፡፡

ከቀረበው ሐሳብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ እንደምንገነዘበው ልዩ ልዩ የፎክሎር ዘውጎች ማለትም ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ ሀገረሰባዊ ሙዚቃና ውዝዋዜ፣ ሀገረሰባዊ እጅ ስራ፣ ሀገረሳባዊ መዋቢያና ምግብና መጠጥ፤ እንዲሁም እንደ ደቦ፣ ጅጌ፣ ወንፈልና ሌሎችም ፎክሎሮች በተፈጥሯዊ ይዘታቸው ተጠብቀው የሚገኙት በገጠሩ ክፍል /በገጠሩ ማህበረሰብ/ ውስጥ ከመሆኑት ጋር ተያይዞ ፎክሎርን ለዝቅተኛው ማህበረሰብ የመተውና የኋላ ቀርነት መገለጫ አድርጎ እስከ መቁጠር ስርሰዶ የነበረ የተሳሳተ ግንዛቤ ቀስበቀስ እየተቀረፈ መጥቷል፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ ደግሞ እንደ ተባለውም ቴሌቭዥንን ጨምሮ ሌሎች መሰል ሚዲያዎችም ሰፊ ማሕበረሰብን በአጭር ጊዜ ውስጥ ተደራሽ በማድረግ የማስተማርና የማንቃት ሚናን መወጣት ይችላሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ቴሌቭዥንና ፎክሎር ውህደት በመፍጠር ከሚታዩበት አጋጣሚ አንዱ የስነ-ቃል ዘውግ ነው፡፡ በሥነ-ቃል የፎክሎር ዘውግ ውስጥ የሚመደቡ እንደ ምሳሌያዊ ንግግር፣ፈሊጣዊ ንግግር፣ተረት ዕንቆቅልሽ፣አፈታሪክ፣እሰጥ አገባ፣ወግና ጥቅሶች (አባባሎች)

መሰል ሎሮች አሉ። እነዚህን ልዩ ልዩ ሎሮች እንደ አስፈላጊነታቸው በተለያዩ ቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ አካትቶ መገልገል በቀላሉ የማይታይ ጠቀሜታ እንዳላቸው የሙያው ባለቤቶች ያስገነዝባሉ።ተከታዩ ማሳያም ለአብነት የቀረበ ነው።

የተለያዩ አባባሎችን (ጥቅሶችን) በቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ ብንጠቀምባቸው የሚያስገኙልን ጠቀሜታ ስለመኖሩ (Tatira 2001) የሀገራቸውን የዚምባብዌን ገጠመኝ በማውሳት ለማስረዳት ሞክረዋል። በማስታወቂያ ስራ ውስጥ አባባሎችን በተከታታይነት መገልገል የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው በጥናት መረጋገጡን አውስተዋል። እንደኚህ ምሁር ሀተታ የማስታወቂያ ስራን ከእውነተኛው የሕይወት ተሞክሮ በታቀዱ አባባሎች (Proverves) አጅቦ ማቅረብ በአድማጭ ተመልካች ዘንድ የተሻለ ተደማጭነትንና ተመራጭነትን ለማግኘት ይረዳል።

ፎክሎርን ከማስታወቂያ ስራ ጋር በማስተሳሰር ጠቀሜታውን ለማስረዳት ከሞከሩ ተመራማሪዎች መካከል Liyanage D. (2013) ይገኙበታል። እንደኚህ ምሁር መረጃ ፎክሎር በማስታወቂያው ዘርፍ ዘወትር ተቀያያሪ የሆነውን የገበያ ፍላጎት በማጣጣምና በማስታወቂያ ወይም በሽያጭ ተግባር ምርትን በማስተዋወቅና ብልጫም እንዳለው በመስበክ ሂደት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ያስረዳሉ። አክለውም በማስታወቂያ (Advertisment) ስራ ፎክሎራዊ ማስታወቂያዎች ብልጫ ያላቸውና ተመራጭ የሆኑ እንደሆኑ በጥናት መረጋገጡን ገልጸዋል። የፎክሎር ማስታወቂያዎች ሁለት ገጽታን የተላበሰ (ቴሌቭዥንና ፎክሎር) ተዝናኖት ስላላቸው የደንበኞችን ቀልብ በመግዛት በመተዋወቅ ላይ ያለን ምርት በቀላሉ ለመሸጥ እንደሚያስችሉ በጥናት የተደረሰበት መሆኑን ገልጸዋል።

በሌላም በኩል Koven J.(2003) በበኩላቸው ከላይ የቀረቡትን ሐሳቦች በሚያጠንክር መልኩ የቴሌቭዥን ጥናቶች አጀማመር ከ1960ዎቹ ጀምሮ የታየ መሆኑን ገልጸው አጀማመሩ ደግሞ ድንገቴ ሳይሆን በወቅቱ የነበሩ ምሁራን በባህላዊ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ ቴሌቭዥን ተጽዕኖ እያሳደረ ነው። በማለት የተጽዕኖውን ደረጃ ለማጥናት ነበር። በወቅቱ የተጀመረው ጥናት ትኩረትም ቴሌቭዥን የባህላዊ አፈታሪኮችን ይዘትና ቅርጽ በሚቀይርባቸው መንገዶች ላይ ነበር። ይሁንና የቴሌቭዥንና የባህላዊ ቅርስ የፎክሎር ጥናትና እንዲሁም የቴሌቭዥን ጥናቶች መዝለቅ የቻሉት ሁለቱ በጋራ የሚገናኙባቸውንና የሚጠኑባቸውን መንገዶች ያመላከተ ሁለገብ የጋራ ጥናቶች እስከ መሆን ደረጃ ድረስ ነበር (Koven 1994)::

በአጠቃላይ ከፍሲል በተከታታይ የቀረቡት መረጃዎች ወይም ገለጻዎች እንደሚያስገነዝቡት ቴሌቭዥንና ፎክሎር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ሁለት የተለያዩ ዘርፎች ቢሆኑም በሁለቱ

ዘርፎች ላይ በተለያዩጊዜያት እና በተለያዩ አጥኚዎች የቀረቡ የጥናትና ምርምር ውጤቶች እንዳመላከቱት ፎክሎር በቴሌቭዥን ውስጥ እንዴት እንደሚወከል፣ቴሌቭዥንም በፎክሎር ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድርና ቴሌቭዥን ፎክሎርን ለመጠበቅና ለማስተዋወቅም ፋይዳ አለው፡፡ በተለይም ፎክሎርን በቴሌቭዥን ማስታወቂያዎች ማካተት ምርትን በማስተዋወቅና ሽያጭን በማፋጠን በአጭሩ ገበያና ገበያተኛን በማገናኘት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ስለመሆኑ የሙያዉ ባለቤቶች ካቀረቡልን መረጃ ብቻም ሳይሆን በማሕበረሰባዊ ዕውቀታችንም የምንገነዘበው እውነታ ነው፡፡

## 2.6. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ንኡስ ክፍል ቀደም ሲል የተጠኑ እና ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው የምርምር ስራዎች ተዳሰው፤ አንድነትና ልዩነት ተብራርቶ የሚቀርብበት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ቀጥሎ በተከታታይ የምንመለከታቸው ቀደምት ጥናቶች በዚሁ አግባብ የተቃኙ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የተቃኘው ጥናት አዳነች "የፎክሎር ቅርጽና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መጻሕፍትና ዜና መዋዕሎች" በሚል ርዕስ በ2001 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት ያቀረበችው ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በአብይ ዓላማነት በተመረጡ የታሪክ መጻሕፍትና ዜና መዋዕሎች ፎክሎር የገባበትን አውድ በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የአዳነች ጥናት በተጨማሪም በታሪክ መጻሕፍትና በዜናመዋእሎች ውስጥ ያለውን አንድነትና ልዩነት በንጽጽር መመልከት፣የፎክሎር አይነቶች በምን አይነት ሁኔታ ሊገቡ እንደቻሉ ማለትም ደራሲው ይሁነኝ ብሎ ያስገባቸው ናቸው ወይስ እንደክስተት የዘገባቸው ናቸው የሚሉ ንዑሳን አላማዎችም አሉት፡፡ ዓላማዎቹን ለማሳካትም በዓላማ ናሙና አማካኝነት አምስት የታሪክ መጻሕፍትንና ሁለት ዜናመዋእሎች መርጣ የፈተሸች ሲሆን የአዳነች ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰልባቸውና የሚለያይባቸውም ነጥቦች አሉ፡፡

ሁለቱም ጥናቶች ፎክሎርነክ መረጃዎችን ይዘው የተገኙ ሰነዶች ከመሆን አኳያ ይመሳሰላሉ፡፡ በተጨማሪም ፎክሎርን ከሌሎች ዘርፎች ጋር በማዛመድ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ከመሞከር አንጻርም ተመሳስሎ አላቸው፡፡ በአንጻሩ ይህ ጥናት የፎክሎር አይነቶችና ፋይዳዎችን ከቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ በማሰስ አውዳቸውን መሰረት ያደረገ ትንተና ያቀረበ ጥናት በመሆኑ ፎክሎርን ከታሪክ መጻሕፍትና ከዜና መዋዕሎች ጋር አስተሳስሮ ትንተና ካቀረበው የአዳነች ጥናት ጋር ሲነጻጸር ልዩነት ይታይበታል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተቃኘው ጥናት ደግሞ ወሰን ባዩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሶስተኛ ዲግሪ (PhD) ማሟያነት ያቀረቡት ጥናት ነው፡፡ ባዩ በ(2010ዓ.ም) "በኢትዮጵያ ቲያትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት" በሚል ርዕስ ያቀረቡት መመረቂያ ጽሑፍ ዋና ዓላማው በኢትዮጵያ ትያትር ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች አስረጅነት ማሳየት ነበር፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካትም ጥናቱ ሌሎች ንኡሳን ዓላማዎችንም ያካተተ ስለመሆኑ በመግቢያው ክፍል የቀረበው ሀተታ ያስረዳል፡፡ እነዚህም የፎክሎራዊ ጉዳዮችን ይዘቶች መግለጽ፣በተውኔቶች ውስጥ የተነሱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ከዘመን አንጻር የሚገልጹትን መልእክት መፈተሽ፣ሥነ-ቃላዊ ጉዳዮች ከቀረበው ተውኔት ጭብጥ ጋር መስተጋብር የፈጠረበትን ሁኔታ በመመርመር ተንትኖ ማቅረብ የሚሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም የፎክሎርን ፋይዳ በተሻለ መልኩ ያሳዩልኛል ያላቸውንና ያመነባቸውን ሰባት ያህል ተውኔቶች በመምረጥ በቃለ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት መረጃዎችን በመሰብሰብ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ የወሰን ጥናት ሥነ-ቃላዊና ሀገረ ሰባዊ ጉዳዮችን በማጥናት ላይ የተገደበ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ከነዚህ በተጨማሪ ለጥናቱ በተለዩት የፋና እና የኢቢኤስ ቴሌቭዥን ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ ሁሉንም የፎክሎር ዘውጎች በመንቀስ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ጭምር በመንቀስ የሚተነትን በመሆኑ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ በሌላ በኩል ሁለቱን ጥናቶች በፎክሎር ትንተና ላይ ያካተቷቸው መረጃዎችና እንዲሁም ፎክሎርን ከፊልም ጋር በማዛመድ ለመተንተን ሞከራቸው ፎክሎር ከሌሎች ዘውጎች ጋር የሚኖረውን መስተጋብር ለማሳየት በመሞከር ረገድ ሁለቱ ጥናቶች የሚመሳሰሉበት ሁኔታም አለ፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የተቃኘው ጥናት ዘይባ (2012 ዓ.ም) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት "የፎክሎር ጉዳዮች ፋይዳ ትንተና በመኤኒትና በእምቢልታ ታሪካዊ ልቦለድ ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ያቀረበቸው ጥናት ነው፡፡ ይህ የመመረቂያ ጽሑፍ ለጥናቱ በተለዩት ልቦለድ መጻሕፍት ውስጥ የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመለየት በትእምርትነት የተገለጹትን ከተተኳሪ ልቦለዶቹ አውድ በመነሳትና በመተርጎም ፎክሎራዊ ጉዳዮቹ ለልቦለዶቹ መሳካት ያበረከቷቸውን ፋይዳዎች በመተንተን ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱ የተከተለው አይነታዊ የምርምር ዘዴን ሲሆን ዓላማ ተኮር የናሙና ስልትንም ተከትሏል፡፡

ጥናቱ በዋናነት ያተኮረው በልቦለዶቹ ውስጥ በተነሱ የስነ-ቃል ምድቦች መካከል ምርቃት፣ እርግማን፣መሃላ፣ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች በሁለቱም ልቦለዶች ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡

ሀገረሰባዊ ልማዶችን በተመለከተም በሁለቱም ልቦዶች ውስጥ ሰፊውን ቦታ የያዙ መሆናቸ ቸውና ክብረበዓላትና ሃገረሰብዓዊ ስያሜዎች መካተታቸው ተጠቅሷል፡፡ቁሳዊ ባህልን በሚመ ለከት ደግሞ ባህላዊ አልባሳቶች፣ጌጣጌጦች፣ሃገረሰባዊ ምግብና መጠጦችና ባህላዊ ቦታዎች በሁለቱም ስራዎች ውስጥ የተገኙ ስለመሆኑ በጥናቱ የትንተና ክፍል ተብራርቷል፡፡ በመጨረሻም የነዚህን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳዎች ለመግለጽ የተሞከረ ሲሆን ይኼውም የገጸባህርያትን ማንነትለማሳየት፣የዘመኑን አጠቃላይ መንፈስ ለማጉላት፣ግጭትን ለማክረር፤ ግጭትን በማብረድ ለአንባቢ እፎይታ ለመስጠት፣እንዲሁም ጭብጥን ለመንገርና ለማጉላት፣ የልቦለዶችን ትልም ለማዋቀር ከፍተኛ ኪናዊ ፋይዳ ያላቸው መሆኑ ተጠቅሷል ፡፡ የዘይባ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰልባቸውም የሚለይባቸውም ነጥቦች አሉ ፡፡

ከተመሳስሏቸው ስንነሳ ሁለቱም ጥናቶች ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የተመለከተ መረጃን ለአንባቢያን የማቅረብ ሚናን የሚወጡ መሆናቸው፤የፎክሎር ዘውጎችን አውዳዊ ፋይዳ የማስረዳት ሚና ስላላቸው የሚመሳሰሉ ሲሆን በአንጻሩ የዘይባ ጥናት የፎክሎርን ፋይዳዎች በፈጠራ ድርሰቶች አንጻር የሚዳስስ መሆኑና ፎክሎርን ከመጻህፍት ጋር አስተሳስሮ የሚገመግም በመሆኑ ፎክሎርን ከቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ጋር በማዛመድ ትንተና ከሚያደርገው ከዚህ ጥናት ጋር ሲነጻጸር ልዩነት ይታይበታል ፡፡

በአራተኛ ደረጃ የተቃኘው ደግሞ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረበ ጥናት ሲሆን ይኼውም "ፎክሎርና መገናኛብዙሃን (Folklore and Mass Media)በሚል ርእስ የቀረበ ነው፡፡ፎክሎር ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ያለውን ትስስር የቃኘው የ( Liyanage 2013) ጥናት የተካሄደው ሲሪላንካ ውስጥ ሲሆን በጥናቱ መግቢያ ክፍል እንደተገለጸው በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ አያሌ ጥናትና ምርምሮች ተካሂደዋል፡፡ በማሳያነት ከተዘረዘሩት መካከልም የDorson (1960)፣ Degh (1994)፣ Dundes (1989)፣ Sullenberg (1974)፣ Newell (1994) ይገኙበታል፡፡ Liyanage አክለው እንደገለጹት እነዚህን ጥናቶችን ጨምሮ ሌሎች መሰል ጥናቶችም በጉዳዩ ላይ ተካሂደዋል፡፡ ምንም እንኳ ጥናቶቹ የየራሳቸው የሆነ የአጠናን ዘዴ፣የናሙና አወሳሰድና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያን ተከትለው ቢካሄዱም በመጨረሻ ላይ የተደረሰበት ውጤት የሚያመለክተው ግን በተመሳሳይ መልኩ ፎክርና መገናኛ ብዙሃን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎችን ያህል የማይነጣጠሉና ትስስር ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ "ፎክሎርና

መገናኛ ብዙሃን“ በሚል የቀረበው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ሲነጻጸር የሚመሳሰልባቸውም የሚለይባቸውም ነጥቦች አሉ፡፡ ልዩነታቸውን በተመለከተ የሚነሱ ነጥቦችን ስንመለከት ይህ ጥናት ከመገናኛ ብዙኃን አይነቶች አንዱ በሆነው በቴሌቭዥን ላይ በማተኮር በ2012 በፋና እና በኢቢኤስ የቴሌቭዥን ሳምንታዊ ፕሮግራሞች የተካተቱ ፎሎራዊ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በማሳየትና ጠቀሜታቸውን በመተንተን ላይ ያተኮረው ከዚህ ጥናት ጋር ሲነጻጸር ልዩነት ይታይበታል፡፡ በአንጻሩ ሁለቱም ጥናቶች ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ መረጃዎችን አካትተው የሚገኙ ሰነዶች ከመሆን አንጻርና እንዲሁም ፎክሎርን ከሚዲያ ጋር አስተሳስሮ ትንታኔ ከመስጠት አንጻር ተመሳሳይነትም አላቸው፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ

### 3.1.የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት በአይነቱ ዓይነታዊ መረጃዎችን የሚጠቀም በመሆኑ ገላጭ የምርምር ንድፍን በመከተል ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ በዚህ ዘዴ ላይ በመመርኮዝም ለጥናቱ የሚያስፈልገው መረጃ የተሰበሰበበትን መንገድና መረጃው የተተነተነበትን ዘዴ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ ቀደም ሲል በመግቢያው ክፍል ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2012 ዓ.ም በፋና ቴሌቪዥን፣ በጉዞ ኢትዮጵያ ፕሮግራም እና በኢቢኤስ ቴሌቪዥን፣ ኢትዮጵያን እንወቅ ፕሮግራም ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የዳሰሱ ዝግጅቶች ላይ ትንታኔ ማቅረብ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግም አይነታዊ የምርምር ዘዴ ተመርጧል፡፡ አይነታዊ ምርምር እንደ ያለው (2004፣20) ገለጻ ተመራማሪው ለማጥናት የፈለገው ጉዳይ በመጠን ሳይሆንና በአይነት የሚገለጽ ሳይሆን መረጃዎችን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ለአንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለጻዊ ዘዴን ተጠቅሞ እንጅ በእስታስቲክሳዊ ዘዴ ተጠቅሞ አይደለም፡፡ ይህ ጥናትም አሃዛዊ መረጃን ስለማይመለከት አይነታዊ የምርምር ዘዴን እንዲከተል ተደርጓል፡፡ በአጭሩ አጥኚው ይህንን የምርምር ንድፍ የመረጠበት ምክንያት ይዞት የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ በ2012 ዓ.ም በፋና ቴሌቪዥን "ጉዞ ኢትዮጵያ" ፕሮግራም እና በኢቢኤስ ቴሌቪዥን "ኢትዮጵያን እንወቅ" ፕሮግራም ላይ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በዘገቡ ፕሮግራሞች ላይ የተካተቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ፣ ድግግሞሻቸው ምን መልክ እንዳለውና የፎክሎራዊ ጉዳዮችን አውድ ለመተንተንተን የገለጻ እና የትረካ ስልት ተመራጭ በመሆኑ ነው፡፡

### 3.2. የመረጃ ምንጭ

የዚህን ጥናት ዋና ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ አጥኚው ለጥናቱ ተገቢ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ እነዚህም በ(2012 ዓ.ም) በፋና "ጉዞ ኢትዮጵያ" እና በኢቢኤስ "ኢትዮጵያን እንወቅ" የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ የቀረቡት ፊልሞችና ቪዲዮዎች ናቸው፡፡ ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ ትንተናውን ለማካሄድ ፊልሞችና ቪዲዮዎች የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል፡፡ በነዚህ ሁለት የቴሌብዥን ጣቢያዎች በቀጠሮቀን በተደጋጋሚ በመገኘት ዘጋቢዎችን (የፕሮግራሙ አቅራቢ ጋዜጠኞችን) በማናገር መረጃ ለማግኘት ተሞሯል፣ተደማጭ ቪዲዎችንና እንዲሁም ፊልሞችን፣በዘገባ ወቅት በካሜራ የተቀረጹ

ድምጾችንና እንዲሁም ፎቶግራፎችን፣ማስታዎሻዎችን በመጠየቅና በማስቀረብ የመረጃ ፍተሻ ማለትም የሰነድ ፍተሻ፣የቪደዮ ፍተሻና እንዲሁም ምልከታ ተካሂዷል ። በአጭሩ ለዚህ ጥናት አብይ የመረጃ ምንጮች የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮች ናቸው። ያለው (2004፣32) Wersma(1996)ን በዋቢነት ጠቅሰው እንዳስረዱት የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ሲባል ጉዳዩ ሲከሰት ወይም ሁነቱ ሲሆንና ሲከወን የተመለከቱ ወይም የሰሙ ሰዎች ወይም እነዚህ ሰዎች የጻፏቸው መጻሕፍት፣ጋዜጦች፣መጣጥፎችና የተለያዩ ሰነዶች እንዲሁም ቅሪተ አካሎች፣ነባር ቅርሶች፣በቴፕ ወይም በቪዲዮ ካሜራ የተቀረጹና በፎቶጋራፍ የተነሱ አሊያም በሌላ መልኩ የተዘጋጁ ነገሮችን ሁሉ ያካትታል። በመሆኑም የመረጃ ምንጮቹ በ(2012 ዓ.ም) በፋና "ጉዞ ኢትዮጵያ* እና በኢቢኤስ "ኢትዮጵያን እንወቅ* የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ የቀረቡት ፊልሞችና ቪዲዮዎች ናቸው። ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ ትንተናውን ለማካሄድ ፊልሞችና ቪዲዮዎች የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል።

## 3.3. የናሙና አመራረጥ ስልት

### 3.3.1. የቴሌቭዥን ጣቢያዎች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተለዩት የቴሌቭዝን ጣቢያዎች "ፋና" ቴሌቭዥንና "ኢቢኤስ" ቴሌቭዥን ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት ከፍ ሲል እንደ ተጠቀሰው በዓላማ ተኮር ናሙና ነው። ይኼውም ሁለቱም ጣቢያዎች ተቀራራቢ ሳምንታዊ ፕሮግራሞችን ማለትም ጉዞ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያን እንወቅ ፕሮግራሞች የሚያሰራጩ መሆናቸው፣የቴሌቭዥን ጣቢያዎቹ ባለቤትነት አንድ ከግል(ኢቢኤስ) አንድ ከመንግስት(ፋና) መሆናቸው እንዲሁም ቀላል የማይባል ቁጥር ያለው አድማጭና ተመልካች ያላቸው እንደ መሆኑ መጠን በእነዚህ ጣቢያዎች ምን ያህል ህዝባዊ ባህል ወይም የሕዝብ ሃብት የሆነው ፎክሎር በውህደት እንደሚሰራጭ ለመመርመር በማሰብና በተጨማሪም የጥናቱ አቅራቢ በስራ ምክንያት ሁለቱን ድርጅቶች በቅርብ የመመልከት እድል አጋጥሞት የነበረ በመሆኑ መረጃን በመሰብሰብ ሂደቱ ጫናን ከመቀነስ አኳያ ጠቀሜታ ይኖረዋል በሚል መነሻ እነዚህን ድርጅቶች በተጠኝነት መርጧል።

### 3.3.2. ለጥናቱ የተለዩ ፕሮግራሞች አመራረጥ

ይህ ጥናት ዓላማ ተኮር ናሙናን የተከተለ ስለመሆኑ ከፍ ሲል ተጠቁሟል። በመሆኑም የጥናቱ ትኩረት ዓላማን መሰረት ባደረገ ሁኔታ በ2012 ዓ.ም በፋና ቴሌቭዥን በጉዞ ኢትዮጵያ እና በኢቢኤስ ቴሌቭዥን ኢትዮጵያን እንወቅ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ

በቀረቡት ፊልሞች ላይ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዓላማ ተኮር ዘዴ ተመራማሪው ተጠኚውን የሚመርጠው ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ነው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ በተለየው ጊዜ (2012 ዓ.ም) የቀረቡትን የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ለመውሰድ ተሞክሯል፡፡ ምክንያቱም የመስኩ ምሁራን ለአብነትም ያለው (2004፣136) እንደሚገልጹት "ተጠኝዎቼ የምፈልገው መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ?" በማለት አጥኚው ራሱን በመጠየቅ ምርጫ ማድረግ ስለሚችል የዚህ ጥናት አቅራቢም "ከየትኞቹ ፕሮግራሞች ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመዳሰስ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ?" በሚል መነሻ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ የቴሌቭዥን ጣቢያዎችን ሊመርጥ ችሏል፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ በ2012 ዓ.ም በፋና ጉዞ ኢትዮጵያ እና በኢቢኤስ ኢትዮጵያን እንወቅ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ የቀረቡት ፊልሞች ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት አይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተደርጎ የተመረጠው ቪዲዮ ፍተሻ ነው፡፡ ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመጠቀም በ 2012 ዓ.ም በፋና "ጉዞ ኢትዮጵያ" እና በኢቢኤስ "ኢትዮጵያን እንወቅ"የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ የቀረቡ የፊልም አስክሪፕቶችንና ቪዲዮችን ፈትሿል ፡፡ እንዲሁም ምልከታም በአጭሩ ሰነድ ፍተሻ አይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል ፡፡ በተጨማሪም በመረጃ ማጠናከሪያነት ምልከታም አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

### 3.4.1 ቪዲዮ ፍተሻ

በዚህ ጥናት በ2012 ዓ.ም በፋና ጉዞ ኢትዮጵያ እና በኢቢኤስ ኢትዮጵያን እንወቅ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ የቀረቡት ፊልሞችን በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ በመሆኑም በሰነድ ፍተሻ አማካኝነት የመረጃ አሰባሰቡ ሂደት ምን እንደሚመስል ተከታዩ ማብራሪያና ገለጻ በውል ያስገነዝባል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2012 ዓ.ም በፋና ጉዞ ኢትዮጵያ እና በኢቢኤስ ኢትዮጵያን እንወቅ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ የቀረቡት ፊልሞችን ከፎክሎር ዘውጎች ጋር ያላቸውን ዝምድና እና ልዩነት ከይዘት አንፃር በንፅፅር መፈተሸ ነው፡፡ በመሆኑም በእያንዳንዱ የቴሌቪዥን ጣቢያ የቀረቡ የፕሮግራም ፊልሞች ከፎክሎራዊ ጉዳዮች አንፃር የትኛውን የፎክሎር ዘውግ ጥቅም ላይ አውለዋል የሚለውን ለመፈተሸ ያስችል ዘንድ እያንዳንዱ ፊልም በቀረበበት የጊዜ ርዝማኔ ምን ምን ጉዳዮችን ዳሷል? የሚለውን

በመተንተን ከፎክሎር አንጻር ለምዘና ተግባር የዋሉ ስራዎችን ለመለየት የሚያስችል ቅፅ ከተዘጋጀ በኋላ በፎክሎር ትምህርት ዘርፍ ሁለተኛ ድግሪ ባላቸው ሁለት የስራ ባልደረቦች አማካኝነት በማስገምገምና የሙከራ ተግባር (pilot project) በማከናወን በታዩ ክፍተቶች ላይ እርማት ከተወሰደ በኋላ መረጃ የመሰብሰብ ስራው ተካሂዷል፡፡ በተዘጋጀው ቅፅ አማካኝነት ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ከመዳሰስ አንፃር በየፕሮግራሞቹ በመቅረብ በስራ ላይ የዋሉ ስራዎችን ለማወቅ በፕሮግራሞቹ ያለው የድግግሞሽ መጠን ቆጠራ ተካሂዷል፡፡ አቆጣጠሩ የቀረቡትን ፕሮግራሞች በመዘርዘር የተከናወነ ሲሆን አስቀድሞ ይህን ተግባር ለማከናወን አጥኚው ስለጥናቱ አካሄድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ይሆን ዘንድ የጥልቀት ንባብ አካሂዷል ፡፡

### 3.4.2. ሰነድ ፍተሻ

ከቪዲዮው ፍተሻ በተጨማሪም በፕሮግራሞቹ የቀረቡትን የፊልም ይዘቶች በምን አይነት ሁኔታ እነደሚዘገቡና እንደሚሰነዱ፣ በተከታታይ ስለመዘገባቸው፣ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሚቀርቡት ታቅደው ወይም በእግረመንገድ ጉዳይ የሚሉትን ለመለየት ደግሞ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሆነውን የሰነድ መፈተሻ ቅጽ መሠረት ያደረገ ፍተሻና እንዲሁም መደበኛ ያልሆነ የቃል ጥያቄ ለሚመለከታቸው አካላትና ለፕሮግራም ጋዜጠኞች በማቅረብ መረጃ የማሰባሰቡ ሂደት ተከናውኗል፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ አስተማማኝነት በጣም ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ መሆኑን ለማረጋገጥ ተሞክሯል ፡፡ ይህም የተደረገበት ዋናው ምክንያት የጥናቱን የአስተማማኝነት ደረጃ ለማጎልበት ታስቦ ነው፡፡

### 3.4.3. ምልከታ

ከፍሲል ለመጠቆም እንደተሞከረው ምልከታ በአጋዥነት አገልግሎት ላይ የዋለ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ ይኼውም ለጥናቱ የትንተና ተግባር የሚውለውን መረጃ ተቀባይነትና ተአማኒነት ለማሳደግ ሲባል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያውን ከአንድ ይልቅ ሁለት ቢሆን ተመራጭ መሆኑን በማመን ምልከታን ለቪዲዮና ለመዛግብት ፍተሻው በአጋዥነት ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡ ምልከታውን ለማካሄድም በመጀመሪያ የምልከታ መከታተያ ቅጾችን ለማዘጋጀት የተሞከረ ሲሆን ለጥናቱ በተለዩት የቴሌቭዥን ጣቢያዎች በሁለት በሁለት ዙሮች በመገኘት ማመሳከሪያ ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በምልከታው ወቅት ትኩረት ከተደረገባቸው ነጥቦች መካከልም በተተኳሪ የቴሌቭዥን ጣቢያዎቹ በቋሚነት የሚተላለፉ ዕለታዊ፣ሳምንታዊ እንዲሁም ወርሃዊ ፕሮግራሞች ስለመኖራቸው፣በየፕሮግ ራሞቻቸው ፎክሎር ነክ ጉዳዮች ስለመካተታቸው ፣ የተነሱ ጉዳዮች የሚሰጣቸው ሽፋን ምን መልክ እንዳለው ለመቃኘት የተሞከረባቸው ሂደቶች ተጠቃሽ ናቸው ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመረጃ ትንተና

### 4.1. በፋና ቴሌቪዥን በጉዞ ኢትዮጵያ ፕሮግራም የተላለፉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንተና

ይህ ክፍል የተሰበሰበው መረጃ ተተንትኖ የቀረበበት ነው፡፡ ይህውም በጥናቱ ዓላማ መሰረት ጥናቱ የሚያጠነጥንባቸው መሰረተዊ ጥያቄዎች ማለትም ፡-

- ❖ ተተኳሪ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች የትኞቹን ፎክሎራዊ ጉዳዮች በፕሮግራሞቻቸው አካትተው አቅርበዋል?
- ❖ የፎክሎር አይነቶች በተሻለ ድግግሞሽ ተካትተው የቀረቡት በየትኛው የቴሌቭዠን ጣቢያ ነው?
- ❖ በፋናና በኢቢስ የቴሌቭዝን ሳምንታዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች የተካተቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሚኖራቸው ፋይደ ምንድን ነው?ለሚሉት ጥያቄዎች በዚህ ክፍል ውስጥ ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

| ቁ | የቀረበው ፕሮግራም ርዕስ | ክፍል | ደቂቃ | ቀን/እ.ኤ.አ/ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | "እመ-ጓል ቅዱሱ ፅዋ የተሰወረበት ተዓምረኛ ቦታ"በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል1 | 24:44 | Feb 15/2020 |
| 2 | ‹‹በጌዴኦ ውብ ደህንነት አርንጓዴ የቱሪዝም ፍለጋ›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 21:58 | |
| 3 | ‹‹ጥምቀትን ከአርባራቱ ታቦታት ጋር›› በሚል የቀረበው ፕሮግራም | | 19:36 | jan 21/2020 |
| 4 | ‹‹አባ ዮሐኒ የምድር ወገብ ላይ ውቅር ቤተክርስቲያን›› በሚል የቀረበው ፕሮግራም | | 22:39 | Apr26 /2020 |
| 5 | ‹‹ከዙር አምባ እስከ ቤተልሔም ቀደምቶቹ ዩንቨርስቲዎች››በሚል የቀረበው ፕሮግራም | ክፍል1 | 23:25 | may 15/2021 |
| 6 | ‹‹ወደ ማጎ ብሔራዊ ፓርክ››በሚል የቀረበው ፕሮግራም | | 21:47 | Aug12/2020 |
| 7 | ‹‹የማሪያም ታንባ ውቅሮች ተንቤን››በሚል የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም | | 20:24 | |
| 8 | ‹‹ጨበራ ጩርጩራ ብሄራዊ ፓርክ›› በሚል የቀረበው ፕሮግራም | ክፍል1 | 30:17 | Nov 13/2021 |
| 9 | ‹‹ቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ›› በሚል የቀረበ የቴሌቪዥንፕሮግራም | | 24:37 | |
| 10 | ‹‹ጋራይሌ ብሄራዊ ፓርክ››በሚል የቀረበው ፕሮግራም | | 23:01 | |
| 11 | ‹‹እመ-ጓል ቆላ ውስጥ የተሰወረው ፅዋ›› በሚል በቀረበው ፕሮግራም | ክፍል2 | 24:41 | Feb 16/2020 |
| 12 | ‹‹የብልባላ ውቅሮች ››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 22:48 | sep 28/2021 |
| 13 | ‹‹ዘቢሞላ መስጂድ መካነቅርስ ››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል1 | 26:47 | |
| 14 | ‹‹የቡና ጫካ የሸፈነው የጌዲኦ ትክል ድንጋዮች››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 24:22 | |
| 15 | "ከ ጋራ ዱላ ጋራ ሰልፍ አድዋን ፍለጋ"በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል1 | 23:12 | |
| 16 | "የቆርኪዎች መጠለያ ሰንቀሌ ብሄራዊ ፓርክ" በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል1 | 23:41 | Oct31/2022 |
| 17 | ‹‹የፊውስ ተራራው ሚስጥር››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 25:05 | |
| 18 | "ጉንዳ ጉንዶ ከግዙፉ ተራራ እግርጌ" በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 22:07 | Jul 28/2020 |
| 19 | "የሰንቀሌ ቆርኪዎች መጠለያ ብሄራዊ ፓርክ"በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል2 | 25:41 | Oct 31/2022 |
| 20 | "የቦረና ተራራው ሽለቆው ከዳከታ--ኤሪርና ጎበሌ ሽለቆ" በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል1 | 22:06 | |
| 21 | "የቦረና ተራራው ሽለቆው ከዳከታ--ኤረርና ጎበሌ ሽለቆ" በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል2 | 22:06 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 22 | ”ከጮፌረ እስከ ድብቁ ፏፏቴ በጨበራ ጨፍጨራ ብሄራዊ ፓርክ“ በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል2 | 22:07 | Sep15/2021 |
| 23 | “ዘቢሞላ መስጂድ ታላቁ መካነ ቅርስ” በሚልየቀረበ ፕሮግራም | ክፍል2 | 24:48 | |
| 24 | ‹‹የ400 ዓመቱ ባለጸጋው ልብስም ጉርስም የሆነው ጓሳ››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል1 | 25:33 | |
| 25 | ‹‹ልብስም ጉርስም የሆነው ጓሳ›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል2 | 25:33 | |
| 26 | ‹‹ደብረሲና ማርያም ቤተክርስቲያን ጎርጎራ ጣና ሀይቅ››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 23:07 | Dec17/2019 |
| 27 | ‹‹አቡነ ሙሴ ገዳም›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 20:44 | Jan26/2021 |
| 28 | ‹‹የታደለው የቦረና ብሄራዊ ፓርክ››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 24:46 | oct 8/2019 |
| 29 | ‹‹ የሸህ አሊ መካነቅርስ መቃብር ጎንደር››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 23:43 | |
| 30 | ‹‹ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ ›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል2 | 23:12 | |
| 31 | ‹‹ከምንት ዋብ እስከ ቁስቋም ጎንደር ›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል1 | 27:08 | |
| 32 | ‹‹ድብቁ ውቅር ቅርስ ዞዝ አምባ ጊዮርጊስ››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 23:53 | |

## ሰንጠረዥ አንድ፦ በፋና ቴሌቪዥን በጉዞ ኢትዮጵያ ላይ የተላለፉ ፕሮግራሞች

### 1ኛ/“እመ-ጓል ቅዱሱ ፅዋ የተሰወረበት ተዓምረኛ ቦታ (ክፍል1)”በሚል የቀረበ ፕሮግራም ትንተና፡፡

ይህ ፕሮግራም “እመ-ጓል” በተባለ ስፍራ ላይ የሚያተኩር ሆኖ መልዓኩ ቅዱስ ኡራኤል የኢየሱስ ክርስቶስን ደም በጽዋ በመያዝ በዓለም የረጨበት ጽዋ የተሰወረበት ተአምረኛ ቦታን የሚያስቃኝ ፕሮግራም ሲሆን፤ ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚታየው የ (24:44) ደቂቃ ሽፋን አግኝቷል፡፡ የታሪኩ መቼት ከቦታ አንጻር መንዝ ማማ ሲሆን የመንዝ ማማ ከተማም ‹‹ሞላሌ›› ትባላለች ፡፡

ፕሮግራሙ የዳሰሳቸው ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ስንመለከት ከፍ ሲል በተጠቀሰው ቦታ ላይ የተሰወረው ቅዱስ ጽዋ፣ አምስቱ ጽዋዎች የተሠወሩበት ቦታን፣ የመንዝ ባህላዊ ቤቶችን፣ ቀደምት አድባራትና ገዳማትን የምናገኝ ሲሆን በአጠቃላይ የሃይማኖታዊ መስህብነትን የተላበሰ ቦታ ስለመሆኑ ከቀረበው ፕሮግራም መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ ዘገባ ውስጥ መንፈሳዊና ቁሳዊ የሆኑ ጥንታዊ ቅርሶች ተዘግበዋል፡፡ በዚህ አግባብ የተዘገቡት ፎክሎሮች የአካባቢውን ተአምረኛነት በማስተዋወቅ የቱሪዝም ማዕከልነቱን መንገር ብቻ ሳይሆን ተጨባጭ አድርጎ እንዲታይ ማድረግ ነው፡፡

‹‹እመ-ጓል›› ማለት ምን እንደሆነ በፕሮግራሙ ሲገለፅ እንሰማለን፡፡ ይኼውም ‹‹እመ›› ማለት እናት ማለት ሲሆን በዚህ አውድም ቅድስት ማርያም ማለት ሲሆን፡፡ ‹‹ጓል›› ማለት ደግሞ እየሱስ ክርስቶስ ማለት እንደሆነ በፕሮግራሙ ተገልጽዋል፡፡

እሙ-ጓል ከታሪካዊ ስፍራነቱ በተጨማሪም ፈዋሽ ፀበል የሚገኝበት ሲሆን ታሪካዊነቱም ዘመን ተሻጋሪ እንደሆነ እና ከአክሱምም እንደሚልቅ በፕሮግራሙ ተገልጽዋል ፡፡
የእሙ-ጓል ቅዱስ ኡራኤል ህንፃ ቤተ-ክርስቲያን /ደብር/ ዘመን ያስቆጠረ ቅርስ መሆኑን፤ የአካባቢው ህዝብ እንግዳ ተቀባይና እግዚአብሔርን አምላኪ በመሆኑ ትዕዛዝ አክባሪ መሆኑ ነው፡፡

ይህ ፅዋው የተሰወረበት ተዓምረኛ ቦታነት የተነገረበት እና የስፍራውን ታላቅነት ለተመልካቾቹ ያቀረበበት ፕሮግራም ነው፡፡ በመሆኑም ከተካተቱት ፎክሎሮች ውስጥ ህማመሥጋ ያለበት ለጸበለ ፈውስ እንዲበቃ፣ህማመነፍስ ያለበት ደግሞ ወደ ታሪካዊውና ዘመን ተሻጋሪው የኡራዔል ደብር ቢመጣ ዋጋ እንደማያጣበት የመስበክን ፋይዳ እናስተውላለን፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ሲል ከቀረቡት ሀተታዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በቀረበው ፕሮግራም የተካተቱት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ውስጥ ከስነ-ቃል አፈ-ታሪክ፣ከሀገረሰባዊ ልማድ መካከል ለምሳሌ የሃይማኖትና የእምነት ሎሮች ተካትተዋል፡፡ መንፈሳዊ ባህልና እንዲሁም ቁሳዊ ባህል ሰፊ ሽፋን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ተመልካቾቹም ከነዚህ ገለጻዎች የሚማሯቸው ልዩ ልዩ ፎክሎራዊ ፋይዳዎቸ መኖራቸው እሙን ነው፡፡ የመጀመሪያው ጉዳይ እነዚህን ማህበረ-ባህላዊ ጉዳዮች ያቀረበላቸውን ተቋም በባለቤትነት ስሜት አንዲያዩት ያስችላል፡፡ ከዚህም ባሻገር እምነታቸውን ያጠነክሩበታል፣ በጸበላቸውም መንፈሳዊም ይባል ሥጋዊ ፈውስን እንደሚያገኙበት የሚያስተማምን አስተምህሮትን ይቀስሙበታል፡፡

እንደሚታወቀው ቴሌቭዥን ተደራሽነቱ ሰፊ በመሆኑ በቴሌቭዥን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ሲሰራጩ ሰፊው ማህበረሰብ የባህል ውርርስ፣ ማሳደግና ባህልን ማስቀጠል እንደሚገባው ትምህርት ይቀስምበታል፡፡ ባህላዊ ማንነትንና ውክልናን ይማርበታል፤ ያሳድግበታል፡፡ ተመልካች ልክ እንደ መስታወት የራሱን ባህል፣ እምነትና ሃይማኖት ያይበታል፤ይማርበ ታል፤ ለተውልድ ያቆይበታል፡፡

## 2ኛ/"በጌዴኦ ውብ ደህንነት አረንጓዴ የቱሪዝም ፍለጋ"በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንተና፡፡

ፕሮግራሙ የዲላ ከተማን ይመለከታል፡፡ ስፍራው በታላቁ የአፍሪካ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ ይገኛል፡፡ ጌዶኦ ወይና ደጋ የአየር ንብረት ያለው አከባቢ ነው፡፡ አስተዳደር ባህላዊ መሪ ‹‹ጎቲ›› ቀበሌ የጌዲዮ አባገዳ መቀመጫ ናት፡፡ ከጋዲቻ ዳንቢባ ማሩ የአባገዳው

ምርቃት/መመረቅ/ሀገረሰባዊ ዕውቀት ደኑን እንዲጠበቅ አድርጎታል፤ይጠበቃልም። ከተፈጥሮ ጋር መጣላት ከፈጣሪ ጋር መጣላት እንደሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ በመታመኑ የሚጠበቅ ስፍራ እንዲሆን አድርጎታል።

የቡና ደን ተጠብቆ በመኖሩ የቡና ቱሪዝምን መስህብም ቦታ ነው። የሀገር በቀል ዕውቀት ከተፈጥሮ ጋር ተናቦ እየኖሩበት መሆኑን ማሳያም ስፍራ ነው። የአካባቢው ቀበሌዎች በዛፍ ስም መጠራታቸው ይህንንም ምክንያት በማድረግ የሚጠበቅበት ስፍራ ነው። በሌላም በኩል የጥምር ደን መገለጫም የሆነው ስፍራው ቡናና እንሰት በጥምረት የሚበቅሉበት ስፍራ እንደሆነ በፕሮግራሙ ቀርቧል።

በአጠቃላይ የእነዚህና መሰል ሌሎች ፎክሎሮች ለአብነትም ምርቃት፣አምልኮት፣ልዩልዩ ስያሜዎችና ሃገር በቀል ዕውቀቶች በቴሌቪዥን ፕሮግራሙ ተካትተው ለተመልካቾቹ መቅረባቸው የሚያስገኙት ፋይዳ ምንድን ነው? ወደሚለው ጥያቄ ስንመለስ ተከታዮቹን ምላሾች እናገኛለን። የመስኩ ምሁራን ለአብነትም Degh(1994) አንደሚያስረዱት ፎክሎር የቴሌቭዥን ምልከታዎችን(Shows)ያደፋፍራል፤ያነሳሳል፤የታዳሚንቀልብ ቆንጥጦ ይይዛል፤ ተመለተካቾች ወደራሳቸው ባህልና ልማድ፣እሴት እንዲያስቡ ብሎም የፎክሎር ፍላጎት እንዲኖራቸውም ያደርጋል። ስለሆነም ከላይ የተመለከትናቸው የፎክሎር ዘውጎች በፋና ቴሌቭዥን ፕሮግራም ተካትተው መቅረባቸው የሚያስገኙት ፋይዳም ከዚህ የሚለይ አይሆንም። በሌላ በኩል ቴሌቭዥን ደግሞ አድማሰ ሰፊ እንደመሆኑ መጠን በአንድ ጊዜ ለሰፊ አድማጭ ማኅበረሰብ የተዘነጉ፣ችላ የተባሉ የማህበረሰብ ሎሮችን መልሰው እንዲያገግሙ (እንዲታወሱ) የማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

**3ኛ/‹‹ጥምቀትን ከአርባ አራቱ ታቦታት ጋር›› በሚለው ፕሮግራም ላይ የቀረበ ትንተና።**

ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ባልጪ ከተማ ይገኛል። ባልጪ አማኑኤል ቤተክርስያን ስድስት መቶ ዓመት እድሜ ያለው ሲሆን በ1540 ዓ.ም የተተከለና ቀደምትነት ያለው ቤተ-ክርስቲያን ነው። ከተራን ሸንኮራ ኡራን ቡቲ ጥምቀት የታቦታት ማደሪያ ስፍራ እና የታቦታት አሸኛኘትን (ክዋኔ) የሚተረክበት ነው። የምጃር ባህላዊ ጨዋታ እና ጭፈራ ታቦታትን ያጀቡት ምዕመናን በዕልልታ ወደ ጥምቀተ ባህር ጉዞ ያደርጋሉ። ታቦታቱ ወደ ጥምቀተ ባህሩ የሚያደርጉትን የጉዞ ክዋኔ በፕሮግራሙ ቀርቧል ።

አስራ አንድ ታቦታት በአንድነት የሚያደረጉት ጉዞ እና የሚያድሩበት ስፍራ እስኪደርሱ በአካባቢው ባህል በጭፈራና ጫወታ ይደምቃል። በድምሩ አርባ አራት ታቦታት በአንድነት የሚያድሩበት ስፍራ "ኡራን ዙር" የሸንኮራ ወንዝ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተመሠረተ

ቦታ እንደሆነ እና ታቦታቱም በመጡበት አኳኋን እንደሚመለሱ በፕሮግራሙ ቀርቧል፡፡ ይህ የመባያ ጉዳይ በ19:36 ደቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን አካቷል፡፡የጥምቀትን ክብረበዓል በተመለከተ የማሃበረሰቡን ሃይማኖት፣ባህል፣እምነትና ማንነት መሰረት ባደረገ ሁኔታ የሚከወኑ ማህበረሰቡም የእኔ የሚላቸው ሃይማኖታዊ ትዉፊቱን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ሲል በተደጋጋሚ የሚከውናቸው ትውፊታዊ እሴቶች ሕዝባዊ ስፍራን በሚያመላክተው የታቦታት ማደሪያ መገለጫነት በፕሮግራሙ ሽፋን አግኝተው ገለጻና ማብራሪያ ተደርጎባቸዋል፡፡

ከፍሲል በቀረበው የቴሌቭዥን ዘገባ ውስጥ አራቱም የፎክሎር ዘውጎች ተካተው ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ስነ-ቃል(በከተራና በጥምቀት ተቦታት የሚታጀቡባቸው ባህላዊ ዘፈኖች የጭፈራ ክዋኔዎች)፣ሐገረሰባዊ ልማድ(የጥምቀት፣ሐገረሰባዊ ጨዋታና ክብረበዓል)፣ሐገረሰባዊ ትውን ጥበብ (የጥምቀት በዓል የካህናቱ ሽብሸባ፣የምዕመናኑ ሐገረሰባዊ ሙዚቃ)፣ ቁሳዊ ባህል (ሐገረሰባዊ ልብስ፤ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ እንዲሉ፣ሐገረሰባዊ የሙዚቃ መሳሪያ ለምሳሌ የካህናት ከበሮና ጽናጽል) ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ ልዩ ልዩ የፎክሎር አይነቶች በቀረበው የቴሌቭዥን ፕሮግራም መካተታቸው ወደሚያስገኘው ጠቀሜታ ስንመለስ ደግሞ የመስኩ ጠበብት የሚያነሷቸውን ቁምነገሮች እዚህ ላይ ማንሳቱ ተገቢ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለአብነትም የTayroeን በዝርዝር የቀረቡ ነጥቦች መመልከት ይቻላል፡፡ ከነዚህም መካከል ፎክሎር የባህሎች ሁሉ ውህድ አሃድ በመሆን ስብስብ ማንነቶች የመግራትና ቅርጽ የማስያዝ ሚና አለው፤ የታዳሚን ተሳትፎ የመቀስቀስና የማሳደግ ሚና አለው፤ ብዝሃ ባህላዊ ማንነትን ከፍ የማድረግ ሚና አለው፤ የባለቤትነት ስሜትን፣ የአብሮነት ስሜትን እንዲሁም ኩራትን የማስገኘት ሚና አለው፤ እንዲሁም ቱሪዝምን የማስተዋወቅና የማሳድግ ሚና አለው፡፡

### 4ኛ/"አባ ዮሐኒ የምድር ወገብ ላይ ውቅር ቤተክርስቲያን" በሚል የቀረበው ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንተና ፡፡

ተንቤን የውቅር አቢያተ ክርስቲያናት መገኛ ሲሆን ደብረ አሳ በዙሪያው አስር ገዳማት አሉት፡፡ ውቅሩ ሦስት ሜትር ከፍታ ያለው ሲሆን አፄ ገብረ መስቀል የሰየሙት ሲሆን ‹‹ባህታዊያኑ እንደ አሳ ናቸው›› በማለታችው ‹‹ደብረ አሳ›› ተባለ፡፡ አባ ዩሃኒ ፃድቅ እና ታላቅ አባት ናቸው፡፡ በሌላም በኩል በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአባ ዩሀኒ ታሪክ በአልሜዳ ቀና አፄ ገብረ መስቀል ደግሞ ገደሙት፡፡ ከቤተ-ክርስተያኑ ለመድረስ በውቅር የአለት ሆድ ውስጥ ማለፍ እንደሚጠይቅ በፕሮግራሙ አቅራቢ አማካኝነት የቀረበው ሀተታ በውል ያስገነዝባል፡፡

በፕሮግራሙ የውቅር አቢያተ ክርስቲያኑ የግድግዳ ስዕሎች እና ስለ ውቅሮቹ አጠቃላይ አወቃቀር ለተመልካቾቹ ቀርቧል፡፡ በዚህ 22:39 ደቂቃዎችን በፈጀው ገለጻ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑት ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህልና እንዲሁም ሥነቃላዊ አፈታሪክን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተካተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ የተለያዩ ፎክሎሮች መካተታቸው ደግሞ ማህበረሰቡ ባህሉን አጠንክሮ እንዲጠብቅና ለትውልድ እንዲያስተላልፍ የመስበክ ሚናን ይጫወታ፡፡ በሌላም በኩል እነዚህን ሰፊው ማህበረሰብ የእኔ የሚላቸውን ሀገረሰባዊ ልማዶችና ቁሳዊ ባህሎች ሽፋን በመስጠት ላቀረበው የቴሌቭዥን ጣቢያም ማህበረሰቡ ዕውቅና እንዲሰጥና የእኔነት ስሜት አድሮበት በአድማጭ ተመልካችነት ቋሚ ደንበኛ እስከመሆን ደረጃ እንዲደርስ የማድረግ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል፡፡

### 5ኛ/‹‹ከዙር አምባ እስከ ቤተልሔም ቀደምቶቹ ዩንቨርስቲዎች (ክፍል1)“ በሚል የቀረበው ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንተና ፡፡

በቤጌ ምድር ውስጥ ጋይንት በደቡብ ጎንደር ዞን የሚገኝ ስፍራ ሲሆን ዙር አምባም በዚሁ አካባቢ ባለ ውብ መልክዓ ምድርና ታሪካዊ የሆነውን የአቡነ አረጋዊ ዙር አምባን በውስጡ አቅፎ የሚገኝ ታሪክ ጠገብ አካባቢ ነው፡፡ ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው እኤአ ግንቦት 15 ቀን 2021 ዓ.ም አየር ላይ በዋለው የ23 ደቂቃ ፕሮግራም ልዩ ዕውቅና ካላቸው ሕዝባዊ ስፍራዎች አንዱ ስለሆነው የዙር አምባ አካባቢ ገለጻና ማብራሪያ ቀርቧል፡፡ በዝግጅቱ እንደተገለጸው የ1500 ዓመት የዕድሜ ባለ ጸጋ የሆነው አቡነ አረጋዊ ዙር አምባ 400 ሜ ከፍታ በምስራቅና፣በሰሜን፣ በምዕራብና በደቡብ 300 ሜትር ከፍታ ያለው ቦታ ነው፡፡

የጉና ከፍተኛ ስፍራ በዕውቀትና በእምነት ከፍ ብሎ የሚኖሩበት ስፍራ ሲሆን የአብነት ትምህርት ቤት ተስፋፍቶ ከሚገኝባቸው ስፍራዎች አንዱ የነበረ ነው፡፡ ለአብነትም ዝማሬ መዋሲት ትምህርት የሚሰጥበት(የሚመሰከርበት) እና ከቅዱስ ያሬድ ጋር የተያያዘ ታሪክ ያለው ታላቅ ቦታ እንደነበረ ተዘግቧል፡፡ ይህ ታሪካዊ አካባቢ በስድስት መቶ ክፍለ ዘመን በአጼ ገብረመስቀል እንደተመሰረተም ተነግሮለታል፡፡ አርባ አምስት መምህራን ከያሬድ ጀምሮ አርባ ስድስተኛው መምህር ድረስ ዝማሬ መዋስዕት ያስመሰክሩበትተቋም ሲሆን የቅዱስ ያሬድ አሻራ ያረፈበትና የምሁራን መፍለቂያም እንደነበረ በሰፊው ተተርኮለታል፡፡ ከዚህም ባሻገር በስፍራው የያሬድን ጥኡመ ዜማ ስትሰማ ለሁለት የከፈለች ዛፍ እስከ አሁን በስፍራው ስለመኖሯም ገልጽዋል፡፡ በስፍራው ከሚገኙ ቅርሶች መካከልም የቅዱስ ያሬድ

ፅናፅል፣ መቋቋሚያ፣ የአቡነ አረጋዊ ትዕምርተ መስቀል እና መቋሚያ፣ የፊታውራሪ ጎሹ ሰይፍ እና የአፄ ቴዎድሮስ መታጠቢያ ሳህን የሚገኙ ስለመሆኑ ተጠቅሷል፡፡

ታችጋይንት በደቡብ ጎንደር ዞን የምትገኝ በአብነት ትምህርት ማስመስከሪያነት ዕውቅና ያላት ባለታሪክ ቦታ ናት፡፡ጥንት አቤ ግድም በኂላ ግንቢያ የሚለውን ስያሜ ያገኘች፣በሁለቱ ወንድማማች ነገስታት በአብርሃና በአጽብሃ እንደተመሠረተችና ገናናነቷን ከአፄ ዳዊት ዘመን ጀምሮ እንዳገኘች የተነገረላት ይህች ስመ ጥር አካባቢ የቤጌምድር ግዛት አካል ነች፡፡ በተጨማሪም በዞጺ እንጨት የተሰራችውና በአብነት ትምህርት የገነነችው ለ400 ዓመታት ያህል የአብነት ትምህርት ድጓ ማስመስከሪያ ሆና የቆየችው ክቧ ደብር (ቤተክርስቲያንም) በዚሁ አካባቢ የምትገኝና የ1600 ዓመታት ታሪክ ያላት በማይዳሰሱ ቅርሶች እና በሚዳሰሱ ቅርሶች የታደለች እንደሆነች በፕሮግራሙ ለተመልካቹ ቀርቧል፡፡

በአጠቃላይ ይህ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ23፡25 ደኪቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃላዊ፣ሀገረሰባዊ ትውንጥበባትን፣ ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ፎክሎሮች በዚህ መልኩ መካተታቸውም ፎክሎር በቴሌቭዥን ውስት እንዴት እንደሚወከልና ቴሌቭዥንም ፎክሎርን ለማስተዋወቅና ለማስጠበቅ እንደሚያስችሉ ይሰብካሉ፡፡

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ለቴሌቭዝን ጣቢያው ተወዳጅነትን እንዲሁም ለታሪኩ ባለቤት ሰፊው ማሕበረሰብ ደግሞ ኩራትን የማላበስ ሚና እንደ ሚኖራቸውም እሙን ነው፡፡ በተጨማሪም ጥንታዊውና ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት በርከፋች መሰረት የነበረው ጥንታዊውና ልማዳዊው የቤተክህነት ትምህርት ባለበት ሁኔታ ተጠብቆ እንዲቆይ፣ እንዲሁም በሐገራዊ ትእምርትነት የሚታወቁት ያሬዳዊ ዜማዎች ባሉበት ሁኔታ ለትውልድ እንዲሸጋገሩ ማድረግ ይቻል ዘንድ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መረጃዎች በመሆን ያገለግላሉ፡ተመልካቾች ወደራሳቸው ባህልና እምነት እንዲመለከቱ ጊዜ ወስደው እንዲ ያስቡና ቅርሶቻቸውን በመንከባከብ ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ የማድረግ ሚናን ይወጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ጣቢያው እነዚህን የሕዝብ ሃብት የሆኑ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ዘግቦ ማቅረቡ በተመልካቾች ዘንድ ተወዳጅና ተደማጭ እንዲሆንና (Dunds1980) እንደ ሚያስረዱት ባህላዊ እምነቶችንና እሴቶችን በዚህ መልኩ ማካተትና መገኘት የፎክሎሮችን ህልውና ጠብቆ ለማሻገር አይነተኛ መሳሪያ ተብሎ እስከመቆጠር የሚያደርስ ዕውቅና ያስገኝላቸዋል፡፡

**6ኛ/"ወደማጎ ብሔራዊ ፓርክ"በሚል የቀረበው ፕሮግራም ላይ የቀረበ ትንተና፡፡**

መገኛውን ደቡብ ኦሞ ዞን ያደረገ መሆኑ የተነገረለት፤በ1972 ዓ.ም በፓርክነት የተከለለ፤ ማጎ ተራራ እና ማክ ወንዝ ተጣምረው ማጎ የሚለውን መጠሪያ ያስገኙለት፤የማጎ እና ሌሪ ወንዞች መገኛ መሆኑ የሚወሳለት ማጎ ብሔራዊ ፓርክ በኢቢኤስ ኢትዮጵያን እንወቅ ፕሮግራም ሽፋን ካገኙ ታሪኮች አንዱ ነው፡፡ በሰንጠረዥ 4.1 እንደሚታየው ፕሮግራሙ ከ21 ደቂቃ በላይ ሽፋን ተሰጥቶታል፡፡ ዝርዝር ሀተታውን ስንመለከትም ፓርኩ የአእዋፋት መኖሪያ መሆኑ መልክዓ ምድሩ፣ማህበረሰቡ እና በውስጡ የሚኖሩ እንስሳቱ መገለጫዎቹ እንደሆኑና ዋንጫና ሰው ሰራሽ ጥርስን ጨምሮ ልዩ ልዩ ጌጣጌጦችን ለመስራት ተፈላጊነት ያላቸው ከ870 በላይ ዝሆኖች እንደሚገኙበት ተዘግቧል፡፡ በተጨማሪም የአካባቢው ማሕበረሰቦች ከቀጭኔ ጭራ የአንገት ጌጥና ከጎሽ ቆዳ ደግሞ ጋሻ እንደሚሰሩ ለተመልካቾቹ አቅርቧል፡፡

በአጠቃላይ ስለማጎ ፓርክ ለ21፡ 47 ደቂቃዎች ያህል ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ከነዚህም መካከል በቁሳዊ ሀብትነት ጋሻ፣ጭራ፣ዋንጫና ሰው ሰራሽ ጥርስ በማሳያነት ተጠቅሰዋል፡፡ ከፍሲል በቀረበው ሀተታ መልክ የቀረበው ዘገባ ለሁለተኛ ቀን የሚቆይ ክፍል ሳያኖረው የተጠናቀቀው በአንድ ክፍል ብቻ ነበር፡፡

ለመሆኑ በዚህ ከፍሲል በቀረበው ዘገባ ልክ ፎክሎራዊ ጉዳዮች መካተታቸው ምን ፋይዳ ያስገኛል? የሚለውን ጥያቄ ስንመለከት የፎክሎር ዘርፍ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች በፎክሎሮቹ ተፈጥሯዊ ጥንተ ነገር ላይ፣ለማህበረሰብ በሚያበረክቱት ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ እንዲሁም በፎክሎሮቹ መጻኢ እጣ ፋንታ ላይ ጥልቅ ጥናትና ምርምር ያካሂዱ ዘንድ መነሻ ምክንያት በመሆን ያገለግላሉ፡፡

**7ኛ/‹‹የማሪያምታንባ ውቅሮች ተንቤን››በሚል በቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ የተደረገ ትንተና ፡፡**

ቆላ ተንቤን 95 ኪሎ ሜትር ያህል ከአቢ አዲ ይርቃል፡፡ የማርያም ታምባ ተራራ ላይ የምትገኘዉ አንዷ ተ/ሃይማኖት የተሰራችው በአቡነ አሮን አማካኝነት ሲሆን በሰባት ምሰሶዎች የቆመች እንደሆነች የፕሮግራሙ አቅራቢ ምንጮችን በመጥቀስ ዘግቧል፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ ተራራ 3 ውቅር አብያተክርሲያናትን ጠምሮ ይዞ የሚገኝ ስለመሆኑ ከዘገባው መረዳት ተችሏል ፡፡ ሁለተኛዋ ውቅር ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የማርያም ውቅር ቤተ-ክርስቲያን ናት፡፡ ወደዚች ቤተክርስቲያን ውስጥ ዘልቆ ለመግባት ጨለማ ከመሆኑ ጋር

ተያይዞ ብርሃን ሰጭ ነገር መያዝን ይጠይቃል። ሦስተኛዋ ማርያምታምባ መድኃኒ ዓለም ስትሆን የተዘጋና በምጽአት ይከፈታል የሚል አፈ ታሪክ ያለበት ስፍራ ነው።

ይህ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ20፡24 ደቂቃዎች በክፍል አንድ ብቻ ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን እንዲሁም የሥነ-ቃል ክፍል የሆነውን አፈታሪክን የተመለከቱ ፎክሎሮች በፕሮግራሙ ተካትተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል። ለመሆኑ የእነዚህ ልዩልዩ ፎክሎሮች በዝግጅቱ መካተት የሚኖራቸው ፋይዳ ምንድን ነው ወደሚለው ጥያቄ ስንመለስ በዘመኑ የነበረውን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ደረጃ ለአዲሱ ትውልድ በማስተዋወቅ ረገድ ጉሉህ ሚና እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል። ማስተዋወቅም ብቻ ሳይሆን በቅርስ ጥበቃና ክብካቤ ተግባር ሰፊው ማህበረሰብ አንዲሳተፍ የመቀስቀስ ሚናም አላቸው።

8ኛ/‹‹ጨበራ ጩርጩራ ብሄራዊ ፓርክ››(ክፍል1) ፕሮግራም ላይ የቀረበ ትንተና።

ፓርኩ በዓመያ የኮንታ ልዩ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን ፓርኩ በጨበራ ጩርጩራ አካባቢ ከአዲስ አበባ 465 ኪ.ሜ፣ከአመያ ደግሞ 13 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ከፋና ቴሌቭዥን ጣቢያ ኢትዮጵያን እንወቅ ፕሮግራም ዝግጅት መረጃ መገንዘብ እንደተቻለው በፓርኩ ትላልቅ እና ትናንሽ የዱር እንስሳት በጋራ ይኖራሉ። ይኼውም 18 አጥቢ ትናንሽ የዱር እንስሳት፣39 ትላልቅና መካከለኛ የዱር እንሰሳት እና ልዩ ልዩ የእፅዋት ዓይነቶች በብዛት ይገኙበታል። መልክአ ምድሩም የተራራ፣ወንዝ፣የእንጨት እና የሳር ምድርን አካቶ የያዘ ነው። ከላይ በሰንጠረዥ 4.1 ከቀረበው ማስታወሻ እንደምንገነዘበው ፕሮግራሙ በ30፡17 ደቂቃዎች በአንድ ክፍል ብቻ ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ሀገረሰባዊ ትውንጥበባት፣ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ሳይነሱ አካባቢያዊ እና ስነ-ምህዳራዊ ጉዳዮችን በመግለፅ ለተመልካቾቹ ቀርበዋል።

በሌላ በኩል በዚህ ዝግጅት ውስጥ የተካተተውን ፎክሎር ከስፍራ አኳያ የምንመለከተው ይሆናል። ሰለሞን (2007፣299) ሕዝባዊ ቦታ አንድ ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ ውስጥ ያለና ልዩ ማህበራዊ ዋጋ የሚሰጠው የሐገረ ሰባዊ ውክልና ዘርፍ እንደሆነ ያስረዳል። በዋናነትም መንገዶች ፓርኮች የሥብሰባ ቦታዎች የእርቅና የእንግዳ ማረፊያ ቦታዎች በዚህ በቦታ ሎር (Place lore) የሚካተቱ ስለመሆናቸው በሰለሞን ሀተታ ውስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን።

ከላይ በቀረበው ሀተታ ውስጥ የተካተተው የፎክሎር ዘውግ የሚያስገኘውን ፎክሎራዊ ፋይዳ ስንመለከት ጨበራ ጨርጨራ ፓርክ በዱር እንስሳትና በልዩልዩ እጽዋት የሞላ ፓርክ በመሆኑ ለቱሪስት መስህብነት እንደሚያገለግል በማስተዋወቅ ረገድ የመቀስቀሻ ሎር ሆኖ ያገለግላል፡፡ በሌላ በኩል የአካባቢው ማሕበረሰብ ይህንን ፓርክ በእኔነት ስሜት ተነሳስቶ እንዲንከባከበውም የማሳሰብ ሚናን ይጫወታል፡፡

**9ኛ/‹‹ቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ››በሚል በቀረበ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ የቀረበ ትንተና ፡፡**

በጠቅላላው ፕሮግራሙ ስለ ግዙፎቹ የአፍሪካ ዝሆኖች እና ስለ አኗኗራቸውን የሚያቀርብ ሲሆን የተከዜ ወንዝ የተፈጥሮ መስተጋብርና የፓርኩን ቁርኝት እንዲሁም የስደተኛ ወፎች ማረፊያ የሆነ ስፍራ ነው፡፡የቃፍት ሽራሮ ብሄራዊ ፓርክ የዕጽዋት ስብጥር ደን መገኛ ነው፡፡

የአካባቢው የደኑ ጠባቂዎች የሚያዘጋጁት‹‹የሻያ››ምግብ ስጋና አጥንት የተቀላቀለበት አይነት ምግብ ነው፡፡ አሰራሩም በውሀ ይቀቀል እና እንደገና በእሳት ተጠብሶ ለምግብነት ይውላል ፡፡ ይህም የፓርኩ ጠባቂዎች የሚመገቡት የተለመደ ምግብ ነው፡፡

ይህ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ24፡37 ደቂቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳይ የሆነውን ሀገረሰባዊ ልማድ የተመለከተ ጉዳይ በፕሮግራሙ በጥቂቱ ተነስቶ ለተመልካቾቹ ቀርቧል፡፡ በዚህ ፕሮግራም ከተካተቱት ሎሮችመካከል ሀገረሰባዊ ምግብና መጠጥ እንዲሁም ሕዝባዊ ቦታ ናቸው፡፡የእነዚህ ዘውጎች መካተትም እንዲሁ የራሳቸው የሆነ ፋይዳ እንዳላቸው እሙን ነው፡፡ለማሳያነት ለመጥቀስ ያህልም አካባቢውን የማስተዋወቅ ጠቀሜታ አላቸው እንዲሁም ለአካባቢው ባለድርሻ አካላት ደግሞ በማወቅም ባለማወቅም ፓርኩን ከመጉዳት እንዲጠበቁ የማስተማር ፋይዳም አላቸው፡፡

**10ኛ/‹‹ጋራይሌ ብሄራዊ ፓርክ››በሚል በቀረበው ፕሮግራም ላይ የቀረበ ትንተና ፡፡**

ይህ ፓርክ በሱማሌ ብሄራዊና ክልላዊ መንግስት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በውስጡም የዶዶ ኮረብታ ይገኝበታል፡፡ ከፍተኛ ስፍራው 1380 ሜትር ከፍታ ያለው እና 1734 ኪ/ሜ ስፋት አለው፡፡ በውስጡ ከአርባ ሁለት በላይ አጥቢ እንስሳት ይገኙበታል፡፡

ስለ ጋራ ይሌ ሌላው የተጠቀሰው ጉዳይ በወፍ ሀብቱ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ፓርክ የመሆኑነገር ነው፡፡ በፕሮግራሙ በዝርዝር እንደቀረበው ፓርኩ ከ230 በላይ ዝርያዎችን ይዟል፡፡

በአካባቢው የሚኖረው የገሬ ጎሳ ለደን አጠባበቅ ያለው እሳቤ እና እሴት ስፍራው እንዲጠበቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል ፡፡ በአጠቃላይ ጋራ ይሌ  የጎሣዎች ምድር ባህል የጠበቀው ባለፀጋ  ቢሆንም  በሰፊው ያልተጠና እና ያልተጎበኘ ፓርክ ነው፡፡ፓርኩ  የገሬ ጎሳ እሴት የሚጠብቀው ስፍራ ነው፡፡

በዚህ የቴሌቭዥን ዝግጅትም እንዲሁ ሕዝባዊ ቦታን የተመለከተ ፎክሎር ተገልጾበታል፡፡ የዚህ አይነቱ የፎክሎር ዘውግ በመካተቱ ምን ፋይዳ ይገኛል ከተባለም ከፍሲል በተራ ቁጥር 8 ላይ ከተገለጸው አንጻር መታየት የሚችል ነው፡፡

## 11ኛ/‹‹እመ-ጓል ቆላ ውስጥ የተሰወረው ጽዋ (ክፍል2)›› በተሰኘው ፕሮግራም ላይ የቀረበ ትንተና ፡፡

እመ-ጓል ቆላ ውስጥ  የተሰወረው ጽዋ መገኛ ስፍራ ነው፡፡ ቤተ-ክርስቲያኑ በአፄ ይኩኖ አምላክ  ዘመነ መንግስት ከተራራው ወደ ታች እንደወረደ ይነገራል ፡፡

የቅዱሱ ፅዋ እየሱስ ክርስቶስ ደም የተረጨበት መገኛ ቆጵሮስ ተራራ የአብነት ትምህርት ቤት አለ በስፍራው በትምህርት ላይ 150 ተማሪዎች ይገኙበታል፡፡ የገዳሙ ፀበል ከአምባው ሆድ ይፈልቃል፡፡ በውስጡ ሚስጥራዊ ዋሻ አለው፡፡ በተራራው ውስጥ ለውስጥ እስከ ቆጵሮስ የሚደርስ መንገድ እንዳለው ይነገራል ፡፡

አካባቢው አፄ ዘርዓ ያቆብ ያስተከላት ቀጭን አምባ መገኛም ነው፡፡ በስፍራው የምትገኘው አምባ ቀጭን በመሆኗ ምክንያት ቀጭን አምባ ማሪያም የተባለች ደብር እንዳለችም በዘገባው ተገልጽዋል፡፡

ደብረ ካሊና በካሊና ተራራ ላይ ትገኛለች፡፡ ስፍራውም የእየሱስ ክርስቶስ ደም የተረጨበት ቦታ ነው፡፡ ስፍራው አምስቱም ፅዋ የተሰወረበት ስፍራ ነው፡፡ በድርሳነ ቅዱስ ኡራኤል ላይ እንደተጠቀሰው በስፍራው ተዓምር ተሰርቶበታል፡፡ ቆጵሮስ አምባ ደሞ የተረጨበት ቦታ ነው፡፡

አምባው ግማደ መስቀሉ ያረፈበት ስፍራም እንደሆነ ይነገራል፡፡ በጠቅላላው በአርኪዮሎጃው ጥናት በተደረገለት መሰረት ጥንታው የመገልገያ ቁሳቁሶች ተገኝተውበታል፡፡

ከላይ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ24፡41 ደቂቃዎች በሁለተኛ ክፍል (ድግግሞሽ) ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን

የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተካትተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ማሕበረሰቡ ሕዝባዊ ሐብቱን እንዲንከባከብ የማሳሰብ፣አካባቢውን ለማያውቁ ወገኖች ደግሞ የማስተዋወቅ እንዲሁም ለቴሌቭዥን ፕሮግራሙ ደግሞ የአለኝታነት ስሜትን ስለሚያስገኝ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅነትን እንዲያገኝ የማድረግ ሚናን ይጫወታሉ፡፡

**12ኛ/‹‹የብልባላ ውቅሮች ››በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ የቀረበ ትንተና፡፡**

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ 4.1 እንደምንመለከተው ይህ ርዕሰ ጉዳይ አየር ላይ የዋለው በአንድ ክፍል ብቻ ሲሆን የወሰደው ጊዜም ሃያ ሁለት ደቂቃ ከአርባ ስምንት ሴኮንድ ነው፡፡ ታሪኩ የሚያጠነጥነውም የ1500 ዕድሜ ስላላቸው ውቅሮዎች ነው፡፡ ይኼውም ላስታ የውቅር አብያተ ክርስቲያኖች መገኛ ስለመሆኗና በአካባቢው ስለሚገኘው ታሪካዊ የቂርቆስ ደብር ነዉ፡፡

በፕሮግራሙ እንደተዘገበው ቤተክርስቲያኑ ከላሊበላ 33 ኪ.ሜ ርቀት ባለው የብልባላ ቀበሌ ይገኛል፡፡የብልባላ ቂርቆስ ቤተ-ክርስቲያን በ497 ዓ.ም ተጀምሮ በ500 ዓ.ም እንደተጠናቀቀ የሚነገርለት ታሪካዊ ደብር ነው፡፡የበሩ ቁመት ሁለት  ሜትር በአንድ ሜትር ነው፡፡ውስጡ ሦስት ሜትር ከፍታና ሁለትሜትር ስፋት ያለው ሲሆን ጥንታዊ  ስዕሎች በግድግዳው ላይ ተኮልኩለው ታሪካዊነቱን የሚያጎሉት ስለመሆኑም ዘገባው ያብራራል፡፡ቤተክርስቲያኑ በቅርስ ረገድም ታዋቂነትን ያገኘ ሲሆን 1500 ዓመታትን ያስቆጠሩ የአፄ ካሌብ መስቀሎች እና የብራና ጽሑፎች እንደሚገኙበትም ተዘግቧል፡፡

በሌላም በኩል የአርባራቱ እንስሳ ውቅርም ከላሊበላ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ መሆኑና ከላሊበላ ጋር በሚመሳሰል መልኩ ታንጸ ግልጋሎት መስጠት የጀመረው ከ485 እስከ 536 መሆኑን ከቀረበው ዘገባ እንረዳለን፡፡ የብልባላ ጊዮርጊስ ውቅር ቤተ-ክርስቲያን ከላሊበላ 30 ኪሎ ሜትር የሚርቅ ሲሆን ስያሜው ከነበ ልባላ  ወደ ብልባላ በጊዜ ሂደት እንደተለወጠ ይነገራል፡፡ ለስያሜው ለውጥ ምክንያቱ ደግሞ የአፄ ዘርዓያዕቆብ የልጅ ልጅ ቁስጥንጥንዮስ በዛ ባደረበት ወቅት ቤተ- ክርስቲያኑ በነበልባል ሲቃጠል በማየቱ በዚያ መነሻ እንደተሰየመ ከቀረበው ዘገባ መረዳት ተችሏል፡፡የዚህ የታሪካዊ ውቅር ቤተክርስቲያን አሰራሩ በምሳሌ ሲሆን አራቱ አምዶች የአራቱ እንስሳ ምሳሌ፣አስራ ሁለቱ ዓምዶች በአስራ ሁለቱ ሀዋሪያት ምሳሌ ፣ሶስቱ በሮች የስላሴዎች ምሳሌ ሲሆኑ አራቱ መስኮቶች ደግሞ የአራቱ ወንጌላዉያንን ተምሳሌት እንዳላቸው የፕሮግራሙ ሀተታ ያስረዳል፡፡ በዚህም ሳያበቃ በዚህ ታሪካዊ ደብር  ጥንታዊ የመስቀል እና የብራና ጽሑፎች የሚገኙ ስለመሆኑም ተወስቷል፡፡

በአጠቃላይ ከፍሲል በተከታታይ ከቀረበው ሀተታ እንደምንመለከተው በዘገባው ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል። የፋና ቴሌቭዥን ባቀረበው በዚህ ፕሮግራም ውስጥ እነዚህ ፎክሎራዊ ጉዳዮች መካተታቸውም ለአቅራቢው ድርጅትም ይባል ለባህሉ ባለቤት ማሕበረሰቦች የሚኖራቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው። ለአብነትም ቴሌቭዥን ጣቢያውን ታዋቂና ተወዳጅ እንዲሆንና እንዲህ አይነት ዘገባዎችን ያቀርባል በሚል መንፈስ ብዙ አድማጭ ተከታዮች በፕሮግራሙ የሚመሰጡበትን ሁኔታ የመፍጠር ጠቀሜታ ይኖራቸዋል። በሌላም በኩል ለአካባቢው ሰፊ ማህበረሰብ ቅርስ ምን ያህል ማንነት መገለጫ ሆኖ እንደሚያገለግልና ከታወቀበት የኢኮኖሚና የልዩልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች መደጎሚያ የገቢ ምንጭም መሆን እንደሚችል፤ በተጨማሪም የነዚህ አስገራሚ ሥነ-ቃሎች፣ሀገረሰባዊ ልማዶችና ቁሳዊ ባህሎች ባለቤት ሆኖመገኘት ታላቅ የኩራት ምንጭ ስለመሆኑ የማስተማር የጎላ ጠቀሜታም አላቸው።

### 13ኛ/‹‹ዘቢሞላ መስጂድ መካነቅርስ ክፍል1››በሚል ርእስ በቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ።

ይህ መካነ ቅርስ ስያሜውን ያገኘው ከአውራዎቹ ኢማሞች ሥም ሲሆን ለዚህም ዘቢ ሞላ አህመድ ተጠቃሽ መሆናቸውን ዘጋቢው በዝርዝር ለማስረዳት ከሞከረበት ሀተታ መረዳት ተችሏል። ዘቢሞላ መስጂድ ረጅም ዕድሜን ያሳለፈ (ከ1866) እስከ አሁን የቆየ አራት ትውልድን ያስተሳሰረ ስፍራ ስለመሆኑ በፕሮግራሙ ተብራርቶ ቀርቧል። ይህንንም ለማስረዳት በህይወት የሌሉትን እና በታሪክ ተጠቃሽ የሚሆኑትን አባቶች ታሪክ በዋቢነት ለማቅረብ የተሞከረበት ሁኔታ በመኖሩ ተከታዮቹ አባቶች ከዚህ አንጻር ቀረቡ ናቸው።

ቃቂዮ (ሼህ መሀመድ ረሺድ) ከ1888-1912 ዓ.ም የነበሩ፤ አብዮ (1856-1914)ዓ.ም የነበሩ፤ ሸህ በድሩ ስሩር(1910-1972ዓ.ም የነበሩ)እንደነበሩ ተጠቁሟል። በተጨማሪም በፕሮግራሙ ከተነሱት ውስጥ ዘቢሞላ ‹‹የመድኃኒት ዓለም(ቦታ)›› ማለት ስለመሆኑ፣መድሀኒት ወይም የበሀላዊ መዳኒት መገኛ ስፍራ ስለመሆኑ፣ስፍራው ከ600 በላይ ዛፎች ግዘፍ ነስተው የሚገኙበት ስለ መሆኑ፣ከነዚህም ውስጥ የ150 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ለምግብነት የሚውሉ ዛፎች የሚገኙበት መሆኑ፣እነዚህ ዛፎች ለአካባቢው ማህበረሰቡ እና ለስፍራው ውበትም መድሀኒትም፣ ጉርስም ሆነው የሚያገለግሉ ስለመሆኑ የፋና ቴሌቭዥን በሚገባ ዘግቦታል። በአጠቃላይ ስለ ዘቢሞላ መካነ ቅርስ ዘርዝሮ ለመጨረስ የማይቻል አስገራሚ ሁነቶች/ቅርሶች/ በመኖራቸው ሁሉንም ለማቅረብ አለመቻሉን በዘገባው ለመጠቆም የተሞከረበት ሁኔታም አለ። ይሁን እንጅ መቅረት የማይገባቸውን ቅርሶች ለማቅረብ

እንደተሞከረ በመጠቆም ለማሳያነትም ቦታው የጽሑፍ ቅርሶች ማዕከል እንደመሆኑ መጠን አንድ መቶ አስር ዓመታትን ያስቆጠሩ የጅማው አባጅፋር ስጦታዎች፣ የቆዩ ደብዳቤዎች፣ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች እና እስላማዊ የፅሁፍ ቅርሶች የሚገኙበት እንደሆነም ተጠቅሷል።

ከላይ በቀረበለን ታሪክ ውስጥ የተካተቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች (የፎክሎር ዘውጎችን) ስንመለከት ስነ-ቃል፣ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህል በፕሮግራሙ ተካትተው ለተመልካቾቹ መቅረባ ቸውን እንገነዘባለን። የእነዚህ ልዩልዩ ቁሳዊና መንፈሳዊ ቅርሶች፣ባህላዊ የህክምና ዘዴዎች በዚህ መልኩ መዘገብ የሚኖረውን ረብ ወይም ፋይዳ ከልዩ ልዩ አቅጣጫዎች በማንሳት ማየት ይቻላል። ለአቅራቢው የቴሌቭዥን ተቋም ተወዳጅንትና ታዋቂነትን ከማስገኘት ጀምሮ ለሙስሊሙማህበረሰብ ሃይማኖታዊ እሴቱን ተቀብሎ ለተተኪው ትውልድ ማስቀጠል እንዲችል በር ይከፍታሉ። አካባቢው በእነዚህ ልዩ ልዩ ሎሮች መኖር የተነሳ እንዲታወቅና ለጉብኝትም እንዲታጭ ያደርጉታል፤የባህላዊ ህክምና ትውውቅንም ይፈጥራሉ።

## 14ኛ/‹‹የቡና ጫካ የሸፈነው የጌዲኦ ትክል ድንጋዮች››በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ።

ስፍራው በሰውነት፣የሰው ፊት፣በወንድ ብልት የተቀረፁ ድንጋዮች ይገኙበታል። የመቃብር ስፍራ ክምችቶች ብዙ ናቸው። ረጅሙ 6 ሜትር ይደርሳል። በጌዴ ኦዞን 6 ትክል ድንጋዮች ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥ ስፍራው ከዲላ 21 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው።ስፍራው በ1986 ኢ.ም ፈረንሳያዊው የአርኪዎሎጂ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ሮጀር ጆንሰን በቁፋሮ ጥናታዊ ስፍራውን ያገኘበት ነው። በቁፋሮውም የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችና የሰው ቅሬተ አካል ተገኝቶበታል።ይርጋ ጨፌ ወረዳ ስዴ ቀበሌ የሚገኙት ትክል ድንጋዮች በብዛትና በግዙፍነታቸው የሚታወቁ ናቸው። ትክል ድንጋዮቹ ከሌሎች የሚለዩ ናቸው። በቁጥር 3 ዓይነት ናቸው። እነዚህም የወንድ ብልት፣አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለዉ፣ሁለት ክርክር ያለው የሚባሉት ሲሆኑ በቁጥር 486 ይደርሳሉ። ርዝመታቸውም 2.8ሜ ይደርሳሉ። አጭሩ 1.28 ሜትር ነው።

በሌላ ስፍራ ከሚገኙት ውስጥ ትክል ድንጋዮቹ ገደብ ወረዳ ሳካሮ ቀበሌ የሚገኙ ናቸው። በጌዴኦ ቋንቋ ‹‹ሶዶ›› ማለት ‹‹ትክል ድንጋይ›› ማለት ነው። ድንጋዮቹ ዉፍረት አላቸው። ብዛታቸው 46 ሲሆን የሚገኙበት ቦታ የፋሎ ባህላዊ አምልኮ የሚከናወንበትን ስፍራ ነበር።

በዚህ መልክ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ24፡22 ደቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ

ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ከላይ በተራ ቁጥር 13 ለመግለጽ እንደተሞከረው እነዚህ ልዩልዩ የፎክሎር አይነቶች በፕሮግራሙ ውስጥ ተካትተው መቅረባቸው የሚያስገኙት ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ Dunedus (1980)እና Degh (1984) በየጽሁፎቻቸው ያስነበቧቸው ቁምነገሮች እንደሚያመላክቱት የፎክሎሮች ቴሌቭዥንን ጨምሮ በሚዲያዎች ተካትተው መቅረብ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው መታወቅ እንዳለበት ነው፡፡ እንደምሁራኑ ገለጻ ከጠቀሜታዎች ጥቂት ለመጥቀስ ያህል ባህላዊ አፈታሪኮችን ለመፍጠርና ለማስቀጠል፣ ባህላዊ እምነቶችንና እሴቶችን እንዲሁም ልምዶችን ለማስጠበቅ የሚያስችል ግንዛቤ በመፍጠር በኩል የማይናቅ ሚና አላቸው፣አካባቢያዊ ወይም ሀገራዊ ከዚህም ሲያድግ ዓለማቀፋዊ የማንነት ስሜትን የመፍጠር ሚናን ይጫወታሉ፣ እንዲሁም ባሕልን ለመለማመድ አይነተኛ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

በሌላ በኩል የፎክሎር በቴሌቭዥን ፕሮግራሞች መካተትና ለስርጭት መብቃት ለሚዲያዎቹ ለራሳቸው ምን ጠቀሜታን ያስገኛሉ ወደሚለው ሌላኛው የጥናቱ ትኩረት ወደሆነው ጥያቄ ስንመለስ ከፍሲል በስም የተገለጹትን ምሁራን ጨምሮ ሌሎች የመስኩ ጠበብቶች ለአብነትም Jakson(1989) አንደሚያስገነዝቡት ማንበብና መጻፍ ለማይችሉ ማህበረሰቦች ስለባህላቸው ተጨባጭ መረጃዎችን ለማቅረብ፣ በአንድ ባህል ውስጥ ያሉ ጭብጦችን በቀላሉ ለማስረዳት እንዲሁም የታሪክ ነገራ(Story Telling) ስልቱን ተመራጭና በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ በማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ጭብጦችን በቀላሉ ለማስረዳት የጎላ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

### 15ኛ/“ከጋራ ዱላ ጋራ ሰልፍ አድዋን ፍለጋ(ክፍል1)”በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

ስፍራው በደቡብ ኢትዮጵያ ደራሼ ወረዳ ጊዶሌ ከተማ ጋርዱላዎች መንደር የጋራዱላ ተራራውን የሚመለከት ነው፡፡ ጋራ ዱላ የሰፊ ግዛት ስም ነው፡፡ የታሪክ ሰነድ እንደሚ ያሳየው እንደ አደዋ የሚጠቀስ ስፍራ መሆኑን የፕሮግራሙ አቅራቢ ካጋራው ታሪክ መረዳት ተችሏል፡፡

የፋና ቴሌቭዥንን ዘገባ ዋቢ አድርገን ስንመለከት ጊዶሌ ተነግሮ የማያልቅ ታሪክ ባለቤት ናት ማለት ማጋነን አይሆንም፡፡‹‹ጊዶሌ››፤‹‹ኪቶሌ›› ወይና ደጋ ማለት ሲሆን ኪቶሌ ከአዲስ አበባ 555 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ በ1929 የተመሰረተች፤ለአድዋ ለመታሰቢያው የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ህንፃ አለ፡፡ የደራሼ፣የማሽሌ፣የኩስሜና የሙሴዬ ብሄረሰቦች መገኛ ናት፡፡ዶሌ ከአድዋ መልስ በዘመኑ አርበኞች የተቆረቆረች ከተማ ናት፡፡ አካባቢው

በፊልም፣በሙዚቃ እና በእርከን ሥራ ይታወቃል፡፡ የጋር ዱላና አድዋ ከአርበኝነት መልስ በዘማቾች በተሰሩ ቤቶች ተቆረቆረች፡፡ አመጣጣቸውም የጊዮርጊስን ታቦት ይዘው ሲዘምቱ ከመራቤቴ ነው፡፡ ወረኢሉ፤አራዳ ጋራዱላ ጊዮርጊስ ታቦቱን አጅቦ በመጡት ሰዎች የተቆረቆረች፤አድዋ የዘመተ ታቦት ነው፡፡

የጋራዱላ ጊዮርጊስ ቅርሶች፣ የብራና መጽሐፍት፤ የብር መስቀሎች፣ ሰው በመሆኑ ብቻ የሚኖርበት ቤት እና ቀደምት ቤቶች ያሉት ከባቢ ስለመሆኑ ተድላ ዘዮሐንስ ስለ ጋሪዱላ ተጋድሎ ኢጣሊያን በኢትዮጵያ መጽሐፍ ተርከውታል፡፡

የሰማትነት መቃብር ስፍራው ለሀገሪቱ የተሰውበት መታሰቢያ የተሰራለት የፊታውራሪ ገበየሁ ማስታወሻ ሲሰራብ 1938 መሰረቱ ተጣለ፡፡ በ1948 ስራ ጀመረ፡፡

‹‹የአደዋን ስላሴ ጣሊያን አረከሰው

ገበየሁ በሞቴ ግባና ቀድሰው፡፡››

የተባለለት፤ በስማቸው ትምህርት ቤት ተሰይሞላቸው የነበሩ ናቸው (አሁን ቢቀየርም)፡፡

ይህ ከላይ የቀረበው ከፋና ቴሌቪዥን ተቀንጭቦ የተወሰደ ማብራሪያ በ23፡12 ደቃዎች የቀረበ ሲሆን ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተካትተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ፎክሎሮች በመካተታቸውም የሚያስገኙት ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ለማሳያነት ያህል ለመጥቀስም ባህላዊ ሥያሜዎችን ከነፍቻቸው የማስተዋወቅ፣ ቁሳዊ ባህሎችን(ብራና መጻህፍት፣የብር መስቀል) በማስተዋወቅ ቱሪዝምን ለመሳደግ፣ የሀብታቸውን አይነትና ደረጃ ልብ ብለው ለማያውቁ የፎክሎር ባለቤቶች በማስተዋወቅ ማንነታቸውን በውል እንዲረዱ የማስቻል ሚና አላቸው የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

### 16ኛ/‹‹የቆርኪዎች መጠለያ ሰንቀሌ ብሄራዊ ፓርክ (ክፍል1) ››በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

ከአ.አ አጄሲራሮ ወረዳ 305 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ በዓለም የትም የሌለን 540 ኪሎ ሜትር ስኩዌር ስፋት ሸፍኖ ያለው ነው፡፡ አካባቢው የተለያዩ የእፅዋት ዝርያ ያለው ስፍራ ነው፡፡ ለአብነትም አታሎ ሰፈራ አራት የግራር ዝርያዎች የሚገኙበት ሲሆን፤አርባ አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ፓርኩ ከ36 በላይ የአጥቢ እንስሳት መገኛ ነው፡፡ 191 የአዋፍ ዝርያዎች የሚገኙበት ስለመሆኑ ከቀረበው ፕሮግራም መረዳት ይቻላል፡፡

ይህ ከላይ የቀረበው ታሪክ ከቴሌቪዥን ፕሮግራሙ ተቀንጭቦ የተወሰደ ሲሆን ሙሉ ትረካው የ23፡41 ደቃዎች ሽፋን የተሰጠው ነው፡፡የሆነ ሆኖ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በፕሮግራሙ በሚገባ ሳይነሱ የቀሩበት፤ያልተካተቱበት ሆኖ ይታያል፡፡ይህም በመሆኑ ፕሮግራሙ ሳቢነት የጎደለውና ተራ ማስታወቂያ መስሎ እንዲታይ አድርጎታል፡፡

**17ኛ/"የፌውስ ተራራው ሚስጥር"በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡**

በደቡብ ክልል የም ታቦር ተራራ የብሄረሰቡ ባህላዊ መድሀኒት የሚለቀምበት ጊዜን የሚያስቃኝ ነው፡፡ጥቅምት 17፤ ከፍታው 2939 ከሆነው የፌውስ ተራራ የጥቅምት ወር ዓመታዊ ስርዓት ወይም ባህላዊ መድሃኒት ለቀማ የሚደረግበት ሲሆን፤ለቀማውም በዓመት በተወሰነ ቀናት ብቻ ይደረጋል፡፡ ለቀማው ስርአትን የተከተለ ሲሆን፤ የፀሀይ በሽታ የሚባለው ፀሐይ ሳይወጣ የሚለቅመው ነው፡፡በህብረት ይለቅማሉ፤ዓመትን ጠብቆ መድሃኒት የሚሰበሰብበት ነው፡፡ ለዘመናት የሚካሄዱት ስርዓትነው፡፡ ስር፤አበባ፤ፍሬ፤ ይለቀማል፤ለመድሃኒትነት ማይውሉት የማይለቀሙ አሉ፡፡ በእኛችን የያዝነውን ወርቅ ‹‹የተረሳው የባህል እክምና›› ስርአቱ ለዘመናት የተከናወነበት ተራራ ነው፡፡

በዚህ የፌውስ ተራራን አስመልክቶ በቀረበ ፕሮግራም ላይ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑት ሀገረሰባዊ መድሃኒት፣ስነ-ቃል(ሕብረዝማሬ)፣ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ ለተለያዩ በሽተኞች የሚሰጡ ስራስሮች አበባዎች ፍሬዎች በቁሳዊ ሃብትነት የሚፈረጁ ፎክሎሮች ናቸው ፡፡ እነዚህ ልዩልዩ ፎክሎሮች መካተታቸውም የሚያስገኙት ፋይዳ በሁለት መልኩ የሚታይ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ለቴሌ ቭዥን ጣቢያው ታዋቂነትን ከመፍጠር አኳያ፣ባህሌን አስተዋወቀልኝ፤ ዘገበልኝ በሚል መነሻ ብዙ ደንበኞችን የማፍራት ዕድል ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩ ለፎክሎሮች ለራሳቸው በቴሌቭዥን የመሰራጫት እድል ማግኘታቸው ፕሮግራሙ ብዙ ተመልካቾችን በአንጼ በመድረስ ረገድ ፈጣን በመሆኑ የሎር ባለቤቶች ስለ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶቻቸው በማወቅና በመረዳት ሊደረጉ የሚገቡ ጥበቃዎችንና ለቀጣይ ተውልድ ለማስተላፍ የሚችሉ ባቸውን መንገዶች የተረዱ ወገኖች ጥበቃ ያደርጉላቸዋል፡፡ በዘገባዎች መነሻ የቅርሶቻቸውን ብዛትና አይነት በመመርመር ቅርሶች እንዳይሸጡ፤ እንዳይለወጡ የሚደረጉበት አሰራር ይዘረ ጋላቸዋል፡፡

**18ኛ/‹‹ጉንዳ ጉንዶ ከግዙፉ ተራራ እግርጌ››በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡**

ጉንዳ ጉንዶ የሚገኘው በስተምስራቅ ሲሆን አይዞን ገለን ለጉንዳጉንዶ የመነሻ አምባ ናት፡፡ ከሰማይ የተደበቁ ተራሮች ለመድረስ ጉዞው ያሲን በግርጌ ዲማ ማርያም የሮብ ማህበረሰብን

የቤት ግንባታ አሠራርን የምናይበት ነው፡፡ የአባቶች ዝማሬና የአባቶች ምስጋና ከሰማይ የሚፈስበት ምድር ነው፡፡

በተራሮቹ ጉንዳ ጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማሪያም ገዳም እና የመንደሯ ቤቶች በተራራው ላይ የሰፈሩ ያለት ቤቶች መገኛ ስፍራ ነው፡፡ ደብረ ገሪዛን ከ600 ዓመት በላይ ያስቆጠረ ደብር ነው፡፡ ታሪካዊ ኪነ ህንፃ ቤቶቹ ከተጠረቡ ድንጋዮች የተሰሩ ናቸው፡፡

ስፍራው ጥር 21 ማርያም ይደምቃል፡፡ ጉንዳጉንዶ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተነባብሮ የተሰራ ኪነ ህንፃ ነው፡፡ ሁለተኛው አበምኔት አባ እዝራ እንደሠሩት ይነገራል፡፡ በፅሁፍ ቅርስ እና በክምቾትና በማቆየት ዋናው ነው፡፡ጥንታዊ መስቀሎች፣ዘውዶች፣ፅዋዎች፣ፅናፅሎች፣ወዘተ መገኛ ሲሆን በተጨማሪም ያስተርዮ በዓል አከባበር ጥር 21 ቀን ሲከበር የኢሮብ ወጣቶች የንግሱ አድማቂዎች ናቸው፡፡

በቀረበው ታሪክ ውስጥ አራቱም የፎክሎር ዘውጎች ተካትተዋል፡፡ ለአብነትም ከሃገራዊ ልማድ ውስጥ ባህላዊ ህክምና፣ ሕዝባዊ ሁነት፣ ክብረ በዓል፣ ስርአተ ከበራ፤ እንዲሁም ከሃገራዊ ትውንጥበባት የአስተርዮ ንግስ ሽብሸባዎች፣ከቁሳዊ ባህል ደግሞ ከጥርብ ድንጋይ የተሰሩ ሀገረሰባዊ ምህንድስናን የተላበሱ ቤቶች የተስተዋለበት የቤት ግንባታ ከሥነ-ቃል ደግሞ የአባቶች ምስጋናና የጥር አስተርዮ ማርያም የባህላዊ የዘፈን ግጥሞችን እናገኛለን፡፡ በ22 ደቂቃ ውስጥ በአንድ ክፍል ብቻ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተካተው ለተመልካቾቹ መቅረባቸው የሚያስገኙት ፋይዳ ስለመኖሩ የሚያጠ ራጥር ጉዳይ የለም፡፡ይኼውም ማህበረሰቡ ስለአካባቢውና ስለ ሃገሩ ያለውን እይታ እንዲ ያሳድግ አስተምህሮ ይሆናሉ፡፡ የማንነቱ አሻራ የሆኑትን ልዩልዩ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህሎች የመጠበቅና የመንከባከብ ብሎም ለትውልድ የማስረከብ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ ማህበ ረሰቡን የማንቃትና የማስተማር ሚናን ይወጣሉ፤በፎክሎር ዘርፍ ለአጥኚዎች መረጃ ይደርስ ዘንድ ምክንያት ይሆናሉ በልምድና በተግባራዊ ድግግሞሽ የዳበረ ዕዉቀትን የመግለጥ ሚናን ይጫወታሉ፡፡

### 19ኛ/‹‹የሰንቀሌ ቆርኪዎች መጠለያ ብሄራዊ ፓርክ››(ክፍል2) በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

ይህ የሰንቀሌ ቆርኪዎች መገኛን የተመለከተ የቴሌቭዥን ፕሮግራም በሁለት ክፍል ተደራ ጅቶ የቀረበ ሲሆን፤ይዘቱም ባህል የታደገቻቸውን እንስሳት የሚያስቃኝ ዝግጅት ነው፡፡ የስፍ ራውን መገኛ፤የፓርኩን ስፋት እና በውስጡ የሚገኙትን ብርቅዬ የእፅዋት ዝርያዎች ምን

መሰልነት አስመልክቶ ዘገባው በቂ መረጃ አቅርቧል፡፡ በማሳያነት የተወሰኑትን እንመልከት፣ ከ36 በላይ አጥቢ እንስሳት መገኛ መሆኑ፣የ191 አዕዋፍት ዝርያ ስፍራ መሆኑ፣በስፋት የቀረበበት ሲሆን በዋናነትም ለፓርኩ መጠበቅ ምክንያት የሆነውን የጎሳ መሪዎችን (አባገ ዳዎች) ትዕዛዝ በማክበር መሆኑን ተገልጧል፡፡ በአካባቢው ሌላው አስገራሚ ባህል ደግሞ ‹‹አንድ ሰው ከአንድ ቆርኬ እኩል ነው፡፡››አንድ ቆርኬ የገደለ (100 ከብት) እንዲከፍል የሚጣልበት ቅጣት ከበድ ስለሚል እና በማህበረሰቡ መሪዎች የተወገዘ ስለሚሆን ቦታው የተጠበቀ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የሰንቀሌ ማህበረሰብ ባህል ቆርኬን የማህበረሰቡ አካል ያደረገ ባህል ነው፡፡

ይህ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ25፡41 ደቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ ሀገረሰባዊ ልማድን በተመለከተ የአባገዳዎች ሥነ-ስርአት ሊተነተን ይችላል፡፡ በሌላም በኩል እንስሳትን የማክበር፣የመጠበቅ ባህል ከሰው እኩል የመቁጠር ዲሞካራሲያዊ ባህል የአካባቢው መገለጫ ሉር ሆነው ቀርበዋል፡፡

ለመሆኑ ፎክሎሮቹ የሚያስገኟቸው ፋይዳዎች ምን ምን ናቸው? ወደሚለው የምርምሩ አይነተኛ ትኩረት ስንመለስ ደግሞ የፎክሎሮቹ አውድ እንደሚያስረዳው ባህላዊ ዳኝነትን የማስረጽ ሚና አላቸው፣ይኼውም ማህበረሰቡ ለአባገዳዎች ፍርድ ራሱን ያዘጋጀ መሆኑ፣ መሪየ ጠባቂየ ብሎ ያስቀመጣቸው ተሰሚነትንና ከበሬታን የቸራቸው ባህላዊ አስተዳዳሪዎች መኖራቸውን በአባገዳዎች ስርአት አለመጣስና አስገዳጅነት ሀተታ አማካኝነት ተገልጽዋል፡፡ ሌላው ደግሞ ዲሞክራሲያዊ አኗኗርን የማለማመድ ሚናም እንዳላቸው ቆርኪዎችን ከሰዎች እኩል የማየት ባህልን በማሳያነት ለማቅረብ የተሞከረበትን ዘገባ ማጤን ይቻላል፡፡

**20ኛ/‹‹የቦረና ተራራው ሸለቆው ከዳከታ-ኤረር እና ጎበሌ ሸለቆ(ክፍል1)›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡**

ባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ነው፡፡ከአዲስ አበባ 560 ኪሎ ሜትር ላይ ይገኛል፡፡ከሐረር ጅጅጋ 40 ኪሎ ሜትር ላይ ዳከታ በሚባል ስፍራ የሚገኝ ነው፡፡ፓርኩ በ1962 ዓ.ም የዝሆኖኖች መጠለያ እንዲሆን ተከልሏል፡፡ስፍራው ከተፈጥሮ አንጻርም በድንጋዮቹ ቅርጽ የሚገርም ነው፡፡

አዜ ኃ/ስላሴ የሚመለከቱበት ቤት ይገኛል፡፡ ኮረብታው‹‹ቱሉ ጃርሳ›› ይባላል፡፡ ስፍራው ከ31 በላይ አጥቢ እንስሳት የሚኖሩበት ሲሆን 782 ኪ.ሜ ስፋት የሚሸፍን ሲሆን ከጋራ ሙለታ-ፋፈም ይደርሳል፡፡

ኤረር ዞን ፊቅ ወረዳ ፊቅ ቀበሌ የሸለቆው ምህዳር እና የኤረር ወንዞች ተገናኝተው ወደ ዋቢ ሸበሌ የሚያደርጉትን ጉዞ በማስቃኘት ከቀረበው ፕሮግራም የምንማረው ብዙ ነገር ነው፡፡ የሆነሆኖ ከብዙ በጥቂቱ የተዘገበው ፕሮግራም የሚያስረዳን ከፍሲል ለመጠቃቀስ የተሞከሩ ትን ነው፡፡ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ22:06 ደቂቃዎች የተሸፈነ ሲሆን ፎክሎራዊ ጉዳዮችን እምብዛም ሳያነሳ ሀገረሰባዊ ልማድን የተመለከቱ ጉዳዮች ብቻ በፕሮግራሙ ተነስ ተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ ለአብነትም "ንጉስ አይወቀስ አይከሰስ" እንዲሉ ቀዳማዊ ኃይለስላሴን አስከማምለክ ድረስ የዘለቁበትን ልማዳዊ (ባህላዊ አኗኗር) ከቀረበው የቱሉ ጃርሳ ከባቢያዊ ሕዝባዊ ሎር መረዳት ይቻላል፡፡

## 21ኛ/"የቦረና ተራራው ሸለቆው ከዳከታ-ኤረር እና ጎበሌ ሸለቆ" (ክፍል2) በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

ይህ ፕሮግራም በሁለት ክፍሎች የቀረበና የተሻለ ትኩረት የተቸረው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ዘገባ በአመዛኙ ሀገረሰባዊ ልማድ የሚባለው የፎክሎር ዘውግ ተካቶበት ይስተዋላል፡፡ ጠቅላላ ዝርዝር ሀተታው ከፍሲል በተራ ቁጥር 20 ከቀረበው ፕሮግራም ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

በዚህ ታሪክ ውስጥ ሕዝባዊ ቦታን የተመለከተ ፎክሎር ተካቷል፡፡ የሰለሞን(2007፣299) መረጃ እንደሚያስረዳው አንድ ማሕብረሰብ በሚኖርበት አካባቢ ውስጥ ያለና የተለየ ማህበ ራዊ ዋጋ የሚሰጠው የሐገራዊ ውክልና ዘርፍ ነው፡፡ በታሪኩ መሰረትም የቀረበልን ሕዝባዊ ቦታ የዝሆኖች መጠለያ እንደመሆኑ መጠን ለጉብኝት ተመራጭንት ያለው ስለመሆኑ ሀተታው ያሳብቃል፡፡ እንዲሁም ለቦታው የተለየ መሆን አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ቁም ነገሮች መካከል ከተፈጥሮ በተቸረው ልዩ ጸጋ የተነሳ አስገራሚ ቅርጾች የሚታዩባቸው ድንጋዮች የሚገኙበት ቦታ መሆኑም ተወስቷል፡፡ በመሆኑም ጎብኝዎችንና ተመራማሪዎችን ጨምሮ የሚሰብ ልዩ ቦታ ተደርጎ እንደሚታይ የተጠናቀረው የቴሌቭዥን ዘገባው በውል ያስረዳል፡፡

## 22ኛ/"ከጮፈረ እስከ ድብቁ ፏፏቴ በጨበራ ጩሩጩራ ብሄራዊ ፓርክ"(ክፍል2) በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

ይህ ፕሮግራም በይደር የቆየና በክፍል ሁለት አንደገና በድጋሜ የቀረበ ሲሆን በይዘቱ ብዙ ጉዳዮች የተዳሰሱበት ነው፡፡ የተወሰኑትን በምሳሌነት እንመልከት የጭፈራ ሐይቅ በኢሰራ ወረዳ የሚገኝ ነው፡፡ ስፍራው ተአምር የሚባል ነው፡፡ ባህል ጠባቂው ደን መገኛ ነው፡፡

ይዘቱ የተራራ ላይ ደን፣የወንዝ ዳር ደን፤ሳር ለበስ ደንና የእንጨት ደን የሞላበት ስፍራ ነው።

ከእንስሳት ጉማሬ፣አዞ፣ዝሆን እና ልዩ ልዩ አዕዋፋት ዝርያ መገኛ ሲሆን‹‹ሰማይ ጭፈረ ላይ ይታያል›› ይባልለታል።

ይህ ቦታ 1410 እስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው፤እንዲሁም160 የእንጨት ዝርያ ደን ያለዉ ሲሆን ይህ ስፍራ በዳውሮና በኮንታ መካከል ይገኛል ።

ሌላው በዳውሮ ዞን በኩል ኤስራ ወረዳ እራሱን ዋሻ ጉያ ውስጥ የተደበቀ ፏፏቴ ይገኛል ። የውሃ ድምፅ እንደሙዚቃ የሚሰማበት ስፍራ መሆኑ በፕሮግራሙ ቀርቦ እናገኘዋለን ።

ይህ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ22፡07 ደቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን ፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል።

## 23ኛ/"ዘቢሞላ መስጂድ ታላቁ መካነ ቅርስ"(ክፍል 2) በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ።

ዘቢሞላ መስጅድ ታላቁ መካነ ቅርስ በሚል የዘገበው የፋና የቴሌብዥን ፕሮግራም በሁለት ዙር (በሁለት ክፍሎች )ተዘግቦ ለአድማጭ ተመልካች የቀረበ ነው። ዝርዝር ሀተታው ስመ ጥር ስለሆነው መስጅድ የሚያወሳ ነው። ስፍራው ለንጽህና ሲባል ያለ ጫማ የሚገባበት ስፍራ ነው። በረመዳን ፆም ወር በርካታ ሰው ይታደሙበታል። ከ 130 ዓመት በላይ እድሜ ያለው ሲሆን ከ1866 እስካሁን ያለ መስጂድ ነው። የሀድራው መስራች ሀጂ ስሩር በሽር ናቸው። የታሪካቸው መነሻ ስፍራ ከዋቤ ወንዝ ባሻገር ትንሿ መንደር ትልቅ ታሪክ የያዘች ናት። ኣቢናዝ የትምህርት እና የዳኝነት ስራ የሚከናወንበት ስፍራ ሲሆን፤ በረጃጅም ዛፎች የተፈጠሩት ከተማ ነው። መስጅዱ በነኢማም አነረጃሞ የታሪክ አሻራ የታተመበት ቦታ ወይም ስፍራ ነው። የመስጂዶቹ ስያሜዎች የአውራዎቹ ሰዎች ስም ነው። የታሪኩ መጀመሪያ ስፍራ ከገበሬ ወይም ዘቢሞላ ሀጂ መሀመድ አሚን ሀድራውን ይመሩታል ።

በአንድ ዋርካ ስር በረመዳን ወር ምእመናን ይቆያሉ። የሰው ልጅ ስርአት የሚታነፅበት ቦታ ነው።ስርዓትን፣ራስን፣ተፈጥሮ፣ፍቅርን፣መተሳሰብን፣ሰላም የሚካሄድበት ነው። በህብረት መፆም፤በህብረት መስራት የሚከናወንበት ስፍራ ነው። ነገር ግን በኮረና ምክንያት ግን የማይቋረጥ ተቋረጠ የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮችን ያነሳ ፕሮግራም ነው። በዚህ አይነት ሰፊ ዘገባ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ24፡48 ደቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን

ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ትውንጥበባት፣ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡በአጠቃላይ አራት የፎክሎር አይነቶች በዚህ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ስለመካተታቸው ከፍሲል የተመለከትነው ዘገባ በውል ያስገነዝባል፡፡

## 24ኛ/"የ400 ዓመቱ ባለጸጋው ልብስም ጉርስም የሆነው ጓሳ"(ክፍል1) በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

‹‹ጓሳ›› ልብሳችን፤ጉርሳችን ይላሉ የአካባቢው ማህበረሰቦች፡፡ የማህበረሰቡ ውርሳቸው መንዝ ጌራ ሰሜን ሸዋ ይገኛል፡፡ ጓሳ የሚጠቀሙበት 7008 ሄክታር ስፋት፤3200--3700 ከፍታ ስፍራ ላይ ያለ ነዉ፡፡ ጓሳ ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ለአራት መቶ ዓመታት በማህበረሰብ ሲጠብቅ የኖረ አሰቦ ና ጌራ የተባሉ ወንድማማቾች ለከብቶቻቸው ግጦሽ አመቺ በመሆኑ ሊጠቀሙበት ወስነው አስከብረውት የነበረ ስፍራ ነው፡፡ ከመንዝ ጌራ 20 ቀበሌዎች ያህል ሲጠቀሙበት 9 ገበሬ ማህበራትም ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ይህውም ሀገረሰባዊ እውቀት እውን የሆነበት ምድር፤ሰውና ተፈጥሮ ተስማምተው የሚኖሩበት፤እውቀትና ጥበብ ቁርኝት ፈጥረው ሀብት ሆኖ የኖረበት ስፍራ ነው፡፡

የእፅዋቱ ስብጥር ከ64 የሚበልጡ ልዩ ልዩ ዝርያዎችም ያሉበት ስፍራ ነው፡፡ የአይጥ ዝርያ ከ6 በላይ ይገኝበታል፡፡ የቀይ ቀበሮ መጠለያ ነው፡፡ ባለጸጋው ልብስም ጉርስም የሆነው ጓሳም ተጠቅሷል፡፡

ይህ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ25፡33 ደቂቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ትውንጥበባት፣ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡

የፎክሎር ዘውጎች በዚህ መልኩ ተዘግበው ከቀረቡበት አውድ መረዳት እንደሚቻለውና የመስኩ ጠበብቶችም በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳኑ ክፍል በቀረበው ሀተታ እንደሚያ ስረዱት ባህላዊ ህክምና መነሻው በየአካባቢው ከሚበቅሉ ዕጽዋት እምብዛም ዕውቀቱ በሌላቸውና ልምድን በማካበት ብቻ ተፈጥሮን ታግለው ይኖሩ በነበሩ ማንበብና መጻፍም በማይችሉ የገጠር ሰዎች አማካኝነት ነበር፡፡ ለባህላዊው ህክምና በመፍትሄነት ከሚያገለግሉ ልዩልዩ የእጽዋቶች ስብጥር በተጨማሪ አንስሳትም እንደሚገኙበትም አመላካች የሆነው ከላይ የቀረበው የቴሌቭዥን ዘገባ ያስረዳል፡፡ በአጭሩ በህክምናው ዘርፍ ዛሬ ለተደረሰበት ዕውቀት መነሻው ባህላዊው የህክምና ዘርፍ ስለመሆኑ በቀጥታም ይባል በተዘዋዋሪ ከፍሲል በቀረበው ሀተታ ተገልጽዋል፡፡

## 25/ኛ"ልብስም ጉርስም የሆነው ጓሳ"(ክፍል2)በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

በዚህ ለሁለተኛ ጊዜ በተዘገበው ይዘትም የታየው ፕሮግራም በክፍል አንድ ከቀረበው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የወሰደው ደቂቃ 25:33 ሲሆን በድጋሜ መቅረቡ በፋና ቴሌቭዥን ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የተሰጣቸውን ትኩረት ከፍተኛነትና ፎክሎሮችም የዘገባ ምንጭ በመሆን በቴሌቭዥን ይዘትነት ተካተው ወደ ሰፊው ማህበረሰብ የሚተዋወቁበትን አጋጣሚ እናስተውላለን፡፡

## 26/ኛ"ደብረሲና ማርያም ቤተ-ክርስቲያን ጎርጎራ ጣና ሀይቅ"በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

ጎርጎራ ጣና ሀይቅ በ16ኛ ክፍለ ዘመን የነገስታት መናገሻ የጣና ዳርቻዋ ቀደምት ከተማ ስትሆን፤ጎርጎራ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተገደመች ናት፡፡ ደብረሲና ማርያም ገዳም ከባህርዳር 78 ኪ.ሜ በውሀ ተጉዘው ያገኙታል፡፡

ደብሯ ከጣራው እድሳት በቀር እንደነበረች ናት፡፡ በመሆኑም በብዙዎች የተወደሰ ነው፡፡ ሳር መልበሷ መገለጫዋ ነው፡፡ የፈጣሪ ፈቃድ በመሆኑ ይች ደብር እስከ ምዕአት ቆርቆሮ አትለ ብስም፡፡በአፄ አምደ ፂኦን የተገነባች ሲሆን፤አራት ሽፍቶችን ለመግጠም በመጣዉ ኤስድሮስ የተባለው አዛዥ ጎርጎሪኦስን አሸነፈ፡፡ስፍራውም ጎርጎራ ተባለ፡፡ ከሸዋ የመጣው ደብረሲና የተተከለ ችሲሆን፤የግድግዳ ስዕሎቹ ድንቅ ናቸው፡፡የወርቃማው ዘመን ስዕሎች በነበሩበት የምህንድስና ጥበብ የተሰሩ ናቸው፡፡

በእትጌመለኮት እንደተሠሩ የቤተ ክርስያኒቱ ታሪክ ይናገራል፡፡ 5ቱ መስኮቶችና 3ቱ በሮች የኪነ ህንፃው መገለጫዎች ናቸው፡፡ የመስኮቶቹ አሰራር ጥበብ ይታይበታል፡፡

ፕሮግራሙም የክብረ በዓላቱን ከዋዜማ ጀምሮ ይተርካሉ፡፡ዝግጅቱን፣መዝሙሩን፣ቅኔ ማህ ሌቱን፣ወረቡን፣ያሬዳዊ ዜማን፣የቀንና የሌሊት ትእይንትን ይተርካል፡፡

ይህ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ23:07 ደቃዎች ሽፋን ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ትውንጥበባት፣ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡

እነዚህ አራቱን የፎክሎር ዘውጎች ተካትተው በዘገባው የቀረቡ ፎክሎሮች በዚህ አግባብ በፋና ቴሌቭዥን መዘገባቸው ጣቢያውን አውቅና እና ዝና እንዲኖረው ከማስቻል ጀምሮ ሎሮችን ለሕዝብ በማስተዋወቅ፣በማህበረሰብ ባህል ውስጥ ያሉ ቁምነገሮችን (ጭብጦችን)በማስረዳት፣

ጎብኝዎችን ከመቀስቀስ፣የዘርፉን ተመራማሪዎች ከማነሳሳት፣የሃገርን ማንነት እንደ መስታ ዎት አንጸባርቆ ከማሳየት አንጻር የሚኖራቸው ፋይዳ በእጅጉ ከፍ ያለ ነው፡፡

**27ኛ/"አቡነ ሙሴ ገዳም"በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡**

ከወልዲያ 196 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኘው ኩርባ የወረዳ ዋና ከተማ ስትሆን፤ስያሜዋ ዳሞት ከሚለው የመጣ ነው፡፡ስያሜው ዳዊት ሁሉም ታሳያለች ዳሞትን ትመስላለች እንደ ማለት ነው፡፡ ጨት አምባ ያለውን ገብርኤልን መሰረት አድርጎ የዳዊት ሞትን ትመስላለች ካለው ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በአብርሃ ወአፅብሀ ዘመን የተፈለፈሉ ቀበሌ 011 የሚባል አካባቢ፤ጋርሳ የድባ ጎጥ ይባላል፡፡ የድባ መቅደስ ሙሴ አንድነት ገዳም ድባ የተባለው የድብ እንስሳ በቦታው ስለነበረ ነው፡፡ መቅደሰ ማርያም የተባለው የማርያም ቃል ኪዳን ታቦት መገኛ ቦታም ነው፡፡በ4ኛው መቶ/ክ ዘመን ይህን ውቅር ቤተክርስቲያን መስራች አቡነ ሙሴ ነበሩ፡፡ የገዳሙም መስራች አቡነ ሙሴ ናቸው፡፡ 1600 ዓመት ያስቆጠረ የወይኑ ታምር ሲሰራ ተካፋይ የነበሩት ሁለተኛው ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ሙሴ ስለመሆናቸው በዘገባው ተገልጽዋል፡፡

ቤተ-ክርስቲያኑ የህንፃ ጥበብ ያለው አቡነ ጀዲ በአለቱ ላይ የተሳሉ ስእሎች፤በሩ ከእየ ሩሳሌም በንፋስ ሰረገላ ተጭኖ እንደመጣ ይነገራል፡፡ 1600 ዓመት ያስቆጠረ በር ነው፡፡ የውስጡ ምሰሶች፤ከ360 በላይ በግድግዳ ላይ የተሳሉ ስዕሎችም የያዘነው፡፡የውቅሩ ውስጥ መተላለፊያዎቹ የፎቅ ላይ መሄጃዎች የሚመስሉ ናቸው፡፡

ይህ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም የ20፡44 ደቃዎች ሽፋን ያገኘ ሲሆን ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮ ግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡

ከላይ በቀረበው የፕሮግራም ዘገባ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በዘገባው ውስጥ ተካትተው መቅረባቸው ለቴሌቭዥን ፕሮግራሙ ተደማጭነትንና ተወዳጅነትን ብሎም ተመራጭነትን የሚያስገኙለት ሲሆን፤በአንጻሩ ለቴሌቭዥኑ ፕሮግራም ታዳሚዎች ደግሞ የፕሮሞሽን ተግባርን እንዲሁም ባህልን ከማስተማር፤ስለባህል ከመስበክ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ባህልን የማክበር፤የመጠበቅ፤ለተተኪው ትውልድ የማሸጋገር፤የተሻሉ ግንዛቤዎችን የመፍጠር ፋይዳ ዎችን የማስገኘት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

## 28ኛ/"የታደለው የቦረና ብሄራዊ ፓርክ"በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

ከአዲስ አበባ ምስ 570 ኪ.ሜትር ርቀት ያቤሎ ከተማ ይገኛል፡፡ፓርኩ የሜዳ አህያ፣ሰጎን፣ አጋዘን እና አእዋፍ ዝርያ መናሀሪያ ነው፡፡ ጨው ቤት የሚባለው የጨው ኩሬ መገኛ ስፍራ ነው፡፡

በአፈ-ታሪክ ከ600 ዓመት በፊት ታሪክ እንደ ነበር ይነገራል፡፡በሌላም በኩል በሳተገሞራ የተፈጠረ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ24:46 ደቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ፎክሎሮቹ የሚኖራቸውን ፋይዳ በተመለከተም የቀረበው አፈታሪካዊ ፎክሎር በተጠቀሰው ዘመንና ወቅት ተከሰተ ተብሎ በዘገባው ለቀረበው ታሪክ ወይም ጉዳይ ፎክሎር አንዱ መልስ የሚገኝበት ማህበረ-ባህላዊ ዕውቀት መሆኑን ያሳያል፤በሌላ በኩል በዚህ መነሻ የዘርፉ ተመራማሪዎችም ጥናት እንዲያካሂዱበት ያነሳሳል፡፡

## 29ኛ"የሼህ አሊ መካነቅርስ መቃብር ጎንደር"በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡

ስፍራው ከአ.አ 748 ኪ.ሜ ላይ ይገኛል፡፡ 5560 የቆዳ ስፋት ላይ ሰፍሮ የሚገኝ  በጎንደር ሰሜን ኢትዮጵያ  ግዙፍ ገበያ ወይም ቅዳሜ ገበያ መገኛም ነው፡፡በታሪክ  ጎድጓዲት  ትባል እንደነበረም ነበር፡፡ በኋላም አዲስ አለም ተባለች፡፡ የወጪናገቢ ነጋዴዎች መቀመጫም ናት፡፡ ሦስት ጊዜ ፈርሶ የተሰረዉ መስጊድ የአዲስአለም መስኪድ መጀመርያ በጻድቁ ዮሐንስ ዘመን የዛሬ 344 ዓመት ተተከለ፡፡ ሼህ አሊ ወሎ ተወልደው የጎንደር መጠሪያ የሆኑ ናቸው፡፡ ወሎ፣ወረኢሉ፣ደብረሲና ተወለዱ፡፡ ሼህ አሊ በፍልስፍና ይታወቃሉ፤መፅሀፍም ፅፈዋል፤ ገጣሚም ናቸው፡፡ ስነ-ልቦናቸው ኢትዮጵያዊ ነው፡፡የታላቁ አሊም የሼህ አሊ ጎንደር ታሪክ ብዙ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ውጭ ሳይቀር ለትምህርት ግብፅ ለ5 ዓመታት ሲቀመጡ ያስተምሩ ነበር፡፡ የመምህሩ ያኔም እውቀትን አብልጠው በመራብ ይነሳሉ፡፡ ሼሁ ጎንደርን ሦስት ጊዜ እንደረገጡ ይነገራል፡፡ አባታቸው ሙሳ ሰኢድ መሀመድ ኑሪ እናታቸው እመት ፋጡማ የሱፍ ናቸው ፡፡ ሼሁ ወሎ ተወልደው ጎንደርን ያስከበሩ ናቸው፡፡

የቃ ወንዝ ዳርቻ በትላልቅ ዛፎች የተከበበች ናት፡፡ የአእዋፍ ዝማሪ የሚሰማባት ስፍራ፡፡ሼሁ 450 ከተሞችን ጎብኝተዋል፡፡ይህን የገለፁበት የግጥም መድብል ‹‹አይፊያ›› የተባለ አዘጋጅተዋል፡፡313 ስንኞች ባሉት ግጥም ከተማዎችን ጠቅሰዋቸዋል፡፡ የአለም ካርታ አዘጋጅተዋል፡፡ ከሁለት መቶ ዓመት በፊት መሬት ስምንት አቅጣጫ አላት ያሉ ናቸው፡፡

ስፍራው የጥሞና ስፍራ ነው፡፡ 1851 ዓመት ሂጅራ ወደ አሄራ ሄዱ ይላል ታሪካቸው፡፡ስፍ ራውን ወይራው፣ዋርካውና ፅዱ አጅቦታል፡፡

በ1904 ያረፉት ሀጂ መሀመድ ሰይድ የጎንደሩ፤1910 ያረፉት ሼህ መሀመድ ራያ በመካነ መቃብሩ ይገኛል፡፡ ስፍራው የበረከት ቦታ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ከዓመት ዓመት እህል አይጠፋም፡፡የእርቅ አባት ይባላሉ፡፡ በዘመነ መሳፍንት አጼቴዎድሮስ እና ራስ አሊ ሲጣሉ አስታራቂ እንደነበሩም ከቀረበው ዘገባ እንረዳልን ፡፡

ይህ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ23፡43 ደቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡

**30ኛ/ "ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ"(ክፍል 2) በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡**

ፕሮግራሙ ቀጥሎ በቀረቡት ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡ ስፍራው ከአንድ ሺ በላይ የእፅዋት ዝርያ ያለው ፓርክ ነው፡፡ ጫሞና አባያን ሀይቅ ያማከለ ነው፡፡ በጫሞና አባይ ሀይቅ መካከል የሚገኝ ነው፡፡ የጫሞ ሀይቅና አባያ ሐይቅን የሚለየው የመሬት ስፍራ ነው፡፡ ስፍራው የተንጣለለ እና አራት ኪሎ ሜትር አለው፡፡ከአርባ ምንጭ 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል ፡፡ ስፍራው የአዞም ገበያ መገኛ ስፍራን የያዘ ነው፡፡

በ23፡12 ደቂቃዎች በፕሮግራሙ የፓርኩን ይዞታና በውስጡ የያዛቸውን ሀብቶች የሚያስቃኝ ፕሮግራም ነው፡፡ በመሆኑም አንድም ፎክሎራዊ ጉዳይ አልተነሳበትም፡፡

**31ኛ/"ከምንት ዋብ-ቁስቋም ጎንደር"(ክፍል1)በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ፡፡**

የአዲሳ አበባ 748 ኪሎ ሜትር የምትርቀው ጎንደር፡፡ የወርቃማው ትውልድ አሻራ መገኛ የሆነው የፋሲል ጊቢ ስድስት ቤተመንግስቶች አሉት፡፡

አንደኛ አፄ ፋሲል፣ሁለተኛ ልጃቸው አላፍ ሰገድ፣ሦስት አድያም ሰገድ ኢያሱ (የአጼ ፋሲል የልጅ ልጅ) ፣አራተኛ አፄዳዊት፣አምስተኛ አፄ በካፋ፣6ኛ የእትየ ምንትዋብ ይጠቀሳሉ፡፡ አፄ በካፋ ቋራ ለጉብኝት በሄዱበት ወባ ይዘዋቸው፡፡ንጉሱን እንድታስታምም የተደረገችው ብርሃነ ሞገስን ሲያገቧት ምንትዋብ ብለው አገቧቸው፡፡ ሲሞቱ የቋራው እያሱ (ልጅዋ) መንገስ ስለማይችል እተጌ ምንትዋብ ተብላ ነገሰች፡፡

የግቢው ቤተ መንግስት አሰራር ጥበብ የተለያየ ነው።እትጌ በቤተ መንግቷ በቆየችባቸው 16 ዓመት ገዝታለች።እያሱ ሲያድግ ደግሞ ከግቢው እንድትወጣ እንደተደረገች የፋና ቴሌቭዥን በዘገባው አብራርቷል። እናትን እንኮዬ አባት ደጃዝማች መንበር ቋራ ላይ ወለተ ጊዮርጊስን የኋላ እቴጌ ምንትዋብ ተወለዱ።የቤተ መንግስቱ በሮችና መስኮቶች የጎንደር መስቀል ነው። አንድ የጎንደር ቅርፅ፣2 የላሊበላ ቅርፅ እና የአክሱም ቅርፅ ይጠቀሳሉ። በውስጡም ያሉት ስዕሎች አቡነ ሳሙኤል ፈረስ እየጋለቡና የአቡነ ዮሐንስ ስዕሎች ይጠቀሳሉ። በርና መስኮቶቹ የጎንደር መስቀል ቅርጽ ያላቸው ናቸው።

እቴጌ ምንትዋብ ቆንጆና ፈታይ ሴት ናቸው።በግቢው ውስጥ ፈትል ግንብ የምትባል ቤት አለች።እቴጌ ምንትዋብ ቆንጆ መሆናቸው እና ሙያ ያላት ናት ለማለት ‹‹የዶሮ አሰራርና የንቅሳትን ጥበብ ያስተማረች ናት›› በሚል ይወሳሉ።

የዶሮ አሰራርና የንቅሳት ጥበብ ትችላለች። የዶሮ አሰራር በሰነዶች እንዴት እንደሚሰሩ ያስተ ማረች ናት።ጀምስ ብሩስ በምንትዋብ ዘመን የነበረ ሲሆን የአባይ ምንጭን ለማጥናት የመጣ  ቢሆንም በቤተ-ክርስቲያንና በቤተ-መንግሰት ለአምስት ዓመታት ኖረዋል።ስለ እቴጌ ምንት ዋብም በስፋት ፅፏል።

ይህ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ27:08 ደቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑ ትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስ ተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል።

**32ኛ/“ድብቁ ውቅር ቅርስ ዞዝ አምባ ጊዮርጊስ”በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንታኔ።**

በለሳ በምስራቅ አማራ ክልል ጎንደር ዞዝ የሚገኝ ስፍራ ሲሆን፤"ዞዝ" ማለት ዕዞት ወይም በትዕዛዝ የመጣ ማለት ነው። በአፈ ታሪክ  ዞዝ አምባ ላሊበላን ያነፀው ነው ይባላል። ሰምዓቱ ጊዮርጊስ በፈረሱ የወጣበት ዳና ያለበት እና የሚታመንበት ስፍራ ነው። በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሰሩት ላለቀ ዋሻ የተጀማመረ ዋሻ ነው። ይህም የመነኮሳት ቀብር ነው።

አቡነ አብሳዲ የተባሉና 444 መነኮሳት በአንበሳ፣በነብር፣በዝሆን ከአቡነ ሳሙኤል ጋር ተጭ ነው ወደ ስፍራው እንደመጡና በዞዝ አምባ ላይ በኖሩበት ጊዜ እንደተገኘ ይነገራል።ከ11ዱ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ተመሳሳይነት የሚታይበት ሲሆን፤ የሚለየው ቀድሞ መስራቱ

ነው፡፡ መስኮቶች በምክንያት፣ለውበትና ለመልእክት የተመቹ ናቸው፡፡የቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ቅድስት አለው፡፡ ምሶሶዎቹ ከሌላ ቦታ መተው የተተከሉ ይመስላል፡፡ መቼታነፀ የሚለውን ግን ፕሮግራሙ አይናገርም፡፡

ይህ የቀረበው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በ23፡53 ደቃዎች ሲቀርብ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች በፕሮግራሙ ተነስተው ለተመልካቾቹ ቀርበዋል፡፡ የነዚህ ልዩልዩ ፎክሎሮች ማለትም ቁሳዊ ሃብቶች፣ አፈ-ታሪኮች፣ ሀገረሰባ ምህንድስናን የተመለከቱ ዘገባዎች በቴሌቭዥን ፕሮግራሞች መካተት የራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ይኼውም ማህበረሰቡ ስለባህሉ ያለውን ግንዛቤ በሚፈለገው መጠን ለማሳደግ፣አካባቢያዊ ማንነትን ሕዝባዊ ማንነትንና ሃገራዊ ማንነትን ለማንጸባረቅ፣የታሪክ ጭብጥን ለማመላከት፣ልማዳዊ ባህላዊ መገለጫዎች ትኩረት እንዲቸራቸውና እንዲጠኑ ለማስቻል ይጠቅማሉ፡፡

የ “ጉዞ ኢዮጵያ “ፊልሞችን ይዘትና ከፊልሞቹ የሚገኝ ፋይዳን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ. ቁ | በፋና ቴሌቪዥን “ጉዞ ኢትዮጵያ “ፕሮግራም ላይ የቀረቡ | የቀረበው ፕሮግራም ይዘት ምሳሌዎች | ከቀረቡት ፕሮግራሞች የሚገኝ ፋይዳ |
|---|---|---|---|
| 1 | “የተሰወረው ቅዱስ ጽዋ፣ አምስቱ ጽዋዎች የተሠወሩበት ቦታ” | መንፈሳዊና ቁሳዊ የሆኑ ጥንታዊ ቅርሶች፤ህማመሥጋ ያለበት~ ህማመ ነፍስ ያለበት ፈውስ የሚገኝበት፤ከስነ-ቃል (አፈ-ታሪክ)፣ከሀገረሰባዊ ልማድ (የሃይማኖትና የእምነት)ተዘግበዋል ፡፡ | ባህልን ከማቆየትታሪክ ከማስተላለፍ፤ ከመንፈሳዊነት&የመትከል፤ የአለባበስ፤ከቱሪዝም፤ ታሪካዊውናዘመንተሻጋሪው፤ አፈ ታሪክን፤ዕውቀት ፤ተመራማሪዎችን የመጋበዝ፤የመስበክን፤ባህልን ከማቆየት የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 2 | “ምርቃት/መመረቅ/ሀገረሰ ባዊ ዕውቀት” | የሀገር በቀል ዕውቀት ከተፈጥሮ ጋር ተናቦ የኖሩበት፤ቀበሌዎች በዛፍ ስም መጠራታቸው፤ልዩልዩ ስያሜዎችና ሃገር በቀል ዕውቀቶች ተዘግበዋል ፡፡ | ከቱሪዝም ተመራማሪዎችን የመጋበዝ ፣ ያደፋፍራል፤ያነሳሳል፤ የታዳሚንቀልብ ይይዛል ፤ተመለተ ካቾች ወደራሳቸው ባህልና ዕውቀት፤ ልማድ፣እሴትእንዲያስቡ ብሎም የፎክሎር ፍላጎት እንዲኖራቸውም ከማዳርጋል የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 3 | ”ከተራን ሸንኮራ ኡራን ቡቲ ጥምቀትየታቦታት አሸኛኘትን (ክዋኔ)“ | ባህላዊ ጨዋታ እና ጭፈራ&ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን አካቷል፡፡ የማሃበረሰቡን ሃይማኖት፣ ባህል፣እምነትና ስነ-ቃል (በከተራና በጥምቀት ተቦታት የካህናቱ ሽብሸባ፣ የምዕመናኑ ሐገረሰባዊ ሙዚቃ)፣ ቁሳዊ ባህል (ሐገረሰባዊ ልብስ የሚታጀቡባቸው ባህላዊ ዘፈኖች የጭፈራ ክዋኔዎች)፣ ሐገረሰባዊ ልማድ(የጥምቀት፣ሐገረሰባዊ ጨዋታና | ከቱሪዝም&ከመንፈሳዊነት&ከመንፈሳ ዊነት፤ ተመራማሪዎችን የመጋበዝ&ስነ-ምግባራትን ያስተምራሉ የአለባበአ&የመትከል ተግባር&የማረጋገጥ፣የማፅደቅ፣ባህልን ከማቆየት የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ክብረበዓል)፣ሐገረሰባዊ ትውን ጥበብ (የጥምቀት በዓል የሙዚቃ መሳሪያ ለምሳሌ የካህናት ከበሮና ጽናጽል) ይጠቀሳሉ፡፡ | ፤ታሪክ ከማስተላለፍ&ጨዋታና ክብረ በዓል&ክዋኔዎች&የባለቤትነትና የማሕበረሰብ ስሜት ለመፍጠር፤ ባህልን ከማቆየት የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 4 | ”የውቅር አቢያተ ክርስቲያኑ የግድግዳ ስዕሎች“ | ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህልናእንዲሁም ሥነ-ቃላዊ አፈ-ታሪክ ተዘግበዋል፡፡ | ማህበረሰቡ ባህሉን አጠንክሮ እንዲጠብቅና ለትውልድ እንዲያስተላልፍከማቆየት የታሪክ ከማስተላለፍ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 5 | “በዕውቀትና በእምነት ከፍ ብየሚኖሩበት ስፍራ” | የያሬድን ጥኡመ ዜማ ስትሰማ ለሁለት የከፈለች ዛፍ፤ፅናፅል፣ መቋቋሚያ፣ የአቡነ አረጋዊ ትዕምርተ መስቀል እና መቋሚያ፣ የፊታውራሪ ጎሹ ሰይፍ እና የአፄ ቴዎድሮስ መታጠቢያ ሳህን፤ በማይዳሰሱ ቅርሶች እና በሚዳሰሱ ቅርሶች የታደለች ፤ስነ-ቃላዊ ፣ሀገረሰባዊ ትውንጥበባትን፣ ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል፡፡ | ተመልካቾች ወደራሳቸው ባህልና እምነት እንዲመለከቱ ጊዜ ወስደው እንዲያስቡ<br>ባህላዊ እምነቶችንና እሴቶችን ህልውና ጠብቆ ለማሻገር ፤ ከቱሪዝም፣ከመንፈሳዊነ ት፣ ከመንፈሳዊነት፣ተመራማሪዎችን የመጋበዝ፤ ባህልንከማቆየት ታሪክ ከማስተላለፍ፤በዓል&ክዋኔዎች፣ የባለቤትነትና የማሕበረሰብ ስሜት ከመፍጠር የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 6 | ”ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህል“ | በቁሳዊ ሀብትነት ጋሻ፣ጭራ፣ዋንጫና ሰውሰራሽ ተዘገበዋል። | ፎክሎር ዘርፍ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች፣ጥናትና ምርምር ያካሂዱ፣መነሻ ምክንያት በመሆን፣ ከቱሪዝም፣ ታሪክ ከማስተላለፍ |
| 7 | ”አፈ-ታሪክ ያለበት ስፍራ” | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን እንዲሁም የሥነ-ቃል፣ አፈ ታሪክን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | በዘመኑ የነበረውን ለአዲሱ ትውልድ በማስተዋወቅ በቅርስ ጥበቃና ክብካቤ ተግባር ሰፊው ማህበረሰብ አንዲሳተፍ የመቀስቀስ፣የማሕበረሰብ ስሜት ከመፍጠር የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 8 | ”በጨበራጨርጨራ አካባቢ“ | ሀገረሰባዊ ትውንጥበባት፣ስነ-ቃልን፣ ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች ሳይነሱ አካባቢያዊ ናስነ-ምህዳራዊ የተመለከቱተዘግበዋል፡፡ | ለቱሪስት መስህብነት በማስተዋወቅ ረገድ የመቀስቀሻ ሎር ሆኖ ያገለግላል፡፡ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 9 | ”ቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ” | ሀገረሰባዊ ልማድ የተመለከተ ጉዳይ በፕሮግራሙ በጥቂቱ ተነስቶ ሀገረሰባዊ ምግብና መጠጥ እንዲሁም ሕዝባዊ ቦታ የተመለከቱ ተዘግበዋል፡፡ | ለቱሪስት መስህብነት ማስተዋወቅ |
| 10 | “ጋራይሌ ብሄራዊ ፓርክ” | የገሬ ጎሳ እሴት የሚጠብቀው ስፍራ ነው፡፡ሕዝባዊ ቦታን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ለቱሪስት መስህብነት፤እንዲንከባከብ የማሳሰብ፣ከተማሪዎችና ከተመራማሪዎች የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 11 | ”የተሰወረው ጽዋ መገኛ ስፍራ“ | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ለቱሪስት መስህብነት፤ተማሪዎችና ተመራማሪዎች፤በቅርስ ጥበቃና ክብካቤ ተግባር ማህበረሰብ አንሳተፍ ከመቀስቀስ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 12 | ”የብልባላ ውቅችሮ“ | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ለማህበራዊ ጉዳዮች መደጎሚያ የገቢ ምንጭም መሆን እንደሚችል፤ሥነ-ቃሎች ፣ሀገረሰባዊ ልማዶችና ቁሳዊ ባህሎች ባለቤት ሆኖመገኘት ታላቅ የኩራት ምንጭ ስለመሆኑ ከማስተማር የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 13 | ”ዘቢሞላ መስጂድ መካነ ቅርስ“ | አባጅፋር ስጦታዎች፣ የቆዩ ደብዳቤዎች፣ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች እና እስላማዊ የፅሁፍ ቅርሶች የሚገኙ በት፤ ስነ-ቃል፣ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህል መንፈሳዊ ቅርሶች፣ባህላዊ የህክምና ዘዴዎች የተመለከቱ ተዘግበዋል ። | ሃይማኖታዊ እሴቱን ተቀብሎ ለተተኪው ትውልድማስቀጠል፤ እንዲታወቅናለጉብኝትም እንዲታጭ ያደርጉታል፤የባህላዊ ህክምና ትው ውቅንም ይፈጥራሉ፡የማስተማር ፤ ወደ ራሳቸው ባህልና እምነት እንዲ መለከቱ ጊዜ ወስደው እንዲ ያስቡ ባህላዊ እምነቶችንና እሴቶችን ህልውና ጠብቆ ከማሻገር የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 14 | “የቡና ጫከ የሸፈነው የጌዲኦ ትክል ድንጋዮች“ | በሰውነት፣የሰው ፊት፣በወንድ ብልት የተቀረፁ ድንጋዮች ይገኙበታል፡፡ የመቃብር ስፍራ ክምችቶች ፤ስነ-ቃልን፣ ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል ። | አፈታሪኮችን ለመፍጠርናለማስቀጠል፣ባህላዊ እምነቶችንና እሴቶችን እንዲሁም ልምዶችን ለማስጠበቅ፤የማንነት ስሜትን የመፍጠር ፤ ማህበረሰቦች ስለባህላቸው ተጨባጭ መረጃ ዎችን ለማቅረብ፣የታሪክ ነገራ ጭብጦችን በቀላሉ ማስረዳት የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 15 | “ከጋራ ዱላ ጋራ ሰልፍ አድዋን ፍለጋ” | ከአድዋ መልስ በዘመኑ አርበኞች የተቆረ ቆረች ከተማ ናት፡፡ አካባቢው በፊልም ፣ በሙዚቃ እና በእርከን ሥራይታወቃል ፡ ፡ የጋራዱላ ጊዮርጊስ ቅርሶች፤ የብራና መጽሐፍት ፤ የብር መስቀሎች፣ ሰው በመሆኑ ብቻ የሚኖርበትፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑትን ስነ -ቃልን ፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል ። | ባህላዊ ሥያሜዎችን ከነፍቻቸው የማስተዋወቅ፣ቁሳዊ ባህሎችን(ብራና መጻህፍት፣የብር መስቀል በማስተ ዋወቅ ቱሪዝምን ለመሳደግ፣ የሀብታ ቸውን አይነትና ደረጃ ልብ ብለው ለማያውቁ የፎክሎር ባለቤቶች በማስ ተዋወቅ ማንነታቸውን በውል እንዲ ረዱ የማስቻል ሚና፤ሰው በመሆኑ ብቻ ከሚኖርበት የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 16 | ”የቆርኪዎች መጠለያ ሰንቀሌ ብሄራዊ ፓርክ“ | ፎክሎራዊ ጉዳዮች በፕሮግራሙ በሚገባ ሳይነሱ የቀሩበት ። | ፕሮግራሙ ሳቢነት የጎደለውና ተራ ማስታወቂያ መስሎ እንዲታይ አድርጎታል፡ |
| 17 | ”የፈውስ ተራራው ሚስጥር” | ባህላዊ መድሀኒት የሚለቀምበት ጊዜን የሚያስቃኝ ነው፡፡ ሀገረሰባዊ መድሃኒት፣ ስነ-ቃል (ሕብረዝማሬ)፣ሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህልን፤ የተመለከቱ ተዘግበዋል ። | የሎር ባለቤቶች ስለ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብቶቻቸው በማወቅና በመረዳት ሊደረጉ የሚገቡ ጥበቃዎችንና ለቀጣይ ተውልድ ለማስተላፍ የሚችሉ ባቸውን መንገዶች የተረዱ ወገኖች ጥበቃ ያደርጉላቸዋል፡፡የቅርሶቻቸውን ብዛትና አይነት በመመርመር ቅርሶች እንዳይሸጡ፤ እንዳይለወጡ የሚደረጉበት፤በማስተዋወቅ ቱሪዝምን ከመሳደግ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 18 | ”ጉንዳ ጉንዶ ከግዙፉ ተራራ እግርጌ“ | የሮብ ማህበረሰብን የቤት ግንባታ አሠራርን የምናይበት፤ታሪካዊ ኪነ ህንፃ ቤቶቹ፤ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተነባብሮ የተሰራ ኪነ ህንፃ፤ በፅሁፍ ቅርስ እና በክምችትና በማቆየት ፤ጥንታ ዊመስቀሎች፣ዘውዶች፣ፅዋዎች፣ፅናፅሎች ፣ወዘተ መገኛ ሲሆን ያስተርዮ በዓል አከባበር፤ከሃገራዊ ልማድ ውስጥ ባህላዊ ህክምና፣ ሕዝባዊ ሁነት፣ ክብረ በዓል፣ | ማህበረሰቡን የማንቃትና የማስተማር ሚናን ሚናን ይጫወታሉ፡፡ በፎክሎር ዘርፍ ለአጥኝዎች መረጃ ይደርስ ዘንድ ምክንያት ይሆናሉ በልምድና በተግባራዊ ድግግሞሽ የዳበረ ዕዉቀትን የመግለጥ፤ በማስተዋወቅ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ስርአተ ከበራ፤ እንዲሁም ከሃገራዊ ትውንጥበባት የአስተርዮ ንግስ ሽብሸባዎች፣ከቁሳዊ ባህል ደግሞ ከጥርብ ድንጋይ የተሰሩ ሀገረሰባዊ ምህንድስናን የተላበሱ ቤቶች የተስተዋለበት የቤት ግንባታ ከሥነ-ቃል ደግሞ የአባቶች ምስጋናና  የጥር አስተርዮ ማርያም የባህላዊ የዘፈን ግጥሞችን እናገኛለን፡፡ | ቱሪዝምን ከመሳደግ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 19 | “የሰንቀሌ ቆርኪ.ዎች መጠለያ ብሄራዊ ፓርክ” | ቆርኪዎች መገኛን የተመለከተ ባህል የታደገቻቸውን እንስሳት የሚያስቃኝ ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮች፤ሀገረሰባዊ ልማድን በተመለከተ የአባገዳዎች ሥነ-ስርአት፤ እንስሳትን የማክበር፤ የመጠበቅ ባህል ከሰው እኩል የመቁጠር ዲሞካራሲያዊ ባህል የአካባቢው መገለጫ ሎር ሆነው ቀርበዋል፡፡ | ባህላዊ ዳኝነትን የማስረጽ ሚና ዲሞክራሲያዊ አኗኗርን የማለማመድ ሚናም ፤ በማስተዋወቅ ቱሪዝምን ለማሳደግ፣ በፎክሎር ዘርፍ ከአጥኝዎች የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 20 | ”የቦረና ተራራው ሸለቆው ከዳከታ-ኤረር እና ጎበሌ ሸለቆ“ | ባቢሌ የዝሆኖች መጠለያ ፤ሀገረሰባዊ ልማድን  ቀዳማዊ ኃይለስላሴን አስከማምለክ ድረስ የዘለቁበትን ልማዳዊ (ባህላዊ አኗኗር) ከቀረበው የቱሉ ጃርሳ ከባቢያዊ የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ከታሪክ ከማስተላለፍ፤ ከቱሪዝም፤ ለአጥኝዎች ባህልን ከማቆየት፤ በዘመኑ የነበረውን ለአዲሱ ትውልድ ከማስተዋወቅ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 21 | “የቦረና ተራራው ሸለቆው ከዳከታ-ኤረር እና ጎበሌ ሸለቆ” | ሀገረሰባዊ ልማድ የሚባለው የፎክሎር ዘውግ ተካቶበት ይስተዋላል፤ሕዝባዊ ቦታን የተመለከተ ፎክሎር ተካቷል፡፡ | ጎብኝዎችንና ተመራማሪዎችን፤ ባህልን ከማቆየት፤ለአዲሱ ትውልድ ከማስተዋወቅ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 22 | ”ከጮፈረ እስከ ድብቁ ፏፏቴ በጨበራ ጨሩ ጨራ ብሄራዊ ፓርክ“ | ስነ-ቃልን ፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ከታሪክ ከማስተላለፍ፤ ከቱሪዝም፤ ለአጥኝዎች ባህልን ከማቆየት፤ በዘመኑ የነበረውን ለአዲሱ ትውልድ ከማስተዋወቅ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 23 | “ዘቢሞላ መስጂድ ታላቁ መካነ ቅርስ” | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ፣ ሀገረሰ ባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ፤ደብዳቤዎች፣ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች እና እስላማዊ የፅሁፍ ቅርሶች የሚገኙ በት፤ስነ-ቃል፣ሀገረሰባዊ ልማድ የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ሃይማኖታዊ እሴቱን ተቀብሎ ለተተኪው ትውልድ ማስቀጠል፤ እንዲታወቅና ለጉብኝትም የባህላዊ ህክምና ትውውቅንም ይፈጥራሉ፡፡ የማስተማር፤ ወደ ራሳቸው ባህልናእምነት እንዲመለከቱ እንዲያስቡ ባህላዊ እምነቶ ችንና እሴቶችን ህልውና ጠብቆ ለማሻገር |
| 24 | “የ400 ዓመቱ ባለጸጋው ልብስም ጉርስም የሆነው ጓሳ“ | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ትውንጥበባት፣ ሀገረሰባዊ  ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል ። | ከታሪክ ከማስተላለፍ፤ ከቱሪዝም፤ ለአጥኝዎች ባህልን ከማቆየት፤ በዘመኑ የነበረውን ለአዲሱ ትውልድ ከስተዋወቅ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 25 | ”ልብስም ጉርስም የሆነው ጓሳ“ | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ትውንጥበባት፣ ሀገረሰባዊ  ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል ። | ከታሪክ ከማስተላለፍ፤ ከቱሪዝም፤ ለአጥኝዎች ባህልን ከማቆየት፤ በዘመኑ የነበረውን ለአዲሱ ትውልድ ከስተዋወቅ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 26 | “ደብረሲና ማርያም ቤተ-ክር ስቲያን ጎርጎራ ጣና ሀይቅ” | የክብረ በዓላቱን ከዋዜማ ጀምሮ ይተርካሉ፡፡ ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ትውንጥበባት፣ | ሎሮችን ለሕዝብ በማስተዋወቅ፣ በማህበረሰብ ባህል ውስጥ ያሉ ቁምነገሮችን(ጭብጦችን) |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | በማስረዳት፣ጎብኝዎችን ከመቀስቀስ፣ የዘርፉን ተመራ ማሪዎች ከማነሳሳት፣የሃገርን ማንነት እንደ መስታዎት አንጸባርቆ ከማሳየት |
| 27 | "አቡነ ሙሴ ገዳም" | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ባህልን ከማስተማር፤ስለባህል ከመስበክ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ባህልን የማክበር፤ የመጠበቅ፤ ለተተኪው ትውልድ የማሸ ጋገር ፤ የተሻሉ ግንዛቤዎችን የመፍጠር ፋይዳ ዎችን ከማስገኘት የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 28 | "የታደለው የቦረና ብሄራዊ ፓርክ" | ስነ-ቃልን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ፎክሎር አንዱ መልስ የሚገኝበት ማህበረ-ባህላዊ ዕውቀት መሆኑን ያሳያል፤በሌላ በኩል በዚህ መነሻ የዘርፉተመራማሪዎችም ጥናት እንዲያካሂዱበት ያነሳሳል፡፡ |
| 29 | "የሼህ አሊ መካነቅርስ መቃብር ጎንደር" | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ከታሪክ ከማስተላለፍ፤ ከቱሪዝም፤ ለአጥኝዎች ባህልን ከማቆየት፤ በዘመኑ የነበረውን ለአዲሱ ትውልድ ከማስተዋወቅ የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |
| 30 | "ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ፤ | አንድም ፎክሎራዊ ጉዳይ አልተነሳበትም፡፡ | |
| 31 | "ከምንት ዋብ-ቁስቋም ጎንደር" | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድንና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ከታሪክ ከማስተላለፍ፤ ከቱሪዝም፤ ለአጥኝዎች ባህልን ከማቆየት፤ በዘመኑ የነበረውን ለአዲሱ ትውልድ ከማስተዋወቅ |
| 32 | "ድብቁ ውቅር ቅርስ ዞዝ አምባ ጊዮርጊስ" | ስነ-ቃልን፣ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ቁሳዊ ሃብቶች፣ አፈ-ታሪኮች ፣ ሀገረሰብ ምህንድስናን የተመለከቱ ተዘግበዋል። | ማህበረሰቡ ስለባህሉ ያለውን ግንዛቤ በሚፈለገው መጠን ለማሳደግ፣ አካባቢያዊ ማንነትን ሕዝባዊ ማንነትንና ሃገራዊ ማንነትን ለማንጸባረቅ፣የታሪክ ጭብጥን ለማመላከት፣ልማዳዊ ባህላዊ መገለጫዎች ትኩረትእንዲቸራቸውና እንዲጠኑ ከማስቻል የሚገኝ ፋይዳ፡፡ |

**ሰንጠረዥ 1.2:- የ"ጉዞ ኢዮጵያ "ፊልሞች ይዘትና ከፊልሞቹ የሚገኝ ፋይዳን የሚያሳይ**

## 4.2 በ2012 ዓ.ም በኢቢኤስ ቴሌቪዥን በኢትዮጵያን እንወቅ ፕሮግራም ውስጥ የቀረቡ ፎክሎራዊ ዘውጎች ትንተና።

| .ቁ | የቀረበው ፕሮግራም ርዕስ | ክፍል | የወሰደውደቃ | የቀረበበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | "የከፋ ጥብቅ ድኖች" በሚል የፕሮግራም ርዕስ የቀረበ ፕሮግራም | | 28:58 | May14/2020 |
| 2 | ‹‹ ጭሳማው ተራራ" በሚል ርዕስ የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል1 | 24:07 | May21/2020 |
| 3 | ‹‹ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም›› በሚል ርዕስ የቀረበ ፕሮግራም | | 24:06 | May 8/2020 |
| 4 | ‹‹በሰሜን ወሎ ላሊበላ አቅራቢያ የሚገኝ ጭስ አልባው ተራራ ›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል2 | 22:12 | May28/2020 |
| 5 | ‹‹የዲዚ ብሔረሰብ ስርአትና ባህላዊ የባላባት አሰያየም ስርዓት›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 25:15 | Feb12/2020 |
| 6 | ‹‹የድሬደዋን አንዳፍታ››በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል2 | 22:28 | Apr 9/2020 |
| 7 | ‹‹የድሬዳዋ የማይጠገቡ ሰፈሮች›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | ክፍል1 | 20:52 | Apr 2/2020 |
| 8 | ‹‹የአባይ ልጆች›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 26:49 | Apr24/2020 |
| 9 | ‹‹የጀባ ወርቅ አወጣጥ ፤ባህላዊ የወርቅ አወጣጥ›› በሚል የቀረበ ፕግራም | | 24:48 | Jan 1/2020 |
| 10 | ‹‹የዘጌ ፈርጥ ኡራ ኪዳነምህረት›› በሚል የቀረበ ፕሮግራም | | 25:41 | Jun11/2020 |

**ሰንጠረዥ 2፦ በኢቢኤስ ቴሌቪዥን በኢትዮጵያን እንወቅ ፕሮግራም ላይ የቀረቡ ፡፡**

**1ኛ/ "የከፋ ጥብቅ ደኖች" በሚል የፕሮግራም ርዕስ ላይ የቀረበ ትንተና ፡፡**

ከፍ ሲል ከቀረበው ሰንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው በኢቢኤስ ቴሌቭዥን ከቀረቡ ፎክሎራዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ ደኑ ከማህበረሰቡ ጋር ያለው ቁርኝት የተቃኘበት ነው፡፡ ደኑ የህይወት እስትንፋስን የያዘ ምድር መሆኑ፤ለከፋው ህዝብ ቤቱ በመሆን፤ለታመመው ለበሽታው ፈውስ የሚሆን የመድኃኒት መገኛ መሆኑ በፕሮግራሙ ተገልጧል፡፡ በተጨ ማሪም የሰው ልጅ ከተፈጥሮ እርቆ መኖር የማይችል መሆኑን ማሳያ ተደርጎም ቀርቧል፡፡ ደኑ ለከፋ ህዝብ ቤቱ፣ምግቡ እና ሲታመም መድሀኒት ማግኛው ከመሆኑም ባሻገር በሌላም በኩል የአምልኮ ስፍራውም ነው፡፡

የቴሌቭዥኑ ፕሮግራም ዝርዝር መረጃ እንዳመላከተው ሰዎች በዓመት ሁለት ጊዜ በጫካው ገብተው የሚከውኑበትና የአምልኮ ስነ-ስርዓትም የሚፈጸሙበት ሁኔታ አለ፡፡ ይኼውም ለማህበረሰቡ አምላኩን መለማመኛው፣ እርቅ ማውረጃው እና መጠለያው ነው፡፡ አምልኮ

የሚያከናውን የማህበረሰቡ አባል በሚያከናውንበት እለት የምስጋና እና የመስዋዕት ስርዓት ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ ፕሮግራሙ ሀገር በቀል እውቀት የሚከወንበት መሆኑን በዝርዝር የሚያብራራ ሲሆን በሌላም በኩል ደኑ የፈዋሽ መድሀኒት መገኛ ቦታ፤የግራዋ ማር በብዛት የሚገኝበት በመሆኑ ለማህበረሰቡ በተለያየ መንገድ የገቢ ምንጭም ማግኛ መሆኑን ዘገባው አመላክቷል፡፡ ማህበረሰቡም ከደኑ የሚገኘውን ሀብት በመጠቀም ከህመማቸን የምንፈወስበት ባህላዊ መድሀኒት ነው ብለው ያምናሉ፤ ይጠቀሙበታልም፡፡ ከዚህም ምንረዳው ከ21ኛው ክፍለ ዘመን በኋላም ማሕበረሰብና ጥንታዊው ባህል ሐገረሰባዊው ባህል፣ሐገረሰባዊው ልማድ የጠበቀ ቁርኝት እንዳላቸው የቀጠሉበት ሁኔታ መኖሩን ነው፡፡

በሌላም በኩል በደኑ ውስጥ ከሚገኙ ሀብቶች አንዱ የእግዜር ድልድይ ወይም የጉርጉቶ ድልድይ በመባል የሚታወቅ 50 ሜትር ቁመትና 5 ሜትር ስፋት ያለው ዝነኛ ድልድይ መገኛም መሆኑን ፕሮግራሙ ያስቃኘናል፡፡ በሌላም በኩል አካባቢው ሁለት ወንዞች የሚቀላቀሉበት መሆኑና ከቦንጋ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ እና ሰባ ሜትር ከፍታ ያለው ስለመሆኑም በፕሮግራሙ ቀርቦ እንመለከታለን፡፡

ከላይ የተመለከትነው ገለጻ እንደሚያስረዳው የቀረበው ፕሮግራም ከፎክሎር ዘውጎች አንፃር ሰው ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ትስስር እና ቁርኝት ለማሳየት የተሞከረበት መሆኑን ከቀረበው ፕሮግራም መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፕሮግራሙ ሀገር በቀል እውቀት ማህበረሰቡን እንዴት እየተጠቀመ እንዳለ በስፋት ለመዳሰስ የተሞከረበት መሆኑን ከቀረበው የ28:58 ደቂቃ ዝግጅት መረዳት ይቻላል፡፡ ለማሳያ ያህልም የባህላዊ መድሃኒት ቅመማና ህክምናን አንድናስብ ገለጻው ይጋብዛል፡፡ ይህ ደግሞ ፎክሎር ከሚያካትታቸው አበይት ዘርፎች መካከል አንዱ መሆኑ እሙን ነው፡፡

ዘገባውን ለታዳሚ ለማቅረብ የፈጀው ግማሽ ሰዓት ነው፡፡ይህ ታሪክ በዚህ መልክ መጠናቀሩ አንደአንድ የፎክሎር ዘውግ ሚናው ምንድን ነው?ወደሚለው የምርምሩ ጥያቄ  ስንመለስ ተከታዮቹን መሰረታዊ ምላሾች እናገኛለን፡፡ማህበረሰብን የማስተማር ባህልን የመትከል እንዲሁም አካባቢን የማስተዋወቅ ሚና አለው ማለት ይቻላል፡፡የከፋ ማህበራዊ ደን በሚለው በዚህ ሐገረሰባዊ ስም መልክዓ ምድራዊ ቦታዎች ልዩልዩ እጽዋቶች እና እንስሳት በመኖሪያነት ታድመውበት መገኘታቸው ለሀገረሰባዊ መድሃኒቶች ቅመማ አመችነት ያለው መሆኑና የከፋው ሰው ሳይቀር የሚደበቅበት መሆኑ መገለጹ መሰረታዊና አውዳዊ ፍቾች አሉት፡፡ በዓመት ሁለት ጊዜ አምልኮ የሚካሄድበት መሆኑም በኢቢኤስ ቴሌቭዥን ጉዞ ኢትዮጵያ ሳምንታዊ ፕሮግራም ተወስቷል፡፡ በመሆኑም ፕሮግራሙ ሕዝብን ለማንቃት፣

ባህሎችና ሕዝቦች የአንድነትም ገጽታዎች መሆናቸውን ለማሳየት፣ለመናንያን፣ለህገረሰባዊ መድሃኒት ቀማሚዎች፣በአጠቃላይ ለተመራማሪዎችና ለቱሪስቶች እንደንግድ ማስታወቂያ ለፈፋ በማድረግ የተሟላ መረጃ በመስጠት የተሻለ ሐገራዊ ስሜትና ማንነትን ለመፍጠር ተችሏል፡፡

**2ኛ/ "ጭሳማው ተራራ" (ክፍል 1) በሚል ፕሮግራም ላይ የቀረበ ትንተና ፡፡**

ይህ ፕሮግራም ትኩረቱን በሰሜን ወሎ ላሊበላ በሚገኘው ከፍተኛ ስፍራ ላይ አድርጎ አቡነ ዮሴፍን፣አባዊ ጋራን፣ዚጊት ተራራን የተመለከተ ዝግጅት ሲሆን 8059 ሄክታር የተከለ ለበትን ስፍራ የሚዳስስ ነው፡፡

አካባቢው በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ አእዋፋት መገኛ፣ የጦስኝ፣ የአስታና የጅብራ ተክሎችም መገኛ መሆኑ በስፋት በቴሌቭዥን ፕሮግራሙ ተብራርቷል፡፡

ዝግጅቱ አካባቢን እና መገኛ ስፍራን በማስቃኘት እና ልዩ ልዩ ስያሜዎችን በማቅረብ እና በማስተዋወቅ የቀረበ ሲሆን የ (24:07) የቴሌቭዥን ሽፋን አግኝቶ ለተመልካች የቀረበ ነው፡፡ ፕሮግራሙ ከፎክሎር ዘውግ አንፃር የዳሰሳቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ፎክሎር ነክ ይዘት በጥልቀ ትም ባይሆን ከስምና ከስያሜ አንፃር በጥቂቱ የታየበት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

**3ኛ/"ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም"በሚል ርዕስ የቀረበ ፕሮግራም ትንተና ፡፡**

‹‹ቅዱሱ ሀይቅ›› በመባል የሚታወቀው የጣና ሀይቅ ላይ የሚገኝ ስፍራ ሲሆን የጣና ሀይቅ ብለን የምንጠራው ይህ ስፍራ ከ35 በላይ ደሴቶች የሚገኙበት ቅዱስ ስፍራ ነው፡፡ አካባቢው ከባህርዳር ወደ አርባ አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አብርሃ ወአጽብሃ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለታቦቱ መሪነት የመረጡት መነኮሳት ገዳም፤ ከ4ኛው እስከ 12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዘለቀዉና የተቀዛቀዘዉ በ1268 ዓ/ም እንደገና አቡነ ሂሩተ አምላክ በተባሉ አባት እንደገና እንደተጀመረ ታሪኩን ፕሮግራሙ ያስቃኘናል፡፡

በሌላም በኩል የአስር ነገስታት አፅም መገኛ መሆኑን ከቀረበው ፕሮግራም መረዳት ተችሏል፡፡ ከነገስታቱም ውስጥ አፄ ዘርአያእቆብ፣ አፄ ሰርፀ ድንግል፣ አፄ ፋሲለደስ፣ወዘተ መሆናቸውን ከምስል ጋር አስደግፎ ለተመልካቹ ያቀርባል፡፡ በሌላም በኩል ስፍራው ሦስት ጊዜ መታደሱን እንዲሁም አፄ ፋሲል ከኖራ ሙዚየም ማሰራታቸውን፤ከ700 ዓመት በላይ ያስቆጠሩ መጽሐፍት የሚገኙበትን ከአስራ ሦስተኛው እስከ ከስድስት መቶ ክፍለ ዘመን

የአፄ ዳዊት፣የዘርዓያቆብ፣የሱሲኒዮስ፣አፅመ ነገስታት የሚገኙበት በተጨማሪም ነጋሪቶችና መለከቶች፤የአገልግሎት አልባሳትና መስቀሎች ጭምር ይገኙበታል።ባሁኑ ጊዜ የሚተዳደረው በርሻ፣ከብት ዕርባታ፣ፍራፍሬና ቡና በመሸጥ ይተዳደራሉ ።

ፕሮግራሙ ከፎክሎር አንፃር ሀገረሰባዊ ልማድን ፣ቁሳዊ ባህልን እና ሀገረሰባዊ ሙዚቃን የተመለከቱ ጉዳዮችን በቀረበው የ 24፡06 ደቂቃዎች ርዝማኔ ባለው ፕሮግራም ላይ ተዳሰው እናገኛቸዋለን።

## 4ኛ/"በሰሜን ወሎ ላሊበላ አቅራቢያ የሚገኝ ጭስ አልባው ተራራ (ክፍል2)" በሚል የቀረበ ፕሮግራም ትንተና ።

አቡነ ዩሴፍ፣ዚጊት እና አቦዊ ጋራ ዳግም ያገገሙ ስፍራዎች ናቸው። በባህል ከቀደምት አያቶች በተላለፈው መመሪያየሚጠበቅበት ጥብቅ ስፍራ ነው። አካባቢው አራት  ቀበሌዎችን የያዘ ስፍራ ነው። ሰው የአካባቢውን ጥቅም በመረዳቱ የሚጠብቀው በንቃት ነው። በፕሮ ግራሙ ላይ የአካባቢ ማህበረሰብ የሚሰጠው የቃል ምስክርነት ተካቶ ሲቀርብ እንመለከታለን። አስተባባሪዎች የቱሪዝምና የእንስሳት ባለሙያዎችን አካቶ በጠቅላላው የሚጠብቁት ስፍራ ነው።

ማህበረሰቡ በማህበራዊም ሆነ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ሲገናኝ ባለሙያዎች እግረመንገዳቸውን በስፍራው ተገኝተው ትምህርት በመስጠት ማህበረሰቡ የሚኖራቸውን ግንዛቤ እንዲዳብርና አካባቢ እንዴት ቢጠበቅ የሚገኘውን ጥቅም በማስገንዘብ የተፈጥሮ ሁኔታው ተጠብቆ እንዲዘልቅ እንዳደረገው ከፕሮግራሙ እንረዳለን።

በዚህም ምክንያት በስፍራው ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ሲያብራሩ ስፍራው ቀይ ቀበሮእና ጭላዳ ዝንጀሮ ለመኖሪያነት የተቸገሩበትና ተፈጥሮው በመበረዙ ምክንያት‹‹ተራራዉ ያለቅሳል››ይባል ነበር። ስፍራው ‹‹ጓሳ›› የሚባል ልብስም ጉርስም የሚሆን የሳር ዓይነት የሚበቅልበት በመሆኑ ለማህበረሰቡ የስራ እድል ፈጠራ እንዲመቻችላቸው እና የመሰረተ ልማት ተጠቃሚ ሆነዋል።

ስፍራው ከላሊበላ 43 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከተፈጥሮ እንክብካቤ አንፃር ተመራጭ ብቻም ሳይሆን ለስፔስ ሳይንስ ተመራጭ ያደረገው ከፍተኛ ቦታ በመሆኑ ተመራጭ አርጎታል። የህዋ ምርምር ከፍተኛ ስፍራ በሙሉ ከሌሎቹ የከፍተኛ ስፍራዎች ትይዩ በመሆኑም  በተለይም ከእስያ ፣ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካና ከደቡብ አሜሪካ እስፔስ ሳይንስ ከፍተኛ ስፍራዎች ትይዩ መሆን የሚችል ነው። በተለይም ደሞ ከቺሊ ቀጥሎ

አመቺና አዋጭ የሆነ የምርምር ስፍራ እንደሆነ በፕሮግራሙ ተጠቁሟል፡፡ የምርምር ጣቢያዎቹ አቡነዮሴፍ የምርምር ጣቢያና የአቦዊ የምርምር ጣቢያ በመባል ይታወቃሉ ፡፡ በስፍራውም ዩኒቨርስቲዎች ምርምር ያደርጉባቸዋል፡፡ እነሱም የመቀሌ ዩኒቨርስቲ፣ የወልዲያናየደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲዎች ምርመር የሚያደርጉ መምህራን መድበው በስፍራው ምርምር እንደሚደረግ በፕሮግራሙ እንመለከታለን፡፡

ፕሮግራሙ ከፎክሎር አንፃር ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህልን የተመለከቱ ጉዳዮችን በቀረበው የ22፡12 ደቂቃዎች ርዝማኔ ባለው ፕሮግራም ላይ ተዳሰው እናገኛቸዋለን፡፡

### 5ኛ/"የዲዚ ብሔረሰብ ስርአትና ባህላዊ የባላባት አሰያየም ስርዓት"በሚል የቀረበ ፕሮግራም ትንተና ፡፡

በፕሮግራሙ አዲሱ ቦርጂ አቀባበል ወይም ከአባቱ ሞት በኂላ የመጣውን የቡርጂ ባላባት የስልጣን ርክክብ  ስርዓት የሚያስቃኝ ነው፡፡

ስርዓቱን ለማከናወን  ከአፈር ቀለም ሰውነታቸውም በማስጌጥ ይቀበላሉ፡፡አዲሱ ቡርጂ ያባቱን ስልጣን የወረሰው ወይም የሚቀበለው ከአባቱ ሞት ወይም ባላባት ሲሞት ‹‹ጉፊ›› ይባላል፡፡ ስርዓቱ  የሚጠይቀውን የሞቱ አያቶቻችንን እናብላ የሚል ስርዓት የሚያደርጉበት ስርዓት እና አጋጌጥ ነው፡፡

ስርዓቱ የሚከናወንበት ወቅት ተነስተው ወደ ስፍራው ሲመጡ እየጨፈሩና እየዘፈኑ ነው፡፡ አብይው አንድ ሰው ነው፡፡ ከብት እየነዱ የሚመጡት እስኪመጡ ድረስ የቀደመ ካለ አንድ ገምቦ ቦርጼ የተሰጥቷቸው እየጠጡ ይጠባበቃሉ፡፡ ሁሉም ሲሰባሰብ  ከብቱ ተባርኮ ይታረድ እና ደሙ በቅጠልና በጋሻ ይቀዳና አያታቸው ድሮ ይተኛበት በነበረው በላይኛው ስፍራ በኩል ደሙን አፍሰው እንዲመረቁ ጠይቀው ይመለሳሉ፡፡ ዘር ስጠን፣ከበሽታ ጠብቀን፣ሰላም አደርገን ብለው ተመራርቀው ወደ ቀጣዩ ስነስርዓት ይሄዳሉ፡፡

ይህ ባህላዊ ስርዓት ከሶስት እስከ አራት መቶ ዓመታትን እንዳስቆጠሩ የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡ ቤንች ማጂ ዞን፣ ቤሮ ናማጂ ወረዳዎች ዲዚዎች በስፋት የሚኖርበት ስፍራዎች ናቸው፡፡ አሰፋፈራቸውም በአብይና ንዑስ የተከፈሉ ናቸው፡፡ በምዕራብ አካባቢ በኩል የሰፈረው ዲዚ ሲሆን በደቡብ በኩል አዲካስ ዲዚ፤ደጋ አካባቢ ማጂ ዲዚ ፤በምስራቅ በኩል ሳይ ዲዚ፤በሰሜን ደሞ የሜሽንና ጎቤ ዲዚ እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ ቤሮ፣ኬፊያ፣ህሮ፣ሙኢ፣ሲኪ፣ አሮ እና አብር ጎሳ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ፕሮግራሙ ስርዓቱን ሲያስቃኝ ከከሲታ ላም ላይ የሚወሰድ ደምና ከቦርዴ ጋር በመቀላቀል ታዳጊዎች እንዲጠጡ ያደርጋሉ።የአካባቢ ታዳጊዎች አጥንት የአካባቢው ወጣቶችም አጥንት እንዲለመልም፤ለበሽታ እጅ እንዳይሰጡ፤ዝናብና ፀሐይ ሳይበግራቸው እንዲሰሩ፤ከብቶች እንዳ ይከሱ ለማድረግ ሁነኛ ዘዴ ነው ብለው ያምናሉ።

የዲዚ ማህበረሰብ አመጣጡ ከካሲ ተገንጥሎ ነው ተብሎ ይታመናል።የዲዚዎች አካባቢ ቤሮ ቀበሌ ከአዲስ አበባ ስምንት መቶ ኪሎ ሜትር ላይ በቤንች ማጂ ዞን ይገኛል።

ዲዚዎች በቋንቋው፣ባህልና በጋብቻ አንድ ናቸው። ዲዚዎች ዘመናዊ አስተዳደር ስርአት ያላቸው ቅቡል የጎሳ መሪ መስርተው ይተዳደራሉ። በማኅበረሰቡ ባሕል መሰረት አንድ የዲዚ ማሕበረሰብ አባል ሲያርፍም ሞተ ተብሎ አይለቀስለትም በተቃራኒው ዘፈን ይዘፈናል፤ይጨፈራል። ስርዓቱ ከብቷን ግንባሯ ላይ በድንጋይ መቶ ይገላል። ዲዚዎች ጉልበት እና ጤና እንዲያገኙ ለማድረግ ሲባል ደም ይጠጣሉ።

በከብት ቆዳውም አባቱን በክብር ይቀብረዋል። ድንጋዩም ይቀመጣል። ሦስት ወይም አራት ዓመት ተቀምጦ እስኪደገስ ድረስ ትቀመጣለች። ሁሉም ባላባቶች ይመጣሉ። አራት ቀን ይደገሳል። ወራሽ እስኪነግስ ድረስ ፀጉሩን አይላጨውም ቅጠሏን ከአንገቱ አያወልቅም። ዲዚዎች የሚተዳደሩት በግብርና ሲሆን የሚያመርቱትም በቆሎና ማሽላ ነው። በሌላም በኩል እንሰትን በማምረት አምቾ አድርገው ይበላሉ፤ገበያም ይወስዳሉ ።

ፕሮግራሙ ከፎክሎር አንፃር ሀገረሰባዊ ልማድን፣ቁሳዊ ባህልን እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን እና ስነ-ቃልን የተመለከቱ ጉዳዮች በቀረበው የ25:15 ደቂቃዎች ርዝማኔ ባለው ፕሮግራም ላይ ተዳሰው እናገኛቸዋለን።

### 6ኛ/ "የድሬደዋን አንዳፍታ (ክፍል 2)"በሚል የቀረበ ፕሮግራም ትንተና ።

ለጋ ኦዳ ዋሻ እና ወዳጂ ዋሻ የጥንት ነዋሪዎች አሻራ ያለበት ስፍራ ነው። የመካከለኛው ዘመን የድንጋይ ላይ ጹሑፎች የሚገኙበትና ሌሎች የሚገኙበት ነው።

ከአምስት ሺ እስከ ሰባት ሺ ዓመታት ያስቆጠሩ ዋሻዎች ናቸው ። በድሬደዋ ገጠራማ ስፍራዎች ላይ ይገኛሉ። ከሰላሳ ስምንቱ የገጠር ቀበሌዎች በአንዱ ይገኛል። ቦታው ላይ እድሜ ያስቆጠረ ዋሻ ነው። በውስጡም በላይናበታች ባሉ የዋሻው ግግዳዎች ላይ የእንስሳት ስዕሎች የተሳሉበት ዋሻ ነው። በተጨማሪም የሰው ስዕሎች፣ትላልቅ ቀንድ ያላቸው እንስሳት፣የፊደል ቅርጽ ያላቸው ጽሁፎች የሚገኙበት ዋሻ ነው።

ከድሬ ደዋ ሃያስምንት ኪሎ ሜትር ቢያዋሌ ቀበሌ የሚገኘው ወዳጄ ዋሻ ከመኪናው ወርዶ ቦታው ላይ ለመድረስ በእግር ከ15 እስከ ሰላሳ ደቂቃ መሄድን ያስገድዳል፡፡ ስፍራው ሁለት መቶ ሃምሳ ከፍታ ያለውና በጣም የሚማርክ አካባቢ ነው፡፡ የአካባቢው ፈርጥ ወዳጆ ዋሻ በጣም ብዙ ሺ ዓመታትን ያስቆጠሩ ስዕሎች የሚገኙበት ነው፡፡

ስእሎቹ በነጭ፣በቀይና በቡኒ ቀለማት የተሳሉና እጅግ ማራኪ ናቸው፡፡ ከሌሎቹ በቀለማት በመሰላቸውም ከሌሎቹ ምስሎች የተለዩ ያደርጋቸዋል፡፡

የቤትና የዱር እንስሳ ስዕሎች በተላይም የግመሎች ስዕል በስፍራው መገኘቱ ጥንትም ማህበረሰብን ሲያገለግሉ እንደኖሩ ያሳያሉ፡፡

በዋሻው ሌላው የሚገኘው  የሰንጠረዥ ስእሎች እና የእጅ ምልክት ስዕሎች ናቸው፡፡
ፕሮግራሙ ከፎክሎር አንፃር ሀገረሰባዊ ልማድን፣ቁሳዊ ባህልን እና ስነ-ቃላዊ የሆኑና ይህንን የተመለከቱ ጉዳዮች በቀረበው የ22፡28 ደቂቃዎች ርዝማኔ ባለው ፕሮግራም ላይ ተዳሰው እናገኛቸዋለን፡፡

**7ኛ/"የድሬዳዋ የማይጠገቡ ሰፈሮች (ክፍል1) "በሚል የቀረበ ፕሮግራም ትንተና ፡፡**

መለያዋ የጅቡቲ፣የፍቅር እና የኢንዱስትሪ ከተማ በመሆኗ ለየት ያደርጋታል፡፡ ዘመናዊነትን አገልግሎት የኢትዮያዊነት ድርሻ የሚወስዱት አፄ ምኒልክ እ.ኤ.አ 1897 የባቡር ዝርጋታን መሳረት በማድረግ የተቆረቆረች እንደሆነ ይገመታል፡፡መልክዓ ምድሯ እና ጥሩውሃ ክምችት ያላት በመሆኑ ተመራጭ ያደርጋታል፡፡

የአርመን ምህንድስና ጥበብ የሚታይባቸው፤ሳምንት ሙሉ የሚጎበኙ የገብያ ስፍራዎች (ሶስት ስፍራዎች) የሚገኙባት ስትሆን መለያዎችዋም ከዚራ የድሬዳዋ መገለጫ ሲሆን የዛፎች በጥላዎችዋ እና በንፅህናዋ ነው፡፡

በፈረንሳይን የባቡር ሰራተኞች የተቆረቆረች እና ማረፊያ የነበረች ስፍራ ነች፡፡ ህንፃዎች በኪነ ህንፃ ጥበብ የተመራች ሲያደርጋት፤የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ህንፃ እና ለየት የሚያደርገው ባለሁለት የደውል ፒላር መለያ ነው፡፡ የቅዱስ ስራው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በ1908 በፈረንሳይ የተሰራ ነው፡፡ እስካሁን አገልግሎት እየሰጠ ያለው እድሜ ጠገብ የሆነና በአሰራሩ የተለየ ያደርገዋል ፡፡

የሚካኤል ቤተክርስቲያን የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን 1884 ዓ.ም በልዑል ራስ መኮንን ትዕዛዝ እንደተገነባ እና ከድሬደዋ ቤተመንግስት እኩል የተሰራን ነው፡፡ መጋላ

የቀደመ መስጊድ በ1902 ዓ.ም በጭቃ የተሰራ እና በልጅ እያሱ አዛዥነት እንደተገነባ ይነገራል።

በጠቅላላው ፕሮግራሙ ድሬደዋ በነባር ሰፈሮችዋ እና በኪነ ህንፃ ውበት ትታወቃለች የሚለውን ለማጉላት የቀረበ ይመስላል ።

ፕሮግራሙ ከፎክሎር አንፃር ሀገረሰባዊ ልማድ፣ቁሳዊ ባህል፣ስነ-ቃልና ከስነ-ቃል ዘውጎች አንዱ የሆነው አፈ-ታሪክም ተካቷል ።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ (የተመለከቱ) ጉዳዮች በቀረበው የ20:52 ደቂቃዎች ርዝማኔ ባለው ፕሮግራም ላይ ተካተው መገኘታቸው ለፎክሎር ዘዉጎችም ሆነ ፎክሎሮችን በመዘገብ ለማሰራጫቸው የቴሌቭዥን ጣቢያም የሚሰጡት ጠቀሜታ ስለመኖሩ በክፍል ሁለት የክለሳ ድርሳናት ክፍል ከልዩልዩ ምንጮች ተወስደው የተደራጁ መረጃዎች በውል ያስገነዝባሉ። ለአብነትም ከፎክሎር አኳያ በባህል ውስጥ ያሉ ጭብጦችን ለማስረዳት፣ባህላዊ አፈታሪኮችን ለመፍጠርና የባለቤትነትና የማሕበረሰብ ስሜት ለመፍጠር የሚሉትን ማንሳት ሲቻል። ለሚዲያው ደግሞ ተመልካች በእኔነት ስሜት ስለሚከታተለው የተሻለ ተደማጭና ተመራጭ እንዲሆን ያስችለዋል። ቴሌቭዥን በአንድ ሃገር ማህበረ-ባህላዊ ማንነት ውስጥ የሚጫወ ተውን ሚና አድማጭ ተመልካች በግልጽ እንዲረዳው የማድረግ ሚናን በፎክሎሮች መካተት የተነሳ ሊያገኝ ይችላል።

**8ኛ/ “የዓባይ ልጆች” በሚል የቀረበ ፕሮግራም ትንተና።**

ስፍራው‹‹ዓባይ›› ከሚል ቃል የተወረሰ መጠሪያ ያለው ነው። የዓባይን ወንዝ ታላቅነት ጠቋሚ ነው። ዓባይ ከአለም ታላላቅ ወንዞች አንዱ ነው።ከፏፏቴው ድረስ ሁለት አማራጮች አለን፡፡ የሚደረስበትን ታሪክ ለዘመናት እያስቃኘ ከቦታው ያደርሰናል። በድልድይ ላይ ያለው ስያሜ የተለያየ ሲሆን ፖርቹጋል ድልድይ፣ፋሲል ወይም እንቁላል የሚባል ስያሜ አለው። የአገሬውን በራርው የተለያየ ስያሜ ያለውን ስፍራ የሃገሬው ተወላጅ በኢትዮጵያና በግራኝ መሃመድ መካከል በተደረገው ጦርነት ቱርኮችን እና ፖርቹጋሎችን እየጋበዘ በመሆኑ ቦታ በፖርቹጋሎች መሠራቱን ይናገራሉ። እንቁላል እና ዱቄትይገብር የነበረው የሀገሬ ሰው በዛ ተሰራ በሚል የተሰጠው ስያሜ ነው። ትክክለኛ መጠሪያው ‹‹አላታ››የሚለው ሲሆን ይህም አካባቢው ካለው የዓባይ ገባር ወንዞች አንዱ መጠርያ ነው። አላታ ምእራብ ጎጃምና ደቡብ ጎንደርን የሚገናኝ ድልድይ ነው። በስፍራው ያካባቢው ነዋሪዎች የእደ ጥበብ ዉጤቶችን ይሸጣሉ።

የአባይ መነሻው ሰከላ ግሽ ዓባይ ሲሆን ከዛ ተነስቶ አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ኪሎ ሜትር ይጓዛል፡፡ ዋና ዋና ከተሞችን አቋርጦ ወይም ደሞ ለጉልበቱ የሚሆን ገባሮች ጨምሮ ይጓዛል፡፡ ፏፏቴው ለአርባ አምስት እስከ ዐርባ ሰባት ከፍታ አለው፡፡ ወደ ጎን አራት መቶ ሜትር ርዝመት ያለው ነው፡፡

የአካባቢው ሰዎች  እንግዳ አቀባበላቸው በጣም የተለየ ነው፡፡ ከቱሪስቶች የሚገኙት ገቢዎች ነጠላ ፣ከበሮ፣ አገልግል፣ ጨሌዎች  በመሸጥ እና ጌጣጌጥ  በመሸጥ እንዲሁም በአንገት ላይ የሚደረጉ እና በእጅ ላይ የሚደረጉ ጌጣጌጦችና ቁሳቁሶችን በመሸጥ ከቱሪዝም በሚገኘው ገቢ የአካባቢው ማህበረሰብ ይተዳደራል ፡፡

በቴሌቪዥን ፕሮግራሙ ላይ የቱሪስቶችን ፍሰትን የመጠቆሚያ በሚመስል መልኩ ቃለ ምልልስ ቀርቦበታል፡፡ ይኼውም ቱሪስቶችን በአማርኛ ቃለ-ምልልስ ሲደረግላቸው ይታያል፡፡ ይኼውም ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሲያቀርቡ ይታያል፡፡ የአካባቢ ልጆች ዋሽንት እንዴት እንደሚጫወቱ እና እንዴት እንደሚዘጋጅ ያሬድ የሚባል የአከባቢውን ልጅ በቃለ-መጠይቅና በተግባር ቀርቦበታል፡፡

የአካባቢው ልጆች ውሏቸው ከቱሪስቶች ጋር በመሆኑም ፎቶ ማንሳትና የእንግሊዝኛ  ቋንቋ መናገርን ችለዋል፡፡ ይህም በተግባር በፕሮግራሙ ላይ ቀርቦ ለማየት ተችሏል፡፡
ፕሮግራሙ ከፎክሎር አንፃር ሀገረሰባዊ ልማድን፣ቁሳዊ ባህልን እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን እና ስነ-ቃልን የተመለከቱ ጉዳዮች በቀረበው የ26፡49 ደቂቃዎች ርዝማኔ ባለው ፕሮግራም ላይ ተዳሰው እናገኛቸዋለን፡፡

## 9ኛ/"የጀባ ወርቅ አወጣጥ፤ባህላዊ የወርቅ አወጣጥ"በሚል የቀረበ ፕሮግራም ላይ የተሰጠ ትንተና ፡፡

ኦሮሚያ፣ትግራይና ደቡብ ክልሎች ወርቅ በማውጣት በኢትዮጵያ ተጠቃሽ ናቸው፡፡በደቡብ ክልል ቤንች ማጂ ዞን ቤሮ ወረዳ ያለውን ባህላዊ የወርቅ አወጣጥ ሁኔታን ያስቃኘናል፡፡ 750 ኪሎ ሜትር ከአዲስ አበባ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የጀባ ቀበሌ ወይና ደጋ የአየር ጠባይ ያለው ስፍራ ነው፡፡ የሌለ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ የለም፡፡ ነዋሪዎቹ ትንሿ ኢትዮጵያ በመባል ትታወቃለች፡፡ ነዋሪዎቹ ከኢትዮጵያ ወርቅ ለማውጣት ከተለያዩ አካባቢዎች ለሚመጡ ናቸው፡፡ ቆፋሪዎቹ በቀላሉ ወርቅ አያገኙም፡፡ ወርቁንም ለማግኘት ትእግስተኛ እና ተስፈኞች መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጪ አማራጭ የለም፡፡ ሾላ ወርቅ የሚገኝበት ስፍራ መጠሪያ ስፍራው ጎግል ተብሎ ይጠራል፡፡ የአንበሶች መንገድ  ማለት ነው፡፡

ከማእድን ቁፋሮ ውጪ የእጅ ስራ ውጤቶች የሚሠሩ አሉ፡፡ አንድ የወርቅ ጉድጓድ ለመቆፈር በትንሹ አምስት ሰዎች የሚሰማሩበት ሲሆን በትንሹ ከአራት እስከ ስድስት ቀን ይቆፍራሉ፡፡ ትልልቅ ድንጋዮች ምልክት ነው፡፡ ቆፍረው ካወጡ ወደ ሌላ ቦታ ጉድጓዱን ደፍነው ይጓዛሉ ማለት ነው፡፡ ስፍራው ህይወት  የሚያሳጣ ሲሆን ይህውም በናዳ ምክንያት ህይወታቸው ሊያልፍ ይችላል፡፡

ፕሮግራሙ ከፎክሎር አንፃር ሀገረሰባዊ ልማድን፣ቁሳዊ ባህልን እና ስነ-ቃላዊ የሆኑና ይህንንም የተመለከቱ ጉዳዮች የቀረበበት ሲሆን በቀረበው የ24፡48 ደቂቃዎች ርዝማኔ ባለው ፕሮግራም ላይ ተዳሰው እናገኛቸዋለን፡፡

**10ኛ/"የዘጌ ፈርጥ ኡራ ኪዳነ ምህረት"በሚል በተሰናዳ ፕሮግራም ላይ የቀረበ ትንተና ፡፡**

ይህ በጣና ሃይቅ ከሚገኙ ደሴቶች መካከል አንዱ በሆነው የኡራ ኪዳነ ምህረት ደሴት ላይ ተመስርቶ የቀረበው የኢቢኤስ ቴሌቭዥን ጉዞ ኢትዮጵያ ፕሮግራም እጅግ መሳጭና ወሳኝ የሆኑ የፎክሎር አይነቶች ተካትተው የቀረቡበት ነው፡፡ ዘጋቢዋ ለማቅረብ እንደሞከረችው ይህ ታሪካዊ ስፍራ ግማሽ አካሉ በየብስ ግማሽ አካሉ ደግሞ በውሃ ላይ ያረፈ ነው፡፡ ኡራ በስፋት ከሌሎቹ የጣና ደሴቶች ቀዳሚዉን ስፍራ የሚይዝ ሲሆን ስያሜውን ያገኘውም አቡነ በትረማርያም ለንግስ ከሌላ ስፍራ ሲመጡ አቡኑ ግን በዘንግ ሆነው ስላገኘዋቸው ነው፡፡በዛም የተነሳ ዘጌ እንደተባለ የሚነገር ታሪክ ስለመኖሩ ከዘገባው መረዳት ተችሏል፡፡

ኡራ ደሴትን ለማግኘት በዉሃ ጉዞና በየብስ ጉዞ ከተደረገ በኋላ ኡራ ኪዳነምህረት ደጃፍ ይደረሳል፡፡ ስፍራው የቃል ኪዳን በመሆኑ ጌሾና ቡናን እንዲያበቅል ቃል ኪዳን ስለተሰጠው ጌሾና ቡና በብዛት ይመረትበታል፡፡ በአጭሩ ኡራ ቡናና ጌሾን ጨምሮ በደን  የተሞላ ደሴት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለደሴቱ ፈርጥ የሆነችው ኡራ ኪዳነምህረት የጥንቱን ዋና የቤተክርስቲያን አሰራር ክብነትን ተከትሎ የተሰራች ሲሆን በዘመነ አምደ ጽዮን በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአቡነ ዮሴፍ አባት ከ(1632 ዓ.ም-1702 ዓ.ም) ባለው ጊዜ የገዳምነት ማዕረግ የሰጧት ስለመሆኑ በእለቱ በቀረበው ፕሮግራም ተጠቅሷል፡፡

የገዳሙ አባት ሲመሰክሩ መቅደስ፣ቅድስትና ቅኔ ቤት ያላት ይህች ውብ ቤተክርስቲያን የስላሴን አንድነትና ሶስትነት በሚገልጽ አምሳል መሰራቷን ጠቅሰዋል፡፡ ቤተ-ክርስቲያኗ12 በሮች እና12 መስኮቶች የተገጠሙላት ሲሆን ይህም በ12 ደቀ መዛሙርት ተምሳሌት ሆን ተብሎ የተሰራ ስለመሆኑ በኚሁ ታላቅ የደብሩ አበምኔት ተገልጧል፡፡ በሮቹ ከዋርካ እና ከዝግባ ተዘጋጅተው  የተገጠሙ ናቸው፡፡

የቤተ ክርስቲያኑ ጣሪያ የተሰራው ከበሬ ቆዳ በተዘጋጀ ገመድ ነው፡፡በውስጥ ያሉት ስዕሎች አዲስ ኪዳንን በሚተርክ መልኩ የቀረቡ ናቸው፡፡ የሰማታት ሰዕል፣ የኪዳነምህረት ስዕል ተስለው ይገኛሉ፡፡ጣራና ግድግው ብዙ የተጋድሎ ታሪኮችን የሚያስረዱ ስዕሎች አሉበት፡ በዚህ ቦታ የቤተክርስቲያኗ ሰባተኛው ንጉስ ተክለ ጊዮርጊስ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ካባና ልብሶቻቸውን ለቤተክርስቲያኑ አበርክተዋል፡፡

ስዕሎቹ የራሳቸው የአሳሳል ጥበብ ያላቸው ሲሆን ከላይ ወደታች ተዋረዳቸውን ጠብቀው የተሳሉ ሲሆን ከምእራባውያን የአሳሳል ቴክኒክ የተለየ ያሳሳል ዘዴን ተጠቅመዋል፡፡ በግድ ግዳዎች ላይ አቅጣጫቸውን ወደ ምዕራብ አድርገው የተሳሉ ስዕሎንችም የምናገኝበት ስፍራ ነው፡፡

በፕሮግራሙ ከፎክሎር አንፃር ሀገረሰባዊ ልማድን ፣በተለይም ቁሳዊ ባህልን እና ስነ-ቃላዊ የሆኑ ዘውጎች መካተታቸውን እናስተውላለን፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 2 እንደምንመለከተው እነዚህን የፎክሎር ዘውጎች የተመለከቱ ጉዳዮችን (በ25፡41)ደቂቃዎች ርዝማኔ ውስጥ ወፍበረራዊ በሆነ ቅኝት ለማቅረብ የተሞከረበት ሁኔታ ቢኖርም የተካተቱትን ሕዝባዊ ሎሮች እያንዳንዳቸውን ለማስረዳት ቢሞከር ፕሮግራሙ አውሎ የሚያሳድር ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡

በዚህ መሳጭ የቴሌቭዥን ዘገባ ውስጥ የተካተቱትን ሎሮችን ስንመለከት ሕዝባዊ እደ ጥበብ፣አፈታሪክ፣ቁሳዊ ሃብት(ሀገረሰባዊ ዕጅ ስራ)፣ሀገረሰባዊ ሥዕሎች፣ሃይማኖት(የስላሴን አንድነት ሶስትነት አመላካች የቤተክርስቲያኗ አሰራር) ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የነዚህ ልዩልዩ ፎክሎሮች በዘገባው ውስጥ መካተትም ከላይ በተከታታይ ሲገለጽ እንደነበረው የራሳቸው የሆነ ፋይዳ እንዳላቸው ግልጽ ነው፡፡ ከጠቀሜታቸው መካከል የተወሰኑትን ለመጠቆም ያህል የትረካውን አቀራረብ ለዛ የማላበስና አይረሴ እንዲሆን የማድረግ፣ የተሰለቸውን፤የተዘነጋውን ባህል የባህሉ ባለቤት ሰፊው ማህበረሰብ እንደገና ቆም ብሎ እንዲ ያጤነውና ያገባኛል ብሎም እንዲንከባከበው፣ከትውልድ ወደ ትውልድም እንዲያስተላልፈው የማድረግ ሚናን ይጫወታሉ፡፡ በአጭሩ የታዳሚን ልዩልዩ ተሳትፎ በማነቃቃት ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታን ያስገኛሉ፡፡ ከአካባቢው እርቆ ለሚገኘው ማህበረሰብ የማስተዋወቅ (ፕሮሞሽን) ስራ ይሰራሉ፡፡

## የ"ኢትዮጵያን እንወቅ "ፊልሞች ይዘትና ከፊልሞቹ የሚገኝ ፋይዳን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | በኢቢኤስ ቴሌቪዥን "ኢትዮጵያን እንወቅ "ፕሮግራም ላይ የቀረቡ | የቀረበው ፕሮግራም ይዘት ምሳሌዎች | ከቀረቡት ፕሮግራሞች የሚገኝ ፋይዳ |
|---|---|---|---|
| 1 | "የከፋ ጥብቅ ደኖች" | አምላኩን መለማመኛው፣እርቅ ማውረጃው እና ሲከፋው መጠለያው ነው:: ያሰው ከተፈጥሮ ጋር ለውን ትስስርና ቁርኝት ለማሳየት የተሞከረበት ነው:: ባህሎችና ሕዝቦች የአንድሳንቲም ገጽታዎች መሆናቸውን ለማሳየት የተሞከረበት ነው:: | ሕዝብን ለማንቃት፣ለሀገረሰባዊ መድሃኒት፤ ለተመራማሪዎችና ለቱሪስቶች ሐገራዊ ስሜትና ማንነትን ከመፍጠር የሚገኝ ፋይዳ |
| 2 | "ጭሳማው ተራራ" | ከስምና ከስያሜ አንፃር በጥቂቱ የታየበት ዘገባ ' | ከቱሪዝም ተመራማሪዎችን የመጋበዝ |
| 3 | "ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም" | ሀገረሰባዊ ልማድን፣ቁሳዊ ባህልንና ሀገረ ሰባዊ ሙዚቃን የተመለከቱ ዘገባዎች። | ከቱሪዝም፣ከመንፈሳዊነት፤ ከተመራማሪዎችን የመጋበዝ የሚገኝ ፋይዳ |
| 4 | "በሰሜን ወሎ ላሊበላ አቅራቢያ የሚገኝ ጭስ አልባው ተራራ" | ሀገረሰባዊ ልማድን እና ቁሳዊ ባህል፡ የተመለከቱ ዘገባዎች። | አፈ ታሪኮችን፣ባህልን ከማቆየትና ታሪክ ከማስተላለፍ የሚገኝ ፋይዳ |
| 5 | "የዲዚ ብሔረሰብ ስርአት ባህላዊ የባላባት አሰያየም ስርዓት" | ሀገረሰባዊ ልማድን፣ቁሳዊ ባህልን እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትንና ስነ-ቃልን የተመለከቱ ዘገባዎች። | ታሪክ ከማስተላለፍ&ባህልን ከማቆየት~ስነ-ምግባርን፤የመትከል&የማረጋገጥ ወይም የማፅደቅ፤ባህልን ከማቆየት የሚገኝ ፋይዳ |
| 6 | "የድሬደዋን አንዳፍታ" | ሀገረሰባዊ ልማድን፣ቁሳዊ ባህልንና ስነ-ቃልን የተመለከቱ ዘገባዎች ነባር ሰፈሮችና ኪነ-ህንፃ ውበት የተመለከቱ ዘገባዎች ። | አፈታሪኮችን፣ ባህልን ከማቆየት፣ ታሪክ ከማስተላለፍ የሚገኝ ፋይዳ |
| 7 | "የድሬዳዋ የማይጠገቡ ሰፈሮችና" | ሀገረሰባዊ ልማድ፣ቁሳዊ ባህል፣ስነ-ቃል(አፈ-ታሪክ) የተመለከቱ ዘገባዎች ። | በባህል ውስጥ ያሉ ጭብጦችን ለማስረዳት፣ባህላዊ አፈታሪኮችን ለመፍጠር የባለቤትነትና የማሕበረሰብ ስሜት ከመፍጠር የሚገኝ ፋይዳ |
| 8 | "የዓባይ ልጆች" | ሀገረሰባዊ ልማድን፣ቁሳዊ ባህልን፤ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትንና ስነ-ቃልን የተመለከቱ ዘገባዎች። | ባህልን ከማቆየት፣ታሪክ ከማስተላለፍ፣ ከመንፈሳዊነት፤የመትከል፤የአለባበስ፣ የአነጋገር፣ከቱሪዝም የሚገኝ ፋይዳ |
| 9 | "የጀባ ወርቅ አወጣጥ፤ ባህላዊ የወርቅ አወጣጥ" | ሀገረሰባዊ ልማድን፣ቁሳዊ ባህልን ና ስነ-ቃላዊ የሆኑ ዘገባዎች። | አነጋገር፣ከቱሪዝም፤ ከመንፈሳዊነት የሚገኝ ፋይዳ |
| 10 | "የዘጌ ፊርጥ ኡራ ኪዳነ ምህረት" | ሀገረሰባዊ ልማድን ፣በተለይም ቁሳዊ ባህልን እና ስነ-ቃላዊ የሆኑ ዘገባዎች።እደ ጥበብ፣አፈታሪክ፣ ቁሳዊ ሃብት(ዕጅ ስራ) ፣ሀገረሰባዊሥዕሎች፣ ሃይማኖት(የስላሴን አንድነት ሶስትነት የቤተክርስቲያኗ አሰራር) ዘገባዎች:: | ባህልን ከማቆየት፤ታሪክ ከማስ ተላለፍ፤ ከመንፈሳዊነት፤የመትከል፤ የአለባበስ፣የአነጋገር፣ከቱሪዝም የሚገኝ ፋይዳ |

ሰንጠረዥ:-2.1የ"ኢትዮጵያን እንወቅ "ፊልሞች ይዘትና ከፊልሞቹ የሚገኝ ፋይዳን የሚያሳይ

በአጠቃላይ የፎክሎር ዘውጎች በፋና እና በኢቢኤስ ቴሌቭዥን ፕሮግራሞች (ሚዲያዎች) ተካትተው መገኘታቸው በአንድም በሌላ መልኩ የሚያስገኙት ጠቀሜታ ስለመኖሩ በዚህ ጥናት የመረጃ ትንተና ክፍል (ምዕራፍ አራት)የቀረቡት ማብራሪያዎችና ገለጻዎች ተጨባጭ መረጃዎች ናቸው፡፡ በሁለቱም የቴሌቭዥን ጣቢያዎች የተዘገቡ በተለያዩ የፎክሎር ዘውግነት የሚፈረጁ የጥንት ዘመን የመካከለኛው ዘመንና የዘመነ ተሃድሶ ሃይማኖታዊ ታሪካዊ ፈጠ ራዊና ፍልስፍናዊ የሆኑ ልሂቅ ስራዎች ማህበረ ባህላዊ አሻራቸውን ጠብቀው በልዩልዩ ቦታዎች የሚገኙ መሆናቸውን ዘገባዎቹ አመላክተዋል፡፡ እነዚህ ጥንታዊነት ያላቸው እንደ ተረት አፈ-ታሪክ ጥንታዊ ባህላዊ ሙዚቃዎች ተሸሽገውና በገጠሩ ክፍል ብቻ ተወስነው ይኖሩ ከነበሩበት እንዲላቀቁ በሰፊው ማህበረሰብም እንዲታወቁ የዝቅተኛው ማኅበረሰብ መገ ለጫ ብቻ ሆነው ከተቀመጡበት አውድ እንዲላቀቁ መገናኛ ብዙሃን ከፍተኛ ሚና መጫወ ታቸውን በዚህ ጥናት ውስጥ በዋቢነት የቀረቡት ሰንጠረዦች ተጨባጭ መረጃዎች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ እነዚህን ልዩልዩ የፎክሎር ዘውጎች ዘግበው ለሰፊው ማኅበረሰብ ተደራሽ ማድረግ ለቻሉ የቴሌቭዥን ጣቢያዎችም ታዋቂነትን ከማስገኘትና ተደማጭነትን ከማስገኘት አኳያ የፎክሎር አይነቶች ያስገኙት ጠቀሜታም ፎክሎርና መገናኛ ብዙሀሃን ያላቸው ትስስ ር ተመጋጋቢ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

በምዕራፍ ሁለት ከተለያዩ ምንጮች ተለቅመው በክለሳ ድርሰኑ ክፍል የቀረቡ ንድፈ ሐሳ ቦችም የሚያመላክቱት ፎክሎርና ቴሌቭዥን (በአጠቃላይ ደግሞ ሚዲያ) የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎችን ያህል የማይነጣጠል ጥብቅ ቁርኝት ያላቸውና አንዱ ከሌላው የሚያገኘው ረብ ወይም ፋይዳ የጎላ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በሁለቱ ተተኳሪ የቴሌቭዠዥን ጣቢያዎች በ2012 ዓ.ም በተላለፉ ፕሮግራሞች ውስጥ አራቱም የፎክሎር ዘውጎች ተካትተው መገኘታቸው የተረጋገጠ ሲሆን ይህም በተዘዋዋሪ መንገድ ሚዲያዎች ለፎክሎራዊ ዘውጎች ከፍተኛ ትኩረት የሰጡ መሆናቸውን አመላካች ሆኖ ታይቷል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. ማጠቃለያና ይሁንታ

## 5.1.ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት በ2012 ዓ.ም በፋና "ጉዞ ኢትዮጵያ" እና በኢ.ቢ.ኤስ "ኢትዮጵያን እንወቅ" የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን መዞ በማውጣት የሚያስገኟቸውን ጠቀሜ ታዎች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተደራጀ ሲሆን በመግቢያው ክፍል በምእራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ ዓላማ፣የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች፣የትናቱ አስፈላጊነት፣የትናቱ ወሰን፣ ጣጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች የሚሉትን ንዑሳን ርእሶች ከነማብራሪያቸው አአካቷል፡፡ምዕራፍ ሁለት ከጥናቱ ርእሰ ጉዳዮች ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ልዩልዩ ጽሁፎችና እንዲሁም ከአሁን በፊት በተማሳሳይ ርእሰጉዳዮች ላይ የተጠኑ ቀደምት ጥናቶች ተዳስሰው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡በተመሳሳይ መልኩ ምዕራፍ ሶስት ደግሞ የጥናቱን ንድፍ፣የመረጃምንጭ፣የናሙ አመራረጥ ስልት የመረጃ መሰበሰቢያ መሳ ሪያዎች የሚሉትን ነኡሳን ርእሶች አካቷል፡፡ምራፍ ምዕራፍ አራት ደግሞ ደግሞ የተሰበሰበው የጥናቱ መረጃ ትንተና የቀረበበት ክልል ነው የመጨረሻው ምዕራፍ፤ምእራፍ አምስት ደግሞ የጥናቱ ማጠቃለያና የአጥኚው አስተያየት በዝርዝር የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

ጥናቱ አይነታዊ ሲሆን በዓላማ ንሞና አማካኝነት ከተለዩት የፋና እና የኢ.ቢ.ኤስ ቴሌቭዥን ጣቢያዎች ተቀራራቢነት ያላቸውን ሁለት ሳማንታዊ ፕሮግራሞችን(ጉዞ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያን እንወቅ)በመምረጥ ለትንተናው ተግባር የሚያገለግሉ መረጃዎችን ከነዚህ ምንጮች በመሰብሰብ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ዳር ለማድረስ ተሞክሯል፡፡

በሁለቱም የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ውስጥ በ2012 ዓ.ም በጉዞ ኢትዮጵያና በኢትዮያን እንወቅ ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ የተሰራጩ የፎክሎር አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ለመለየት ሙከራ የተደረገ ሲሆን በዚህ ሙከራም በተተኳሪ ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተቱ አጠቃላይ ፎክሎራዊ ጉዳዮች የተለዩ ሲሆን በዋናነት የሥነቃል፣ የሀገረሰባዊ ልማድ፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትና ቁሳዊ ባህል አራቱም ምድቦች በሁለቱም ተቋማት ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ መካተታቸው ተረጋግጧል፡፡

በሁለቱም የቴሌቭዥን ጣቢያዎች የተካተቱት ሕዝባዊ ሎሮች የየራሳቸው የሆነ አንዳች ረብ ወይም ፋይዳ ያላቸው መሆኑን መፈተሸ የዚህ ጥናት ዋናው ትኩረት በመሆኑ የገቡበትን

አውድ መሰረት ያደረገ ፍተሻ ተደርጎ የፎክሎራዊ ጉዳዮች መካተት ያስገኙት ፋይዳ ምን እንደሆነ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

በዚህም መሰረት የሥነ-ቃል ምድብ የሆኑት ቃል ግጥሞች በታቦታት የንግስ ስርአት ላይ ለሚደረግ የጭፈራ ዘፈን ግጥም በመሆን ያገለገሉበትና፤የታላላቆችና የሹማምንት ማሞገሻ በመሆን ያገለገሉበት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም አፈ-ታሪክ በተለያዩ አካባቢዎች ተከስተዋል ተብለው በሚታመኑ ያለፉ ታሪኮች ላይ በመመስረት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ እሴቶችን አስተሳሰብና እምነቶችን በመግለጽ ረገድ ጉሉህ ሚና የነበረው መሆኑን በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የሐገረሰባዊ ምድብ ከሆኑት ፎክሎሮች መካከልም እንዲሁ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሃገረ ሰባዊ መድሃኒቶች፣በተለያዩ የሐገሪቱ ክፍሎች የሚከወኑ ፌስቲቫሎችና ክብረ በዓላት፣ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ሎሮች፣የጥምቀትና የገና እንዲሁም ሌሎች መሰል ሕዝባዊ ሁነቶች ለጥናቱ በተመረጡ ሁለቱም የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ባስተላለፏቸው ሳምንታዊ ፕሮግራሞች ውስጥ መካተታቸው ታውቋል፡

በተመሳሳይ መልኩ በትውን ጥበባት ምድብ ውስጥ ከሚፈረጁ ፎክሎሮች መካከል ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በእስልምና ሃይማኖቶች ውስጥ የሚካሄዱ መንፈሳዊ የሀገረሰብ ሙዚቃዎች፣በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ የሚከናወኑ ሀገረሰባዊ ውዝዋዜዎች መኖራቸውን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡

የቁሳዊ ባህል ምድብ ከሚባሉት ፎክሎሮች መካከል ደግሞ በየቤተክርስቲያናቱ ውስጥ የሚገኙ ሕዝባዊ ሥዕሎች፣ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦችና መዋቢያዎች፣ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ስርአቶችን ለማድመቅ ግልጋሎት ላይ የዋሉ ሀገረሰባዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች(ከበሮ፤ ጽናጽል)፣የተለያዩ ሃገረሰባዊ ምግቦችና መጠጦችም እንዲሁ በጥናቱ ከተፈተሹና መካተታ ቸው ከተረጋገጡ ፎክሎሮች ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ጥናቱ ያጠነጠነባቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ስንመለከት ተተኳሪ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች በተመረጡት ፕሮግራሞች ውስጥ የትኞቹን የፎክሎር ዘውጎች አካትተዋል?፣ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በፕሮግራሞች ውስጥ መካተታቸው ለቴሌቭዥን ጣቢያዎቹ የሚያስገኙት ፋይዳ ምንድን ነው? የፎክሎሮች በቴሌቭዥን ፕሮግራሞች መካተትና ለስርጭት መብቃት ለፎክሎር ዘውጎችስ የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው? በተተኳሪዎቹ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ለፎክሎራዊ ጉዳዮች ስለተሰጠው ትኩረት ምን ማለት ይቻላል?የሚሉት ናቸው፡፡ለቀረቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ለማስገኘት ሲባልም ለትንተናዉ ተግባር የሚያስፈልገው

መረጃ በዋናነት በሰነድ ፍተሻ፣ እንዲሁም የመረጃን ተአማኒነትና ተቀባይነት ለማጉላት ሲባል ደግሞ የየቴሌቭዥኖቹን ሳምንታዊ ፕሮግራሞች አጠቃላይ ዝግጅት ምን መልክ እንዳላቸው ለመረዳት የሚያስችል ምልከታ በማካሄድም መረጃውን ለማጠናቀር ተሞክሯል፡፡

ለትንተናው ተግባር የሚውለውን መረጃ በተቻለ መጠን ተአማኒና ተቀባይ ለማድረግ ከተሞከረ በኋላ በገለጻና ትረካ ስልት ትንተናው ተካሂዷል በመሆኑም በጥናቱ የታቀዱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል፡፡ ይኼውም ከመጀመሪያው ጥያቄ ምላሽ ስንነሳ በ2012 ዓ.ም በፋና "ጉዞ ኢትዮጵያ" እና በኢቢኤስ "ኢትዮጵያን እንወቅ" ሳምንታዊ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ላይ በተሰራጩ ፕሮግራሞች የተካተቱ የፎክሎር ዘውጎች ከሥነ-ቃል ዘውጎች(ቃል ግጥሞች፣ አፈ-ታሪክ፣ ሀተታ ተፈጥሮ፣ ባህላዊ ዘፈንና የስራ ዘፈኖች)፣ ከሐገረሰባዊ ልማድ ፎክሎሮች ደግሞ (ሀገረሰባዊ ህክምና ሀገረሰባዊ እምነትና ሃይማኖት) ከሀገራዊ ትውን ጥበባትም ደግሞ(ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ሀገረሰባዊ ውዝዋዜ)እንዲሁም ከቁሳዊ ባህል የፎክሎር አይነቶች ደግሞ (ሀገረ ሰባዊ እጅ ስራ፣ሀገረሰባዊ ሥዕል፣ሀገረሰባዊ የሙዚቃ መሳሪያ፣ሀገረሰባዊ መዛግብት፣ሀገረሰባዊ ምህንድስና) ተካትተዋል፡፡ በአጭሩ አራቱ የፎክሎር ዘውጎች ሥነቃል፣ሀገረሰባዊ ልማድ፣ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብና ቁሳዊ ባህል በተተኳዋሪ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች መካተታቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

እነዚህ የፎክሎር ዘውጎች መካተታቸው ለቴሌቭዥን ጣቢያዎቹ የሚያስገኙት ፋይዳ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ የተገኙት ምላሾች የሚከተሉት ናቸው፡፡ የትረካ ስልትን በማሳመር የፕሮግራም ተደማጭነትን የማሳደግ ሚና ያላቸው መሆኑ፤ለማስታወቂያ ስራዎች ተደራሽነትና አይረሴነት የሚጫወቱት ሚና መኖሩ፣የታሪክ ጭብጥን ለማጉላትና ገጸ-ባህርያትን ለማቅረብም የማይናቅ ድርሻ ያላቸው መሆኑ፣አድማጭ ተመልካቾች ለጣቢያዎቹ አድናቂዎችና ደንበኞች ሆነው እንዲቀጥሉ የማድረግ ሚና እንዳላቸው፣በጥናቱ ተስተውሏል፡፡

በሌላ በኩል የልዩልዩ ፎክሎሮች በቴሌቭዥን ፕሮግራሞች መካተትና መሰራጨት የሕዝብ ሐብት ለሆኑት ፎክሎሮችም ጠቀሜታ እንዳለው በጥናቱ ታውቋል፡፡ ይኼውም የፎክሎሮቹ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ በማወቅም ባለማወቅም የዘነጋቸውን አንጡራ ሀብቱ የሆኑ ልዩ ልዩ ሎሮችን በባለቤትነት ስሜት ተንከባክቦ ለትውልድ እንዲያሻግራቸው በማድረግ ረገድ የማስተማር ሚና ስላላቸው ፎክሎሮች ህልውናቸው እንዲቀጥል ምክንያት የመሆን ጠቀሜታ አላቸው፡፡

የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች በአንዴ ለሰፊ አድማጭ ተመልካች የሚደርሱ በመሆኑ ፎክሎሮች በማህበረሰብ ዘንድ ይታወቁ ዘንድ ሰፊ ዕድል ያገኛሉ፤ከመገኛ ቦታቸው ርቀትና እንዲሁም

በተለያዩ ተፈጥሯዊ ምክንያቶች ለሰፊው ማህበረሰብ ተደራሽ ያልሆኑ ሃገራዊ ብሎም ዓለማቀፋዊ የሆኑ የሕዝብ ሎሮች የመታወቅ ዕድልን ያገኛሉ፣ማንበብና መጻፍ ለማይችሉ ሰፊ ማህበረሰቦች የፎክሎር ዘውጎችን በማስተዋወቅ ረገድ ሚና አላቸው የሚሉ ምላሾች በጥናቱ የትንተና ክፍል ተመላክተዋል፡፡

ጥናቱ ያጠነጠነበት ሌላኛው ጥያቄ ደግሞ ለጥናቱ የተለዩ የቴሌቭዥን ጣቢያዎች በየፕሮግራሞቻቸው ለፎክሎር ዘውጎች የሰጡት ትኩረት ምን ይመስላል? የሚል ነበር። ጥናቱ ተካሂዶ ዳር ሲደርስም በምዕራፍ አራት ከመረጃ ትንተናው ክፍል ማየት እንደተቻለው የፋና ቴሌቭዥንም ሆነ የኢቢኤስ ቴሌቭዥን ለዚህ ጥናት በተመረጡት ሳምንታዊ ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ ሰፊ ትኩረት የሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ይሁን እንጅ ፋና ቴሌቭዥን በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆነው በ2012ዓ.ም በዓመቱ ውስጥ ለ17 ሰዓታት ያህል ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በማካተት ከድግግሞሽ አንጻር ብልጫ አለው፡፡በአንጻሩ በኢቢኤስ ቴሌቭዥን ጣቢያ በዓመቱ ውስጥ አስር ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ብቻ የዘገበ ሲሆን ይህም በሰዓት ሽፋን ስምንት ሰዓታትን ይዟል፡፡ በሌላ አገላለጽ ያነሰ ድግግሞሽ የነበረው ሆኖ ታይቷል፡፡

ለትንተና ከቀረቡት ሰንጠረዦች ማየት እንደተቻለው በፋና ሰባት በፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ያጠነጠኑ ዘገባዎች ከክፍል አንድም በዘለለ በሁለት ተከታታይ ፕሮግራሞች የቀረቡበት ሁኔታ መኖሩ ተስተውሏል፤ በአንጻሩ በኢቢኤስ ጣቢያ ደግሞ ሁለት ሮግራሞች ብቻ በሁለት ክፍል ሲቀርቡ ቀሪዎቹ በክፍል አንድ ብቻ የተጠናቀቁ ነበሩ፡፡ ከዚህም የምንረዳው የተሰጣቸው ሽፋን እኩል ካለመሆኑም ባሻገር ልዩነቱም ሰፊ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል አራቱም የፎክሎር ዘውጎች አካትተው ከመገኘት አንጻር ልዩነት አላሳዩም፡፡

የፎክሎር ዘውጎችን በቴሌቭዥን ጣቢያዎች በየፕሮግራሞቻቸው ማሰራጨት ሚያስገኘው ፋይዳ(ከማህበረሰብ፣ ከተመልካች፣ ከቱሪዝም፣ ከማስተማር፣ ከኢኮኖሚያዊና ከፖለቲካዊ፣ ፎክሎር፣ከጥናትና ምርምር፣ከቴሌቭዥን ፕሮግራም ወዘተ) አንጻር ሲታይም ፈዋሽ ፀበል የሚገኝበት ስፍራ ህማመሥጋ ያለበት ለጸበለ ፈውስ እንዲበቃ፣ ህማመነፍስ ያለበት ደግሞ ወደ ታሪካዊውና ዘመን ተሻጋሪው የእምነት ስፍራ ቢመጣ ዋጋ እንደማያጣበት የመስበክን ፋይዳ፤የተዘነጉና ችላ የተባሉ የማህበረሰብ ሎሮችን መልሰው እንዲያገግሙ(እንዲታወሱ) የማድረግ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ማንነቶችን የመግራትና ቅርጽ የማስያዝ ሚና አለው፡፡ ለማህበረሰብ በሚያበረክቱት ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በዘመኑ ሳልነበረው በዘመኑ የነበረውን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ደረጃ ለአዲሱ

ትውልድ የማስተዋወቅ ሚና አለው፡፡ ሀገር በቀል ዕውቀት ከተፈጥሮ ጋር ተናቦ የመኖር ፋይዳ፤በልምድና በተግባራዊ ድግግሞሽ የዳበረ ዕዉቀትን የመግለጥ ሚናን ይጫወታሉ፡፡

በሌላ በኩል ባህላዊ ዳኝነትን የማስረጽ ሚና፤ ዲሞክራሲያዊ አኗኗርን የማለማመድ ሚናም አለው፡፡ባህልን ከማስተማር፤ስለባህል ከመስበክ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ባህልን የማክበር፤ የመጠበቅ፤ለተተኪው ትውልድ የማሸጋገር፤የተሻሉ ግንዛቤዎችን የመፍጠር ፋይዳ ዎችን የማስገኘት ሚና አለው፡፡ማህበረሰቡ ስለባህሉ ያለውን ግንዛቤ በሚፈለገው መጠን ለማሳደግ፣ አካባቢያዊ ማንነትን፣ሕዝባዊ ማንነትንና ሃገራዊ ማንነትን ለማንጸባረቅ፣የታሪክ ጭብጥን ለማመላከት፣ልማዳዊና ባህላዊ መገለጫዎች ትኩረት እንዲቸራቸው የማድረግ ሚና አለው፡፡

በሌላ በኩል የታዳሚን ቀልብ ቆንጥጦ የመያዝ፤ተመለተካቾች ወደራሳቸው ባህልና ልማድ፣ እሴት እንዲያስቡ የማድረግ ሚና አለው፡፡የታዳሚን ተሳትፎ የመቀስቀስና የማሳደግ ሚና አለው፤ እንዲሁም ኩራትን የማስገኘት ሚና ዓለው፤እንዲሁም ቱሪዝምን የማስተዋወቅና የማሳድግ ሚና አለው፡፡የፎክሎሮችን ህልውና ጠብቆ ለማሻገር አይነተኛ መሳሪያ ተብሎ እስከመቆጠር የሚያደርስ ዕውቅና ያስገኝላቸዋል፡፡

የፎክሎር ዘርፍ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች ለማህበረሰብ በሚያበረክቱት ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ እንዲሁም በፎክሎሮቹ መጻኢ እጣ ፋንታ ላይ ጥልቅ ጥናትና ምርምር ያካሂዱ ዘንድ መነሻ ምክንያት በመሆን የማገልገል ሚና አለው፡፡ ፡፡

በቅርስ ጥበቃና ክብካቤ ተግባር ሰፊው ማህበረሰብ እንዲሳተፍ የመቀስቀስ ሚናም አላቸው፡፡ ለቱሪስት መስህብነት እንደሚያገለግል በማስተዋወቅ ረገድ የመቀስቀሻ ሎር ሆኖ ያገለግላል፡፡ ለቴሌቭዥን ፕሮግራሙ ደግሞ የአለኝታነት ስሜትን ስለሚያስገኝ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅነትን እንዲያገኝ የማድረግ ሚናን ይጫወታሉ፡፡በፎክሎር ዘርፍ ለአጥኝዎች መረጃ ይደርስ ዘንድ ምክንያት የመሆን ሚና አለው፡፡

በጠቅላላው ማንበብና መጻፍ ለማይችሉ ማህበረሰቦች ስለባህላቸው ተጨባጭ መረጃዎችን ለማቅረብ፣ የታሪክ ነገራ (Story Telling) ስልቱን ተመራጭና በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ በማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ጭብጦችን በቀላሉ የማስረዳት፤ ማህበረሰቡን የማንቃትና የማስተማር፣ ኅብኝዎችን ከመቀስ ቀስ፣ የዘርፉን ተመራማሪዎች የማነሳሳት፣ የሃገርን ማንነት እንደ መስታዎት አንጸባርቆ የማሳየት ሚናን የማጎላት ፋይዳ አላቸው፡፡

## 5.2. ይሁንታ

የተለያዩ ፎክሎሮች በተለይም ሥነ-ቃሎች ትውልድን በሥነ ምግባር ከማነጽ አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑ የታወቀ ሲሆን (Bascom 1954) የአፍሪካ ሥነ-ቃሎችን በዋቢነት በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም አጠቃላይ የፎክሎር ዘውጎች ለማሕበረሰብ የሚያስገኟቸውን ጠቀሜታዎች ለማስቀጠል ይቻል ዘንድ በተለያዩ ሚዲያዎች የተሰማሩ የፕሮግራም ጋዜጠኞች በዚህ ላይ አጠንክረው ቢሰሩ፡፡

በዚህ ጥናት መመልከት እንደተቻለው ፎክሎር ከቴሌቭዥን ጋር ያለው ትስስር ከፍተኛ ነው፡፡በመሆኑም በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች በሚገኙባት ሀገር የየብሔረሰቦችን ባህሎች፣ልምዶች፣እምነቶች ሃይማኖቶችና አጠቃላይ ማህበረ-ባህላዊ እሴቶች ባሉበት ቀጥለው ከትውልድ ወደ ትውልድ መሸጋገር ይችሉ ዘንድ በቀላሉ በአንጼ ለሰፊው ማህበረሰብ ተደራሽ እንዲሆኑ በሚያስችሉ የቴሌቭዝን ፕሮግራሞች ተዘግበው የሚቀርቡበትና በየጊዜው በዘገባ መልክ የቀረቡትም ተሰንደው የሚቀመጡበትን አሰራር ባለድርሻ አካላት አጠንክረው ቢሰሩበት፡፡

ፎክሎር በባህሪው በቦታ በጊዜና በመከወኛ አጋጣሚው ተለዋዋጭ በመሆኑ በአንድ አካባቢ ያለውን የአንድ ማህበረሰብ የማንነት መገለጫ የሆነ ወግ ታሪክ፣ልማድና ባሕል በሌላ ጊዜና እንዲሁም አካባቢ ስናገኘው ተበርዞና ተከልሶ አልያም ከነአካቴው ተቀይሮ ሊሆን ስለሚችል ይህንን መሰል ችግር ለማስቀረት ባይቻልም እንኳን ለመቀነስ ሲባል ቴሌቭዥንን ጨምሮ ሌሎች መሰል ሚዲያዎችም ፎክሎሮችን በየፕሮግራሞቻቸው በማካተት ማህበረ-ባህላዊ እሴቶችን ጠብቆ ለማቆየትና ለተተኪ ትውልድ ለማስተላለፍ በሚደረገው ጥረት ተሳትፏቸ ውን ቢያጠናክሩ፡፡

የአንድ ሐገር አጠቃላይ ባህልና እሴቶች በመሰል የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች ተዘግበው መሰራጨታቸው ለትውልድ ለማቆየት ከማስቻሉም በላይ ለዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ በማስ ተዋወቅ በርካታ ጎብኚዎች ወደ ስፍራው ሊመጡ የሚችሉበትን አጋጣሚ መፍጠር ይቻል ዘንድም በተለያዩ የዓለም ቋንቋዎችም የሚዘገቡበትን አግባብ ለማሳደግ ባለድርሻ አካላት ቢተጉ፡፡

# የዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር


ሰለሞን ተሾመ፡፡ ፎክሎር ምንነቱ እና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር፣አዲስ አበባ፣2007 ዓ.ም፡፡

አዳነች አበራ፡፡ "የፎክሎር ቅርፅና ፋይዳ በተመረጡ የታሪክ መፃህፍትና ዜና መዋዕሎች ውስጥ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣2001 ዓ.ም፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ የሥነ-ፅሁፍ መሠረታውያን፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣አዲስ አበባ፣2004 ዓ.ም፡፡

ዘይባ ሁሴን፡፡ "የፎክሎር ጉዳዮች ፋይዳ ትንተና በመኤኒት እና በእምቢታ ታሪካዊ ልቦለድ ተተኳሪነት"። ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣2012 ዓ.ም።

ያለው እንዳወቅ፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም ባሕርዳር፣2004 ዓ.ም ፡፡

ዳንኤል ዘውዱ፣አንበሱ ቢያዝንና ፍቅሬ፡፡ የትምህርት ጥናትና ምርምር አተገባበር። ሙጋ አሳታሚ ድርጅት፣አዲስ አበባ፣1994 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የስነ ቃል መምሪያ፡፡ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት ተቋም፣1991 ዓ.ም፡፡

————፡፡ የሥነ ቃል መምሪያ፡፡ አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣አዲስ አበባ፣1992 ዓ.ም፡፡

ወሰን ባየ፡፡ "በኢትዮጵያ ቴአትር የተነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፋይዳ በተመረጡ ተውኔቶች ማሳያነት"፡፡ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ለፒ.ኤች.ዲ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2010፡፡

Bascom, William. "The Form of Folklore: Prose Narratives". The Journal of American Folklore. VOl.78. No 307. (Jan-Mar 1965) P3-20 http:/www.Jstor.org. Mar 22, 2006.

Ben-Amos. Toward definition of Folklore in Context. The Journal of American Folklore. 84 (331). 3-15.1971.

Bosinger H. Folkculture in the world of Technology .Trans,Elka Dettmer Bloomington: India ,India University Press. 1990.

Dough L. American Folklore and the Mass Media, Bloomington and Indian apply. Indiana University Press. 1994.

Dundes A. "What is Folklore?" The Study of Folklore . New Jersey: Prentice Hall,1965. 1-3. 1965.

Dundes, A. Folklore Matters, the University of Tennessee Press, Knoxville Elizabeth T.Ethnolingustic study: The Foklore Text BloomingtonIndia University Press.1980.

Handoo J.” Theoretical EssaYs in Indian Folklore”. Zooni Publications.2009.

Henderson B.Cuitural performance and popular entertainment: acomm Unications centerd hand book.PP.161-177.oxford university press.2003.

Hoofman F. Prologomena to astudy of Tradition Elements in the Erotic Films ,The Journal of American Folklore 78(308):143-148 https//antroholic.com applied f…Aug20 23.1965.

Martha C Sims and Martine Stephens.”Living Folklore: An Introduction To the study of People and Tradition Utah:” Utah State University.2005.

Jocy.L. “Motives ,themes and symbol”. New York Routledge.2014.

Koven M. “Film Folklore and Urban legends”. the scarecrow Press. Inc.Lanham,Maryland.2007.

Liyanage D. “Folklore and contemporaryMass Media”. AnAssessmentwith Special Refrence to Sri Lanka . (2013).

Newell V.J. “The Adaptation of folklore and tradition” (Folklorismus) ,Folklores 98(2):131-151.1994.

Newton V L. “Foklore and Advertising an examination of traditional Themes and motifs in British twenty first Century,Television Advertising Campaigns Folklife” 48 (1) 48-62. 2010.

Otero S. Iku and Cuban Nationhood: Yoruba Mytology in the Film Guant Anamaera፡africa Today46 (02):117-131. 1999.

Staemmler, B. Virtual Kamikakush: An element of Folk Belief in Changing Times and Media Jpanese Journal of Religious Studies .32(02):341- 352. 2oo5.

Sullenberger T. “Ajaks meets the J0lly Green Giant Someobservatios on The use of Folklore andMyth in American Mass marketing” ,The Journal of American Folklore 83(343) 53-65. 1974.

Tatira L.Proverbs in Zimbabwean Advrtisments.Journal of Folklore Research (3):229-241.2001.

Toelken, B. Dynamicsof the Folklore.Logan.Utah State Univ.Press.1996.

Wood J. Filiming Fairies: Popular Films Audience Response and Meaning In contemporary Fairy Lore,” 117 (03)279-296). (2006).

www.youtube.com/@travelethiopia

www.youtube.com/@ebstvWorldwid

# አባሪዎች

በጥናት ሥራዬ ትኩረት ባደረኩባቸው ሁለት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ላይ የቀረቡ ሥራዎችን ርዕስ አባሪ ለማድረግ ሞክሬያለሁ፡፡ እዚህ ላይ በራሴ ጥረት ያገኘኋቸውን አሰባሰብኩ እንጂ በጣቢያዎቹ የቀረቡት ሥራዎች እነዚህ ብቻ ስለመሆናቸው ማንም ርግጠኛ መሆን አልቻለም፡፡

በ2012 ዓ.ም በኢቢኤስ ቴሌቪዥን በኢትዮጵያን እንወቅ ላይ የተላለፉ ፕሮግራሞች


www.youtube.com/@ebstvWorldwide















ደቡብ ወሎ አባ ጊዮርጊስ ዘ ጋስጫ ገዳም/
ኢትዮጵያን እንወቅ፤ ምዕራፍ 4 ክፍል አንድ




ኢትዮጵያን እንወቅ "የሰሜን ተራሮች" /
DISCOVER ETHIOPIA SE 5 EP 9, ...




ኢትዮጵያን እንወቅ በሰሜን ወሎ ላሊብላ
አቅራቢያ/DISCOVER ETHIOPIA SE ...




ኢትዮጵያን እንወቅ የከፋ ጥብቅ ደኖች /
DISCOVER ETHIOPIA SEASON 4 ...





አስገራሚ እና ፈታኝ የሆነ ባህላዊ የወርቅ
አወጣጥ/Discover Ethiopia season...
ebstv worldwide · 19K views · 4 years ago

በ2012 ዓ.ም በፋና ቴሌቪዥን በጉዞ ኢትዮጵያ ፕሮግራም ላይ የተላለፉ ፕሮግራሞች

www.youtube.com/@travelethiopia-6169




ጎንደር የበለሳው ዘዝ አምባ ጊዮርጊስ
የቅዱሱና ንጉሡ የላሊበላ ቅርስ




ጉዞ ኢትዮጵያ-Travel Ethiopia
ከምንትዋብ እስከ ቁስቋም




ጉዞ ኢትዮጵያ ነጭ ሳር #የእግዜር ድልድይ
#ጫሞ ሐይቅ #አዞ ገበያ #Nichsar na...




የቦረና ተአምረኛ ምድር። ሜዳ አህያ። ሰጎን
አጋዘንና ሌሎች የሚፈነጩበት ጉዞ ኢትዮጵያ




ጉዞ ኢትዮጵያ-Travel Ethiopia-ደብረ ሲና
ማርያም ገዳም




የ400 ዓመት የእድሜ ባለጸጋው ልብስም
ጉርስም የሆነው ጓሳ የማህበረሰብ ጥብቅ...







#የም በፈውሱ ተራራ ዙሪያ #ቦር #እርከን
#Yem #MountBor #GuzoEthiopia...




ወደ ማጎ ብሔራዊ ፓርክ ጉዞ ኢትዮጵያ
Mago National Park travel Ethiop...




People also watched this video

ተራራን ያሸነፈ የቱሪዝም ልማት
#ጉዞኢትዮጵያ #ሀምበርቾ #777 #Ham...




ከአንኮበር እስከ ገማሳ ገደል
#ኮረማሽ#ጉዞኢትዮጵያ #Ankober #tr...




Ethiopia : እመ- ጓል ቅዱሱ ጽዋ
የተሰወረበት ተዓምረኛው በተ መንዝ እመጓ




የአባቶቻችን ድንቅ ስራ ማርያም ታምባ
ውቅር ተንቤን Maryam Tamba Tenben




ታላቁ ገዳም ጉንዳ ጉንዶ ማርያም በጉዞ
ኢትዮጵያ ከተጓዡ ጋዜጠኛ ጋር በጉዞ ኢትዮ...




በአለም የትም የሌለው ቆርኬ መጠለያ
ስንቅሌ, የቆርኪዎች መጠለያ በጉዞ ኢትዮ...




People also watched this video

የቦረና ተአምረኛ ምድር፡፡ ሜዳ አህያ፡፡ ሰጎን
አጋዘንና ሌሎች የሚፈነጩበት ጉዞ ኢትዮጵያ




ጉዞ ኢትዮጵያ-Travel Ethiopia - ጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ ክፍል 2




travel-Ethiopia:- የቡና ጫካ የሸፈናቸው የጌዴዮ ትክል ድንጋዮች




#ምሁር ኢየሱስ #አብነቱ ገዳም #ጉዞ ኢትዮጵያ #ጉራጌዞን #MehurEye...




#ኡራ ኪዳነምህረት #ጣና ደሴት #ጉዞ ኢትዮጵያ #UraKidaneMehret #Orth...



አባ ዩሐኒ የዐለት ምድርና የዐለት ሰማይ ያለው ውቅር ቤተ ክርስቲያን ተንቤን...
Travel Ethiopia-ጉዞ ኢትዮጵያ · 32K views · 4 years ago




Ethiopia : እመ- ጓል /እመጓ ቅዱሱ ጽዋ የተሰወረበት ተዓምረኛው ቦታ ክፍል 2



ሦስት ቀናትን በተከዜ ዳርቻ ከአፍሪቃ ዝኆኖች ጋር በቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ






ከጭፍረ እስከ ድብቁ ፏፏቴ በጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ የተሸሸገውን ተ...




ከዙር አባ #ቤተልሔም, #ጉዞ ኢትዮጵያ #Bethlehem,#Zur-Aba M...




ጉዞ ኢትዮጵያ-Travel Ethiopia - አዲስ ዓለም- ታሪካዊን መስጂድ እና የሼህ...
Travel Ethiopia-ጉዞ ኢትዮጵያ · 9.8K views · 7 years ago




የታላቁ ዓሊም የሼህ ዓሊ ጎንደር መካነ ቅርስ #በጉዞ ኢትዮጵያ







ታላቁ ገዳም ጉንዳ ጉንዶ ማርያም በጉዞ







People also watched this video

የ1600 አመት ውቅር #አቡነ ሙሴ ገዳም #ዳውንት #abun musse monastery...




የ400 ዓመት የእድሜ ባለጸጋው ልብስም ጉርስም የሆነው ጓሳ የማህበረሰብ ጥብቅ...